# ራስ አገዝ ወንጌላዊ

# Biovocational Missionary Evangelist

በሰሜናዊ ሲዳማ ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ

አባባ ሶርሳ ሱማሞ

አዘጋጅ:- ብራየን ኤል ፋርገር

ትርጉም:- በዳያሞ ዳንቃ

# ራስ አገዝ ወንጌላዊ
# Biovocational Missionary Evangelist

በሰሜናዊ ሲዳማ ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ
የአቶ ሶርሳ ሱማሞ ታሪክ፣

አዘጋጅ:- ብራየን ኤል ፋርገር
ትርጉም:- በዶያሞ ዶንቃ



# ራስ አገዝ ወንጌላዊ
# Biovocational Missionary Evangelist

በሰሜናዊ ሲዳማ ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ
አቶ ሶርሳ ሱማሞ

አዘጋጅ:- ብራየን ኤል ፋርገር
ትርጉም:- በዶያሞ ዶንቃ

<u>ዝርዝር መግለጫ</u>

አባባ ሶርሳ ሱማሞ ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ

1. ሶርሳ ሱማሞ
2. የቤተክርስቲያን ታሪክ በኢትዮጵያ
3. የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ታሪክ

በ1995 ዓ.ም ታተመ

# መታሰቢያነቱ

ይህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ መንፈስ ቅዱስ እንደመራቸው ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ወንጌልን ለሚሰብኩ ሁሉ የተሰጠ ነው:: እነርሱ መንፈስ ቅዱስ ለዚህ አገልግሎት የለያቸው የጌታ ባለሙያዎች ናቸው:: የእነርሱ ትጉህ አገልግሎት ባይኖር ቤተ ክርስቲያን ትጠፋ ነበር:: እነዚህ ወንጌላውያን ሁል ጊዜ በመጀመሪያዎቹ ትውልድ አብያተ ክርስቲያናት ፊት የሚታዩ፣ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ባደገች ቁጥር ደግሞ የማይታዩ ናቸው::

ኢየሱስ ተከታዮቹን ተዘዋዋሪ ሰባኪዎች ይሆኑ ዘንድ ላካቸው::

«ከዚህም በኋላ ጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ .... ሂዱ እነሆ እንደ በጐች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ.... ድውዮችን ፈውሱና የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀረበች በሉአቸው» (ሉቃስ 10÷1ቁ. 3ና 9)

ሐዋርያው ጳውሎስ ከቦታ ወደቦታ የሚዘዋወር ወንጌላዊ ሲሆን ከዚያ ወዲህ በብዙ ሺ የሚቆጠሩት አገልጋዮች በዓለም ዙሪያ መልካሙን ዜና ይሰብኩ ነበር:: ከቀድሞ ይበልጥ በአሁኑ ጊዜ የዚህን የወንጌል እውነት የማሰራጨት አስፈላጊነቱ የጐላ ሆኗል::

ይህ መጽሐፍ የመታሰቢያ መጽሐፍ ነው:: መታሰቢያ ማለት እናደርገው ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመራን ነው (ዘፀ. 28÷ 12፤ 39÷7):: ኢየሱስም ለመታሰቢያ እንድናደርግ የነገረንን በማቴ. 26 ÷ 13 እና በማር. 14÷9 ላይ እናገኛለን::

*ብራየን ኤል ፋርገር*



# ማውጫ

## ክፍል አንድ


መግቢያ ........ ገጽ
ራዕይ ........ 1
ምዕራፍ አንድ
የልብ መነሣሣት (የጋለ ስሜት) ........ 5
ምዕራፍ ሁለት
የእንጀራ እናቱ ........ 21
ምዕራፍ ሦስት
በወላይታ መተከል ........ 34
ምዕራፍ አራት
የሲዳማ ሕዝብ ........ 44
ምዕራፍ አምስት
ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ መሻገር ........ 54


## ክፍል ሁለት


መግቢያ ........ ገጽ
አብይ ጽኑ እምነቶች ........ 77
ምዕራፍ ስድስት
የመጀመሪያ ስብከቱ በአርኬ መንደር ........ 81
ምዕራፍ ሰባት
ቁጠር አንድ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች ........ 92
ምዕራፍ ስምንት
የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ........ 107
ምዕራፍ ዘጠኝ
ከሚስዮኑ ጋር በሲዳማ ........ 114


## ክፍል ሦስት


መግቢያ ........ ገጽ
የማያወላውል አቋም ........ 131
ምዕራፍ አሥር
ዋጮ ........ 134
ምዕራፍ አሥራ አንድ
አፍራራ ........ 148
ምዕራፍ አሥራ ሁለት
ፋክክርና ተቃውሞ ........ 169
ምዕራፍ አሥራ ሦስት
ማጠቃለያ ከብራየን ፋርገር ........ 188
ተጨማሪ
የእስቲቨንስ ቤተሰብ በደቡባዊ ሲዳማ ........ 203

# ምሥጋና

ከሁሉም አስቀድሜ ከመጀመሪያ ጀምሮ ያለውን የአባባ ሶርሳን ከሃምሳ ዓመት በላይ ያለውን ታሪክ የጻፉትን ዶክተር ብራዬን ፋርገርን (Dr. Brian Fargher) እና የቅርብ ረዳታቸውንና ባለቤታቸውን ዶሪስ ፋርገርን (Doris Fargher) በጣም አመሰግናለሁ::

ይህንን መጽሐፍ ወደ አማርኛ ቋንቋ እንድተረጉም ያበረታቱኝንና ያሳተሙትን ዶ/ር ፓውል ባሊስኪን (Dr. Paul Balisky) እና ባለቤታቸውን ላይላ ባሊስኪን (Lila Balisky) ጌታ ይባርካቸው እላለሁ::

በቀድሞ አጠራር በሲዳሞ ክ/ሃገር በሲዳማ አውራጃ በአለታ ወንዶ የአንደኛና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ያጠናቀቅሁት በኤስ. አይ. ኤም (S.I.M.) ት/ቤት ነው:: በጊዜው ዶክተር ፋርገርና ባለቤታቸው ዶሪስ እንዲሁም ዶክተር ፓውል ባሊስኪና ባለቤታቸው ላይላ በአለታ ወንዶ ሚስዮናውያን ሆነው ሲሰሩ ነበር::


ትውውቃችን ለ30 ዓመት ያህል ሲሆን፣ ግንኙነታችንም ሳይቋረጥ እስከ ዛሬ ደርሰናል:: ሁለቱም ቤተሰቦች እግዚአብሔርንና የኢትዮጵያን ሕዝብ አጥብቀው የሚወዱ ናቸው::

ይህንን መጽሐፍ ስተረጉም በሰሜናዊ ሲዳማ ያናሴ በሚባል አካባቢ እኔ የማላውቃቸውን የቦታ ስሞች በማስተካከል እንድጽፍ፣ እንዲሁም የታሪኩ ባለቤት አባባ ሶርሳ ወዳሉበት ወደ ሲዳሞ ለኩ ድረስ በመሄድ በአካል አግኝቷቸው የወላይታን አካባቢ ስሞችና ሌሎችንም ጥያቄዎች በመጠየቅ የተሟላና ትክክለኛ ዘገባ በማምጣት፤ በተጨማሪም አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮችንና ቃላትን በመለወጥ አንባቢያን በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ አድርጌ እንድጽፍ የረዳኝን አቶ ጴጥሮስ ገመጮን እግዚአብሔር ይባርከው እላለሁ::

በመጨረሻ ቃላትን በማሳካትና የፊደላት ግድፈቶችን በማስተካከል ከጐኔ ሆና የሞራል ድጋፍ በመስጠት የምታበረታታኝን ውድ ባለቤቴን አልማዝ ማርቆስን በሙሉ ልብ አመሰግናለሁ:: እንዲሁም በኮምፒውተር ታይፕ በማድረግና በማስተካከል ከፍተኛ እገዛ ያደረገችልኝን ወ/ት ሙሉወርቅ በሽርን ከልቤ አመሰግናለሁ::

ዶያሞ ዶንቃ





Map is from E. Paul Balisky's thesis, page 275a, added to by Petros Gemecho, November 2001.

SIDAMA



ይህንን መጽሐፍ ለመተርጐም የፈለግኩበት ምክንያት የመንፈሳዊ አገልግሎት ዕቅድን ከታሪኩ ባለቤት ሕይወት በግልጽ ለማሳየት እንጂ ዕቅዱን በተግባር ያሳዩ ዘንድ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸውን ሰው ለማወደስ አይደለም::

በተጨማሪም አባባ ሶርሳ ሱማሞ የቃለ ሕይወትን ሃይማኖታዊ ድርጅት በሲዳማ ለማስፋፋት ከሃምሳ ዓመት በላይ በተወሰነ ቦታ ረግተው ሳይቀመጡ ነገር ግን አስፈላጊ መስሎ ወደሚታያቸው ቦታዎች እየተዘዋወሩ በያዙት እምነት ወንጌልን ያሰራጩ መሆናቸውን ከታሪካቸው ስንረዳ በእምነታቸውም ምን ያህል ታማኝ መሆናቸውንና እግዚአብሔርን በቅንነት ለማገልገል ለሚፈልጉት ሁሉ መልካም አርአያ መሆናቸውን ሳልገልጽ አላልፍም::

አባባ ሶርሳ ከግማሽ ዕድሜያቸው በላይ በወንጌል አገልግሎት ላይ ያሳለፉ ሲሆን፣ በመልካም አገልግሎታቸው ምክንያት ብዙ መራራ ክስተቶችም እንዳጋጠሟቸው ስንረዳ ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞ. 4÷2 ላይ «ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፣ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፣ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም» ያለውን ቃል በትክክል በተግባር አሳይተዋልና እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካቸው::

*ዳያሞ ደንቃ*



## የታሪኩ /የፍሬ ሀሳቦች/ ቅደም ተከተል

- የተጻፉት ዓ.ም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው::

1917/ በግምት/ አቶ ሶርሳ ሱማሞ ተወለዱ::

1924 ታህሣሥ 17 የመጀመሪያው ጥምቀት በሲዳሞ፣

1925 ታህሣሥ 2 በወላይታ የመጀመሪያዎቹ አሥር አማኞች ተጠመቁ

1928 የአቶ ሶርሳ እንጀራ እናት ወደ ሶዶ ሆስፒታል ሄዱ

1929 ጥር 19 ጣሊያን ሶዶን ያዘ

1929 በወላይታ አማኞች በአራት መልክዓ ምድር አቅጣጫዎች

1929 ሚያዝያ 9 የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን ሶዶን ለቀቁ

1931 ጉዳቴ ጫቦ በዱጉና ወንጌልን አሰራጩ

1933 ግንቦት 19 የሶዶ ከተማ በብሪታንያ ኃይሎች ተያዘች

1933-1937 በወላይታ ቤተ ክርስቲያን ያደገችበት የነፃነት ዓመታት

1935 ሐምሌ ኘሊይፈር፣ ሮክና ኮውስር ወላይታን ጐበኙ

1937 መጋቢት ላውሪና ሊሊ ደቪስን ሶዶን ጐበኙ

1937 ሐምሌ ኦህማን፣ ሰልማ በርግስታንና ብትሪስ ባርናርድ ወደ ሶዶ ተዛወሩ

1938 ግንቦት ደልማርና ሜሪ እስቲቬንስን ወደ ሆማቾ ሄዱ

1938 ሕዳር ዶልማርና ሜሪ እስቲቬንስን ከሆማቾ ወደ አለታ ወንዶ ተዛወሩ

1938 ሕዳር ኦህማንና የሥራ ባልደረቦቹ ወደ ኦቶና ተዛወሩ

1938 ታህሳሥ የጤና ባለሙያ ት/ቤት ተከፈተ

1939 ሚያዝያ የውጪ አገርና የወላይታ ወንጌላውያን ሻሸመኔ ደረሱ

1939 ሚያዝያ በኦቶና የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ተከፈተ

1939 አቶ ሸንጋ ሳዴቦ ወንጌላዊ ሆነው ወደ ሲዳሞ ሄዱ

1942 ሐምሌ በሲዳማ ጉንዴ የመጀመሪያው የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ተካሄደ

1942 አቶ ሶርሳ አገቡ

1943 ጥር አቶ ሶርሳ ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ ተሻገሩ

1944 የመጀመሪያው ቃለ ሕይወት ማህበር በሰሜናዊው ሲዳማ ተመሠረተ

1943-1947 በአርኬ ሠሩ

1945 የመጀመሪያው ታላቁ ተቃውሞ በያናሴ

1947 በሐምሌ የእስቴቬንስ ቤተሰብ ወንዶን ለቅቀው ሄዱ

1947-1948 አቶ ሶርሳ ከነቤተሰባቸው ወደ ዋጮ ተዛወሩ

1945-1950 ጆርጅና ዶሪቲ ምድልተን በወንዶ

1950 አቶ ሶርሳ በወንዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት

1951-1953 ግሌን ቃየል በወንዶ

1951 60 የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ማህበራት በያናሴ ህጋዊ ሆኑ

1952 በያናሴ ሁለተኛ ታላቁ ተቃውሞ

1955-1960 ዶንና ቲኒ ግሬይ በወንዶ

1955-1965 ፒተርና ማርዩን ክላሴን በወንዶ

1960-1963 ፓውልና ላይላ ባሊስኪ በወንዶ

1966-1968 ብራየንና ዶሪስ ፋርገር በወንዶ

1966-1983 አብዮታዊ ሥርነቀል ለውጥ

1981-1982 ወደ ለኩ ተዛወሩ

1993 እድመንትን አልቤርታ ካናዳን ጐበኙ



## መግለጫ

ይህ ድንቅ ታሪክ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ በሰሜናዊው ሲዳማ ሐዋርያ ስለሆኑት ሰው የሚያወሳን ነው::

አቶ ሶርሳ ሱማሞ ማራኪ ያልሆነ ተክለ ሰውነት ያላቸው ቁመተ አጭር ሰው ናቸው:: ነገር ግን ራዕያቸውን፣ ጽኑ እምነታቸውንና ምርጫቸውን ስንገምት ከ50 ዓመታት በላይ በታማኝነት በማገልገል ለጌታ ብዙ ፍሬ ያፈሩ አባት ናቸው::

ይህ መጽሐፍ የመልካም ነገር ክምችት ሆኖ በዶክተር ብራየን ፋርገር ታላቅ ማስተዋል የተዘጋጀ ነው:: ምክንያቱም ዶ/ር ፋርገር ራሳቸው ከኤስ.አይ.ኤም ጋር በኢትዮጵያ ለ30 ዓመታት ያህል ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ ሆነው ያገለገሉ ነበሩ::

በአሁኑ ጊዜ ዶ/ር ፋርገር ከባለቤታቸው ወ/ሮ ዶሪስ ጋር ከካምፐስ ክሩሴድ የወንጌል አገልግሎት በካናዳ እድመንትን አልቤርታ ውስጥ ይገኛሉ::

የአቶ ሶርሳ ታሪክ በግልጽ የሚታይ፣ አሳዛኝ፣ ጽኑ አቋማቸውንና ታማኝነታቸውን ያቀፈ ነው::

በዚህ ትረካ ውስጥ ዶ/ር ፋርገር ቤተክርስቲያንን ስለ መመሥረት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ መመሪያዎች ይጋብዙናል::

ይህ የአቶ ሶርሳ ሱማሞ የሕይወት ታሪክ በፍቃደኝነት ምቹ መኖሪያቸውን ለቅቀው በሰሜናዊ ስኮትላንድ በሳክሰን ኢንግላንድ ዋርላይክ ፒክስ አካባቢ ወንጌልን እንደሰበኩት የክልቲክ ወንጌላውያን ጋር ይመሳሰላል::

የክልቲክ ወንጌላውያን በባህር ነውጥና ባልሰለጠኑ ጐሳዎች መካከል ፍርሃት እንደነበረባቸው አቶ ሶርሳም በወንዝ ሙላትና ለዝናቸው ሲሉ ሰውን በሚገድሉ በሲዳማ ሰዎች ምክንያት ፍርሃት ነበረባቸው:: ከአቶ ሶርሳ ሱማሞ ሕይወት የምንይዘው ነጥብ በጨረፍታ ታይቶ የማይታለፍ ለውጥ በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የተዳረሰ መሆኑን ነው::

በመቶዎች የሚቆጠሩ ተራ ክርስቲያኖች «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ» የሚለውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዝ በትጋት ተቀብለዋል:: በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ራሳቸውንም በመሠዋት የብዙውን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕዝብ የለወጡት እነዚያ የወንጌል መልዕክተኞች ናቸው::

የዚህን መጽሐፍ ዝርዝር የሚያነብ ሁሉ በፍሬ ሃሳቡ ዙሪያ ማንነቱን እንደሚፈትሽ እናምናለን::

*ፓውልና ላይላ ባሊስኪ*
*ኤስ.አይ.ኤም ኢትዮጵያ*
*ጥር 21 ቀን 1993*

# መግቢያ

## ብራዬን ፋርገር

በ1993 ዓ.ም ቲቶ ኀሬስሌር የተባለው ፀሐፊ በኮውልይ ማተሚያ ቤት በጻፈው መጽሐፉ የተናገረው ቃል:-

የአብርሃም ጥሪ የተመሠረተው በማያቋርጥና ጽኑ በሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት እግዚአብሔር ለብዙዎቹ የራሱን አብይ ሃሳብ ለማድረስ እርሱን እንደመረጠ ማስተዋል ይቻላል የሚል ነው::

በዚሁ ምዕራፍ የተሰጠው ርዕስ ሰባኪው «እግዚአብሔር በጥቅስ ውስጥ» ብሎ እውነታው እግዚአብሔር በግለሰቦች በኩል እንደሚሠራና አንዱን ወዲያው በብቃት መርጦ ወደ ብዙዎቹ እንደሚልክ መረዳት ነው ብኋል::»

ይህ የሚያነብቡት መጽሐፍ ብዙዎችን በወንጌል ይደርሱ ዘንድ እግዚአብሔር ስለመረጣቸው ወንጌላዊ የሚተርክ ነው::

እግዚአብሔር ታማኝ፣ ሁልጊዜ በስፍራው የሚገኝና ማስተማር የሚችል ሰውን ይፈልጋል:: አቶ ሶርሳ ሱማሞ ሦስቱም ብቃት ነበራቸው:: እኚህ ሰው እግዚአብሔር ወንጌላዊ እንዲሆኑ የሰጣቸውን ጥሪ ባለመጣላቸው በአገር ውስጥና በካናዳም ሳይቀር ታማኝ ሆነዋል::

እምነት ማለት የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብሎ በተግባር ማሳየት ከሆነ፣ አቶ ሶርሳ ይህን የፈፀሙ ታማኝ አገልጋይ ናቸው:: እርሳቸው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስቀድሙ በመሆናቸው በየትኛውም ሥፍራ የሚገኙ ናቸው:: አቶ ሶርሳ የተመረጡ አገልጋይ ናቸው:: የገንዘብ ማግኛቸው የተመሠረተውም በእርሻቸው ነው:: ዳሩ ግን የስብከት አገልግሎታቸውን ምንጊዜም ከእርሻቸው ያስቀድማሉ:: ልባቸው ዘወትር ወደ እርሻቸው ሳይሆን ወደ ስብከታቸው ያደላ ነው::

አቶ ሶርሳ ማስተማር የሚችሉ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ፈጣን ታዛዥ ከመሆናቸውም በላይ ለውጫዊው ማንነታቸው በምንም ሁኔታ ክብር የማይሰጡ ናቸው::

ይህ ማለት ሁልጊዜ ትክክል ናቸው ማለት አይደለም! ቢሳሳቱ እንኳን ስህተታቸውን ለመቀበል የተዘጋጀ ልብ አላቸው:: ሕይወታቸውን ለአንድ ዓላማ ያተኮሩ ከመሆናቸው የተነሳ የማስተማር ብቃታቸው የጐላ ሆኖ ይታያሉ::



ሰዎች በማንኛውም ሥፍራ ወንጌልን ለመስበክ መልካም አጋጣሚ የሚፈጥርላቸው ከሆነ ምንጊዜም በቅድሚያ ለመስማት ለማየትና ለመማር ይሻሉ::

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በቅድሚያ በኢትዮጵያ ውስጥ የምትገኘውን የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለማወቅ ለሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ነው::

አቶ ሶርሳ ሱማሞ እዚህም እዚያም መሠረት የጣሉለትን ትልቅ ሕንፃ የክርስቶስ አካል /ቤተክርስቲያን/ ብለን እንጠራለን::

በዚህ መልኩ ነበር ካቴድራሎች አንዱን ድንጋይ በአንድ ጊዜ በማስቀመጥ የመሰረቱት አቶ ሶርሳ የሕዝቡን ትኩረት የሚስብ ልዩ ነገር አላደረጉም፣ ፀጉር የሚያቆም አስደንጋጭ ታሪክ በፍፁም አያወሩም፣ ለዓመታት የሚቆይ እሥርም አላጋጠማቸውም፣ አብይ ተግባራቸው አንዱን እግር ከአንዱ እያስቀደሙ ብዙ ሺ ኪሎ ሜትሮችን በእግራቸው እየተጓዙ በለሜናዊው ሲዳማ ወንጌልን ማሰራጨት ነበር::

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ የአገልግሎት ዕቅድን በግልጽ ለማሳየት እንጂ ዕቅዱን ለመተግበር እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰው ለማወደስ አይደለም::

አቶ ሶርሳ ሱማሞ በአገልግሎት ዘመናቸው ለመታየት ብለው ያሳኩትና የሕዝብን ስሜት ለመሳብ ያደረጉት ጥረት አልነበረም:: አብዛኛውን ጊዜ ለመታየት አይፈልጉም:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለመግለጽ የተፈለገው አቶ ሶርሳ የሠሩትን ሥራ ለሰዎች ለማሳወቅ ሳይሆን እግዚአብሔር በእርሳቸው በኩል የሠራውን ታላቅ ሥራ ሕዝብ እንዲያውቅ ለማድረግ ነው::

የዚህ ንዑስ ርዕስ እቅድ የአቶ ሶርሳ ሱማሞን መንፈሳዊ ምርት ለመግለጽ ነው:: በ21ኛው ክፍለ ዘመን የተላከ የሚለው ቃል አዲስ ትርጉም ይዟል:: ማንኛውም ሰው ያመነበትን ሃይማኖት ለመስበክ ከአገሩ ውጪ የሚሄድ የተላከ «ሚሽኔሪ» ተብሎ ይጠራል:: ስለዚህም ነው ቃሉን ወንጌላዊ ከሚለው ቃል ጋር ማገናኘት አስፈላጊ የሆነው::

የተላከ፣ ወንጌላዊ ልዩ ባለሙያ ነው:: እርሱ በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ብዙ ክንውኖች እንዳሉ የሚያስታውቅ ሲሆን፣ ቀዳሚ ተልዕኮው ወንጌልን መስበክ ነው:: እንደ ሌሎቹ ባለሙያዎች የእርሱም የሥራ መስክ ጠባብ ነው:: አቶ ሶርሳ ተከራካሪና የሃይማኖት ሊቅ

አይደሉም። ሃይለኛ ተናጋሪ ወይም የቤተክርስቲያን ሽማግሌም አይደሉም። እርሳቸው የመልካም ዜና አብሳሪ /ሰባኪ/ ናቸው።

የእርሳቸው ዓላማና ግብ የእግዚአብሔርን ቃል በፍፁም ሰምተው ለማያውቁት ወንጌልን መመስከር ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ በአቶ ሶርሳ ሱማሞ አገልግሎት ዙሪያ ሦስት ነጥቦችን ጭብጥ እናስይዛለን፣

እነዚህም ጭብጥ ነጥቦች

ራዕይ፣ ጽኑ እምነትና መወሰን ናቸው።

## ራዕይ

ራዕይ ማለት ጥልቅ የፍቅር ስሜትን ያመለክታል፣ ይህም ማለት የሚያቃጥል ስሜት፣ ላመኑበት ነገር ለመሞት እንኳን የሚያስወስን ስሜት ማለት ሲሆን፣ የአንድ ሰው የአገልግሎቱ የልብ ምት ማለት ነው። ራዕይ ያለው ሰው ምንጊዜም የሚናገረው ስለዚያ ስለአንዱ ነገር ይሆናል።

## ጽኑ እምነት

ጽኑ እምነት የአገልግሎት ዋነኛው ክፍል ነው። ወንጌላዊ የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ የሰዎች ሕይወት ሊለወጥ እንደሚችል ቅንጣት እንኳ አይጠራጠርም።

እነዚያ የተለወጡት ሰዎችም ቤተክርስቲያንን መመሥረት እንደሚችሉ ያምናል። እነዚያ አብያተ ክርስቲያናት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተለወጡ የሰዎች ስብስብ ናቸው። እነርሱ የሰሙትን መልካም ዜና ላልሰሙት ሰዎች በትጋት የሚያሰሙ ናቸው።

ከዚያም የፍላጎት ኃይልና የውሳኔ ተግባራት ይከናወናሉ፤ ያም ተልዕኮ ማለት ነው። አቶ ሶርሳ ሱማሞ የተሟላ ልምድ ያካበቱ ናቸው። ከልምድ ውጪ የሆነ ሌላ የስብከት ዘዴ የላቸውም። ግን ይሰብካሉ።

የእርሳቸው ተልዕኮ ጉልበት እስካላቸው ድረስ የእውነትን ቃል መስበክ ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ያላቸውን ጉጉት ያመለክታል።

## ራስ አገዝ (Bivocational)

ራስ አገዝ የሚለው ሐረግ ስያሜ አቶ ሶርሳ ሱማሞ ሁልጊዜ ሁለት ሥራ እንደሚያከናውኑ ለመግለጽ ነው። እርሳቸው የሙሉ ጊዜ፣ ወንጌላዊና የሙሉ ጊዜ ገበሬ ናቸው። በሳምንት ውስጥ ባሉት 6 ቀናት ገበሬ ናቸው፣ በሌላው ጊዜ በሳምንት ውስጥ 7 ቀናት ሰባኪና ወንጌላዊ ናቸው።



ከነዚህ ከሁለቱ ሥራዎቻቸው ውስጥ በአንዱ ብቻ የገቢ ምንጭ ያገኛሉ። ነገር ግን ለእርሳቸው ትልቅ እርካታ የሚሰጣቸው ምንም ገንዘብ የማያገኙበት ሥራ ወንጌልን መስበክ ነው።

በሌላው ዓለም እንደሚታወቀው ሁሉ በኢትዮጵያም በቅንነት የግልን ሥራ እየሠሩ ወንጌልን መስበክ የተለመደ አይደለም። ወንጌላዊ፣ ማለት ለአገልግሎቱ የመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ባለሙያ ማለት ነው። ወንጌል በመስበኩ ሥጋዊ ጥቅም ባያገኝም ነፍሳትን ለማዳን በመቻሉ በእግዚአብሔር እና በሰዎች ዘንድ ክበሬታ አለው።

የወንጌል አገልጋይ ማለት ለቤተክርስቲያን ሥራ በሳምንት አራት ወይም ስድስት ሰዓት የሚቸር ማለት አይደለም። ወይንም ሳምንቱን በሙሉ ሥራውን እያከናወነ እሁድ ዕለት ብቻ ብቅ ብሎ የሚሰብክ ማለት አይደለም። አገልግሎቱ በጊዜ የተገደበ አይደለም «ቃሉን ስበክ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና ፈጽመህ እየታገስክና እያስተማርክ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም» (2ጢሞ. 4:2) ተብሏልና።

አቶ ሶርሳ ሱማሞ እውነተኛ ወንጌላዊ ናቸው።ሰባኪ የሚባሉ ብዙ ወንጌላውያን አሉ፣ ግን ወንጌልን ለመስበክ ፍላጎት የላቸውም ብዙ ወንጌላውያንም ድንበር አቋርጠው ወደ ሌላ ክልል በመሄድ የእግዚአብሔርን ቃል ለማብሰር የማይፈልጉ ናቸው።

አቶ ሶርሳ ሱማሞ ግን ሰባኪም፣ ወንጌላዊም፣ እርሳቸው ትውልድ ቦታቸውን ትተው የሌላውን ጉሳ ድንበር ተሻግረው በማያውቁት አካባቢ ወንጌልን ሰብከዋል። የእርሳቸው ዋነኛው ፍላጎት መልካሙን ዜና ማብሰር ነውና በዚሁ ምክንያት እውነተኛ ወንጌላዊ ናቸው።

## ሥረ መሠረቱ (Background)

ታሪኩ የተዘገበው አቶ ሶርሳ ሱማሞ ታላቅ ልጃቸውን ጳውሎስንና ቤተሰቡን ለመጎብኘት ካናዳ መጥተው በነበረ ጊዜ ከመጋቢት 1993-ጥቅምት 1994 ድረስ ነው። አቶ ሶርሳና እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘ ነው በአለታ ወንዶ በ1950 ዓ.ም ነው። በጊዜው አቶ ሶርሳ በአለታ ወንዶ ኤስ አይ ኤም የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ተማሪ የነበሩ ሲሆን፣ አለታ ወንዶ ከደብረ ብርሃን የቋንቋ ት/ቤት ቆይታዬ በኋላ ለመጀመሪያ የተመደብኩበት ቦታ ነበር። ካለፉት 45 ዓመታት ወዲህ ከአቶ ሶርሳ ጋር ግንኙነታችን አልተቋረጠም።

ከሁሉም በላይ ለእኔ አስፈላጊው ነጥብ የልብ ምታቸውን መካፈል መቻሌ ነው። ወንጌላውያን ለመንፈሳዊ ሥራ አስፈላጊዎች ቢሆኑም የተረሱ የክርስቶስ አካሎች ናቸው።

ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የጠፉና ሙሉ በሙሉ የማይታዩ ናቸው።

እነዚህ ወንጌላውያን ቤተክርስቲያንን ከላይ ሆነው የሚንከባከቡና ሁል ጊዜ የነበሩ ናቸው:: ጳውሎስም ያ ልምድ ነበረው::ወንጌላውያን አስተምረው በሜዳ በትነው አይሄዱም፣ ዳሩ ግን መንጋውን እየተንከባከቡ ያሳድጋሉ::

«ለዓለም ለመላዕክትም ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናልና፤ እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች እንዳደረገን ይመስለኛልና:: እኛ ስለ ክርስቶስ ሞኞች ነን እናንተ ግን በክርስቶስ ልባሞች ናችሁ፤ እኛ ደካሞች ነን፣ እናንተ ግን ኃይለኞች ናችሁ፤ እናንተ የከበራችሁ ናችሁ እኛ ግን የተዋረድን ነን:: እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፣ እንጠማለን፣ እንራቆታለን፣ እንጐሰማለን፣ እንንከራተታለን፣ በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን፤ ሲሰድቡን እንመርቃለን፣ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፣ ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን፣ እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል::» (1ቆሮ. 4:9-13)

የወንጌላዊ ሚና ከሌሎች በአንድ ማህበር ተወስነው ከሚያገለግሉ አገልጋዮች በጣም የተለየ ነው:: ምናልባት ትልቁ ልዩነት እርሱ ወይም እርሷ በአንድ ቦታ ተወስኖ ካለው ማህበር ይልቅ የሚያስንቅ ራዕይ ስላላቸው ይሆናል /በተለይም ቻይና ብዙ ሴት የተላኩ ወንጌላውያንን በማፍራት ተባርካለች/::

## ስብከት (Preaching)

በሲዳማ ከአቶ ሶርሳ ተወዳጅ ቃሎች አንዱ በሲዳሚኛ ቋንቋ «ማጪሼ፣ ማጪሼ» የሚል ሲሆን ይህም ማለት ስሙ፣ ስሙ፣ ማለት ነው::

እርሳቸው ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ለመስማት ለሚፈልጉ ሁሉ እንዲያስተላልፉት የተሰጣቸውን ቃል ለማሰማት ስሙ በማለት ይጋብዛሉ:: እናም ከመጽሐፍ ቅዱስ የሆነውን ጭብጥ መልዕክት ለማሰብ ኑ ይላሉ!!

በታሪካቸው ውስጥ ለአቶ ሶርሳ መንፈስ ቅዱስ የሙሉነትና የታማኝነት ስሜት አጐናጽፏቸዋል:: ወንጌልን በመስበክ ቤተ ክርስቲያንን ማፍራት እንደሚቻል ያለምንም ጥርጣሬ ያምናሉ:: የእርሳቸው ጠቅላላ ታሪክ የሚዘዋወረው በስብከት ዙሪያ ነው:: ይህም ማለት በሐዋርያት ዘመን እንደነበረው አገልግሎት ማለት ነው::

የተቃውሞው ጭብጥ ሃሳብ በምዕራፍ አሥራ ሁለት ይገለጻል:: ስለተቃውሞው የሁልጊዜው ታሪክ የአገልግሎትን አቀራረብ



የሚያጣምም ይሆናል:: እኚህ ሰው በአገልግሎታቸው ዘመን ሁሉ ተቃውሞ ነበረባቸው:: ነገር ግን ተቃውሞው ሥራቸውን የሚያስተጓጉል አልነበረም:: የጠላት የተቃውሞ መላ ብዙ ዕውቅና አላለባቸውም ነበር፤ዘወትር ዋናው ትኩረታቸው በዚህ እርሳቸው በተመሩት የአገልግሎት ልምድ ውስጥ እግዚአብሔር ምን አከናወነላቸው?

## ቤተ ክርስቲያንን መትከል

በአቶ ሶርሳ ሉማሞ ታሪክ ውስጥ የተላከ ወንጌላዊ የቤተክርስቲያን ተካይ አይደለም:: ወንጌላዊ ፣ አዋጅ ነጋሪና የመልካም ዜና አብሳሪ ማለት ነው::

አቶ ሶርሳ የሚያምኑት በመስበክ ነው:: መልካሙ ዜና በአጥንታቸው ውስጥ ስለሚነድ ዝም ማለት አይችሉም:: በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚለው በመለኮታዊው ፍቅር ስለተጠመዱ ለመስበክ ይገደዳሉ፣ ሌላ ምርጫ የላቸውም::

አቶ ሶርሳ ታማኝ ወንጌላዊ እንደመሆናቸው ቤተክርስቲያን ተመሥርቶ ቢያዩ በጥልቅ ይደሰታሉ:: የእርሳቸው አገልግሎት ባህርይ ሲታይ ግን ቤተ ክርስቲያንን የሚተክሉት ምንጊዜም አዳዲስ አማኞች ናቸው እንጂ ወንጌላዊ አይደለም::

አዳዲስ አማኞች ባሉበት አካባቢ ሆነው ቤተክርስቲያንን ለመመሥረት መትጋት ይጠበቅባቸዋል:: ወንጌላዊው ግን ከቦታ ወደ ቦታ እየተንቀሳቀሰ ስብከቱን መቀጠል አለበት ብለው ያምናሉ:: ይህ ዘዴ ወንጌላዊው በአንድ ቦታ እያገለገለ አማኞች ተሰባስበው አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ባልተዘጋጁበት ቦታ ወራትና ዓመታት እንዳይፈጅ ይረዳዋል::

በመጀመሪያው ትውልድ፣ በሲዳማ፣ ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያንን የመመሥረት እንቅስቃሴና ተሳትፎ ለአዳዲስ አማኞችና ሰባኪዎች እንግዳ የሆነ ሃሳብ ነበር::

የቤተ ክርስቲያን ሚናዎች ሁለት ሲሆኑ ይኸውም ወንጌልን መስበክና አዳዲስ አማኞችን መገንባት ነው:: አዳዲስ አማኞች በእግራቸው ከ30 እስከ 45 ደቂቃ የሚፈጅ ርቀት እየሄዱ የሚያመልኩ ከሆነ ባሉበት አካባቢ /በቅርባቸው/ ተሰባስበው አዲስ ቤተክርስቲያን እንዲመሠርቱ ይበረታታሉ:: ወንጌላዊው መልካሙን ዜና ይሰብካል፣ አዳዲስ አማኞች ግን አዲስ ቤተክርስቲያን ይመሠርታሉ፣

የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችም ከላይ ሆነው አዳዲስ ምዕመናንን ይመራሉ ያሳድጋሉም::

በእኛ ዕውቀት ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከተማ በተከታታይ ከቤተክርስቲያን ጋር እንደነበረው ህብረት በሰሜናዊ ሲዳማ የነበረው የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ከ20ኛውና ከ21ኛው ምዕተ ዓመት የበለጠ ለውጥ አሳይቷል::

በሲዳማ የወንጌል ሥርጭት ስኬታማ ሊሆን የቻለው በዚሁ ምክንያት ሊሆን ይችላል::



# *ማብራሪያ*

አቶ ሶርሳ የሚሉትን ለመረዳት የጥቂት ቃላትን ትርጉም ማብራራት እንፈልጋለን::

የመጀመሪያው ቃል «ማመን» የሚለው ነው:: በአቶ ሶርሳ ዘገባ ማመን ማለት አቅጣጫን መለወጥ፣ ከጨለማ መንግሥት ወደ ብርሃን መንግሥት፣ ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገር ማለት ነው :: ለማመን የሚጋበዙ ብዙ ሰዎች የሚያቀርቡት ጥያቄ አይኖርም፤ አቅጣጫቸውን መለወጥ ይፈልጋሉ፣ እናም ያምናሉ:: አስቀድሞ የነበሩበት ሕይወት ስላላረካቸው መንገዳቸውን ለመለወጥ ፈለጉ ወዲያውም ቃሉን ሰምተው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ይለወጣሉ፣ በአዲስ ሕይወትም ይመላለሳሉ::

ሁለተኛው «የሰይጣን አምልኮ» ነው:: እስቲ የሰይጣንን አምልኮ በስፋት ያስቡት (ማቴ. 7÷14):: ሰዎች በዚህ ላይ ምን እንደሚያስቡ ግልጽ የሆነ ሀሳብ ይኑርዎት::

አንድ የማናደርገው ነገር ቢኖር የጠፉትና ሰይጣንን የሚያመልኩት ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩ እየመሰላቸው ነው ነገር ግን ወደ እውነት የሚያመጣቸው አምልኮ አይደለም::

የባሕል ሃይማኖት ማለት ምን ማለት ነው? የባሕል ሃይማኖት ማለት አንድ ሰው ከቤተሰቡ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ባህላዊ እምነት ማካሄድና ቀድሞ በኖረበት አስተሳሰብ መቀጠል ማለት ነው::

ሲዳማ፣ አቶ ሶርሳ የሠሩበት በቀድሞ አጠራር የሲዳሞ ክፍለ ሀገር ይባላል:: በአሁኑ አጠራር የሲዳማ ዞን ይባላል:: በሲዳማ ዞን የሚኖሩ ጐሳዎች የሲዳማ ሕዝቦች ናቸው:: ቋንቋቸውም ሲዳሚኛ ይባላል::ከሲዳማ ጐሳዎች ውጪ በዞኑ ውስጥ በርካታ ብሔሮችም ይገኛሉ::

የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያው ኤስ አይ ኤም ጋር የተቀናጀ ብሔራዊ የሃይማኖታዊ ህብረት አለው:: የቃለ ሕይወት ሃይማኖት ክፍል ከኤስ አይ ኤም ጋር ድርጅታዊ የሆነ የጋራ ሥራ አሁን የላቸውም፣ ነገር ግን በየግላቸው የጋራ ግብ ያለውን ተግባር ያከናውናሉ::

# መቅድም

በዚህ ታሪክ ውስጥ የተዘረዘሩት ፍሬ ሃሳቦች ፍፁምና ስህተት የሌለባቸው ናቸው ወይ?

እንደዚህ ዓይነት መጽሐፍ፣ለመጻፍ የታቀደው የመጀመሪያው እንዲሆንና የሃሳብ ክፍተት እንዳይኖረው ለመጠንቀቅ ነው። ስለዚህ ታሪኩን እንዳለ ለመፃፍና እውነታውን ሳይለቅ የጐደለውን በመሙላት የሚጽፍ ቢኖር ፈቃደኛ መሆኔን እገልጻለሁ።

ይህን ታሪክ በምዘግብበት ጊዜ አቶ ሶርሳ ሱማሞ የ76 ዓመት ሽማግሌ መሆናቸውን በአዕምሮዎ ይያዙት። በዚህ ዕድሜ ከወደኋላቸው የነበረውን ሁሉንም ነገር በደንብ ማስታወስ ይችላሉ ብሎ ማሰብ ተገቢ አይመስለኝም። አብረው የሠሩአቸውን ሰዎችና የገንዘብን ጉዳይ ሁሉቱንም ነገሮች መልሶ ለማስታወስ ያዳግታቸዋል።

አቶ ሶርሳ የሚፈልጉትን ተግባር ለማከናወን የራሳቸው ራዕይና የራሳቸው መንገድ አላቸው። ስለዚህም ሌሎች ስለሚሠሩት ሥራ ምንም አይጨንቃቸውም። ሌሎች ሰዎች ስለሚያከናውኑት ሥራ ዝም ማለታቸው የእነርሱን የአገልግሎት ክንውኖቻቸውን ማጥላላታቸው አይደለም። በማንኛውም ጊዜ ምንም ደመወዝ በአበል መልክ መቀበል ፍላጐታቸውና ልማዳቸው አይደለም።

የማስታወስ ችሎታቸው ማነስ በገንዘብ አካባቢ የነበረውን ሥዕል የተዛባ አድርጐታል። ዋናው አስፈላጊ ነገር ከቁም ነገር እይታ እንዳያጡ ልመናዬ ነው።

እግዚአብሔር በሰሜናዊ ሲዳማ የተለየ ሥራ ይሠሩ ዘንድ ትሁት ሰው መርጧል፣ ለጌታ ምሥጋና ይድረሰው!!

የመጨረሻውን ውጤት በጥረት ለማሳመር የረዱንን የተወሰኑ ሰዎችን ለማመስገን እወዳለሁ። ከሚስተር ባሊስኪ የጥናት ምርምር ከፍተኛ አስተዋይነትና እርዳታ ተቀብያለሁ። የወላይታ ወንጌላውያን የሃይማኖት ፈጠራ ጥናት በደቡብ ኢትዮጵያ ከ1929-1987 ለፓውልና ላይላ ባሊስኪ ለመጽሐፍ መግቢያ የሚሆኑልኝን ነጥቦች ላበረከቱልኝ አስተዋጽኦ ትልቅ ምሥጋና አቀርባለሁ። በተጨማሪም መጽሐፉን አንብበው በመተቸትና አስተያየት በመስጠት በዚሁ ሁኔታ እንዲዘጋጅ ረድተውኛል።



የደልማርና ሜሪ እስቲቬንስ ዘገባ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ የተጨመረበት ምክንያት መታወስ ያለበት ስለሆነ ነው። እናም ታሪኩ እንደተላከልኝ በዚህ መጽሐፍ እንዲታይ አድርጌአለሁ።

የተወሰኑ ሰዎች መጽሐፉ ሳይታተም አስቀድመው በማንበብ አንዳንድ ስህተቶችን አርመዋል። በተለይም ኤልሳቤጥ የአቶ ሶርሳ የልጅ ልጅ ምንባቡን በማንበቧ ልዩ ምሥጋናዬ ይድረሳት። ልጃቸው ጳውሎስ ሶርሳ ደግሞ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርጐልኛል።

ጸሐፊን ደጋግመው በማንበብ ባህላዊ ጥርስ ያለው ሚዶ በማድረግ የቃላትና የሰዋሰው ዝብርቅርቅ ሀሳብ ስላስወገዱልኝ ለባለቤቴ ለዶሪስ ልዩ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

ይህንን መጽሐፍ ስጽፈው እኔን እንዳነቃቃኝ እናንተንም እንዲያበረታታችሁ ፀሎቴ ነው።

ብራዪን ኤል ፋርገር

እድመንተን አልበርታ

ህዳር 1993

# ክፍል አንድ

## ራዕይ

በሚቀጥሉት አምስት ምዕራፎች ውስጥ የምገልጽላችሁ ታሪኬ ከ50 ዓመት በፊት ጌታ ከሰጠኝ ራዕይ ጋር የተያያዘ ይሆናል፡፡

ጌታ አንዳንድ ነገሮችን እንዳደርግ እንደፈለገኝ በተሰማኝ ጊዜ በውስጤ የነበረው ፍላጐቴ ራዕይ ስለመሆኑ ምንም ሃሳብ አልነበረኝም፡፡ ራዕይ የሚባለውንም ቃል በፍፁም ሰምቼ አላውቅም ነበር፡፡ ስለ ሕይወት ጉዳይ ሲነሳም አንድም ሰው ስለ ራዕይ ተናግሮ አያውቅም፡፡ በጊዜው በአካባቢያችን ራዕይ የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ ሕልም እንደማለት አድርገው ይወስዱታል፡፡

ለእኔ ግን ራዕይ ኃላፊነት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበሩት ነቢያቶች «የእግዚአብሔር ቃል» ያሉት ነበር፡፡

«ወደ ሶፎንያስ የመጣ የእግዚአብሔር ቃል» (ሶፎንያስ 1÷1)

ለሕይወቴ ይህንን ኃላፊነት እቀበል ዘንድ እግዚአብሔር መርጦኛል፡፡ ስለዚህ እርሱን በደስታ ተቀበልኩ፡፡ ይህንንም የተሰጠኝን ራዕይ እንኳን ደህና መጣህ ብዬ ተቀበልኩት፡፡ ጌታ የሰጠኝ ራዕይም ገና ምንም ወንጌልን ላልሰሙት ሕዝቦች ወንጌልን እንድሰብክ ነበር፡፡ እኔን በሚመለከት ተልዕኮዬ በሰሜናዊው ሲዳማ ልዩ ስሙ ያናሴ በሚባለው አካባቢ ወንጌልን በማሠራጨት እንዳገለግል ነው፡፡

ከጳውሎስ ጋር እኔም እንዲህ እላለሁ፡-

«እንዲሁም በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ሥፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ» (ሮሜ 15÷20

ምናልባት የራዕዩ የተሻለ ሙሉ መግለጫ የመጣው በካናዳ በነበረኝ አስቸጋሪ ልምምድ ውስጥ ነው፡፡

በሕይወቴ ካሳለፍኳቸው ጊዜያቶች ውስጥ በካናዳ የቆየሁባቸው ወራቶች ለእኔ በጣም የጨለሙና እጅግ አስቸጋሪ ነበሩ፡፡ ዋናው ምክንያት እዚያ በነበርኩ ጊዜ ወንጌልን መስበክ አለመቻሌ ነበር፡፡ ልክ ነቢዩ ኤርምያስ እንደሚነድ እሳት ያለ በልቤ ሆነብኝ እንዳለው ዓይነት ነገር በውስጤ እንደደረሰብኝ ተሰምቶኝ ነበር፡፡ «እኔም የእግዚአብሔርን ስም አላነሳም፣ ከእንግዲህ ወዲህ በስሙ አልናገርም ብል በአጥንቶቼ ውስጥ እንደገባ እንደሚነድድ እሳት ያለ በልቤ ሆነብኝ ደከምሁ፣ መሸከምም አልቻልኩም» (ኤርምያስ 20÷9)፡፡

በልቤ ውስጥ ያለውን እውጥቼ ለመናገር በተሳነኝ ጊዜ ተመሳሳይ እሳት ልቤን አቃጥሎታል:: ራሴንና ሌሎቹንም ጐድቷል፣ ልክ በብረት አጥር ውስጥ እንዳለ አንበሳ እንደሆንኩ ነበር የተሰማኝ::

በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በአንድ ነገር ብቻ ሙሉ ፍላጐት አለኝ ይኸውም በኃጢያት እና በፍርድ ውስጥ ላሉት ወንጌልን መስበክ ነው:: ሰዎች ወንጌልን ሲሰሙ የዘላለምን ሕይወት ያገኛሉ፣ ስለ ሥጋዊ ምቾት ቃል አልገባላቸውም::

ወደ ካናዳ በሄድኩኝ ጊዜ ተመሳሳይ አገልግሎት ይኖረኛል የሚል ግምት ነበረኝ፣ ነገር ግን የማይቻለኝ ሆኖ አገኘሁ:: በድንገት ራዕዬ የተወሰደብኝ መስሎ ተሰማኝ፣ ሁሉም ነገር ተደነጋገረብኝ፣ ግራ ተጋባሁ:: ላልተሰወጡት ካናዳውያን አለመስበክ የማልደግፈው ነገር ሆኖ ታየኝ::

## አዲስ አጋጣሚ

ታላቁ ልጄ ጳውሎስና ባለቤቱ አምሳለ እኔንና ባለቤቴን ወንድምየውን አማኑኤልንና እህቱን ታደለችን ወደ ካናዳ እንድንመጣ ጋበዙን:: ልጄ ጳውሎስና ቤተሰቡ በካናዳ ከ20 ዓመት በላይ የኖሩ ናቸው::

ግብዣውን በተቀበልኩኝ ጊዜ ስለ ካናዳ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረኝም:: በድንገት የመስበክ ነፃነቴን አጣለሁ የሚል ግምትም ፈጽሞ አላደረብኝም ነበር:: በካናዳ የ20 ዓመት ቆይታ ልጄንና ቤተሰቡን የዚያ አገር ሕዝብ ባሕል ይለውጣቸዋል ብዬም አልጠበቅኩም፤ በመጨረሻም ሕዝቡንና ባህሉን ልረዳ አለመቻሌን አስተዋልኩ::

ወደ ካናዳ ለመምጣት ባቀድኩ ጊዜ ምናልባት እግዚአብሔር ለአገልግሎቴ አዲስ በር እየከፈተልኝ ነው የሚል ግምት ነበረኝ:: ምናልባት በሰሜናዊው ሲዳማ እንዳደረገው በካናዳም ሊጠቀምብኝ ይሆናል ብዬ እጠብቅ ነበር::

## መናገር እንደማልችል፣ መስማት እንደማልችል መንቀሳቀስ እንደማልችል

በአጠገቤ ያሉት ሰዎች የሚናገሩትን ለመስማት እንደማልችል ወዲያው ተረዳሁ:: የአገሩ ሰዎች በአስተርጓሚ ተናግረው አያውቁም፣ እናም የገዛ ልጆቼ እንኳን ሊተረጉሙልኝ አልፈለጉም::

የመገለልና የብቸኝነት ስሜት ተሰማኝ:: ሽማግሌ እንደመሆኔ እንግሊዝኛ ተምሬ በደንብ ለመናገርና ለመስበክ እንደማልችልም አውቄአለሁ:: ወዲያውኑም እንደ ዲዳ ሰው ሆንኩኝ:: ወንጌልን ለመስማት የሚፈልጉትን ሰዎች ተገናኝቻቸው ነበር:: ለእነርሱ ወንጌልን ለመስበክ የተቃጠለ የፍቅር ስሜት አለኝ፣ ዳሩ ግን አንድ ነገር እንኳን መናገር አልቻልኩም::



በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ በነፃነት ከቦታ ወደ ቦታ እየተንቀሳቀስኩ የመስበክ ነፃነት ማጣቴ ተሰማኝ:: ምክንያቱም ከሰዎች ጋርም ለመነጋገር አልቻልኩም ነበር:: ቤተሰቤም በአውቶቢስ እንድዘዋወር አልፈለጉም፣ ቤተሰቤና ወዳጆቼ ሁሉ በየሥራቸው ስለሚውሉ እያዞረ የሚያስጐበኘኝ አልነበረምና ራሴን እንደ እሥረኛ ቆጠርኩት::

አንዳንድ ጊዜ ለራሴ «ይህስ ከእሥር ቤት የከፋ ቦታ ነው» እላለሁ፣ ምክንያቱም በእስር ቤት መስበክ እችል ነበር::

የካናዳውያን ባሕል ለእኔ በጠቅላላው እንግዳ ነበር:: ምንም ስሜት በማይሰጠኝ ዓለም ውስጥ ሆኜ በድንገት በጧቱ ከእንቅልፌ እነቃለሁ:: ሁሉም ለእኔ መጥፎ ነገር ይመስለኝ ነበር:: በማንኛውም አቅጣጫ ስመለከተው በሰይጣን እየተጠቃሁ ያለሁ ስለሚመስለኝና፣ በተለይም እሁድ ለእኔ ከሁሉም የተሻለ ቀን ከመሆን ይልቅ የከፋ ቀን ይሆንብኝ ስለነበር ነው:: መስበክ እፈልጋለሁ ግን አልቻልኩም፣ በአገልግሎት መሳተፍ እፈልጋለሁ ግን አልቻልኩም:: ለአገልግሎት ያለኝን ጥልቅ ፍቅር መግለጽ እፈልጋለሁ፣ ዳሩ ግን ሊሰማኝ የሚፈልግ የለም:: ልሰጥ እፈልጋለሁ፣ ዳሩ ግን ገንዘብ አልነበረኝም:: አንዳንዴ በአማርኛ ብሰብክስ ብዬ አስብና የማህበሩን ቋንቋ አለማወቅና ባህላቸውን ስረዳ ሁሉ ነገር ልዩና የተሳሳተ ይሆንብኛል:: ምናልባት ተስፋ የሚያስቆርጠኝ በተከፈለ ሕይወት ውስጥ መኖሬ ነበር ብዬ አስብኩ:: አካሌ በኤድመንተን ካናዳ ሆኖ ልቤ ግን በለኩ ነበር:: ስለዚህም ነው ታሪኬን በምዕራፍ አንድ ላይ በለኩ ከተማ ምን እየተደረገ ነው? በሚል የጀመርኩት::

ዕድሜዬ ከሰባ ዓመት በላይ ቢሆንም በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ ላሉት ወንጌልን ለመስበክ ያለኝ ምኞት በሃያዎቹ ዕድሜዬ እንደነበርኩ ሆኖ ይሰማኛል::

## ምዕራፍ አንድ

## ለኩ

### የልብ መነሳሳት /የጋለ ስሜት/

በ1993 ዓ.ም ኤድመንተን ካናዳን በጐበኘሁ ጊዜ አዕምሮዬ ሳያቋርጥ ስለለኩ ያብሰለስል ነበር:: እናም ሃላፊነት የሚሰማኝ በለኩ ከተማ ዳር ለሚገኘው ሁለተኛው አዲስ ማህበር ነበር:: እዚያ የሚገኙት አዳዲስ ምዕመናን አዲስ ሀሉን ቤት ለመሥራት በሂደት ውስጥ ነበሩ::

እነርሱ ለሚሠሩት የቤተክርስቲያን ሥራ እኔ በአካልና በስሜቴ በጣም ተሳትፌበታለሁ:: ሳላቋርጥም እፀልይላቸዋለሁ:: ስለነርሱ፣ በሰፊው ልሰማ ብፈልግም የምሰማው ግን በጣም አነስተኛውን ነገር ነው::

ወደ ካናዳ ስመጣ ከሕልሞቼ አንዱ የፀሎት ቤታችንን መሥሪያ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት መሞከር ቢሆንም ለማግኘት ባለመቻሌ ተስፋ ቆርጬአለሁ::

## ታሪክ

በ1942 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ያናሴ ሄድኩኝ:: ያኔ ለኩ በሰሜናዊ ሲዳማ የምትገኝ የሸበዲኖ ወረዳ ከተማ ማዕከል ነበረች::

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የምንኖር ብዙዎቻችን የከተማውን ኑሮ አንችልም:: ከተማውን ችግር የበዛበት አድርገን ስለምንቆጥረው፣ እንደ አብዛኛው የገጠር ሕዝብ በተቻለን መጠን ከከተማው ራቅ ብለን ሰፈርን:: ምክንያቱም እርሻ ለማረስና ከብት ለማርባት የገጠሩ አካባቢ አመቺ ከመሆኑም በላይ ለወንጌል ተልዕኮዬም ለገጠሩ ህዝብ መሰበክ የበለጠ ስለሚቀናኝ በገጠር መኖርን መረጥኩ::

ለኩ ለሰሜናዊው ሲዳማ አነስተኛ ከተማ የነበረች ብትሆንም አንዳንድ የመንግሥት መ/ቤቶችም ነበሩባት:: እነዚያ የመንግሥት መ/ቤቶች ሁለት ተግባሮችን ያከናውናሉ፣ ይኸውም ግብር መጣልና ሙግት ናቸው:: ሁለቱም መራራ ተግባሮች ብዙ ስላስተማሩን በሚቻለን ሁሉ ከአካባቢው እንድንርቅ አድርጉናል::

በአካባቢው ትልቁ ገበያ በለኩ የነበረው ሲሆን ገበያውና የመንግሥት አስተዳደር ሁለቱም የተለያዩ ናቸው:: ገበያው የእኛ ነው:: የከተማውም ነዋሪዎች ይገበያዩበታል:: የአስተዳደሩ ቢሮዎችም የራሳቸው ናቸው:: እኛም በሚቻለን ሁሉ ልናርቃቸው እንሞክራለን:: በዘመኑ ከፍተኛ ት/ቤቶች የሚገኙት በከተማዎች ውስጥ ነበር:: በ1942 ዓ.ም አካባቢ ከገጠር በጣም ጥቂት የሆኑ ተማሪዎች ብቻ ወደ ከተማ ሄደው የመማር ፍላጎት ነበራቸው::

የለኩ ከተማ ለሁሉም አመቺ ሥፍራ ቢሆንም ለቤተክርስቲያን ግን አመቺ አልነበረም:: በጊዜው ከነበረው ከአማራው የገዢ መደብ ጭቆናና ከሚደርስብን ዝቅተኝነት የተነሳ ከተማውን ሁሉ በተለየና በጥላቻ መልክ እንድናይ አድርጉን ነበር::

## የከተማው ዙሪያ

ከ1966-1983 አብዮታዊ ለውጥ ድረስ በከተማ የሚኖሩ ሕዝቦች በገጠር ከምንኖረው ሕዝቦች በተለየ ማህበራዊ ምድብ ያሉ ይመስላቸው ነበር:: ለስሜታቸው ዋናው ምክንያት በከተማ የሚኖሩት አሥር ዓመት ከእኛ



ቀድመው እንደሄዱና በገጠር የምንኖረውን ሕዝብ አሥር ዓመት ወደኋላ የቀረን አድርገው ስለሚገምቱ ነው:: በእርግጥ የከተማው ነዋሪዎች ንቃተ ሕሊና ከእኛ ከገጠር ነዋሪዎች ሊበልጥ ይችላል:: ነገር ግን ጊዜው ተለውጦ የተማሩ የገጠር ሰዎች ከከተማዎቹ እኩል ሆነዋል::

ለዚህ ዓይነት የሃሳብ ርቀት ቋንቋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ዋነኛው ምክንያት ነበር:: በከተማው አካባቢ አማርኛ የሚመረጥ ቋንቋ ነበር:: በብዙ ቦታዎች የከተማው ነዋሪዎች ለማህበራዊ ሥራና እንቅስቃሴ አማርኛን መምረጣቸው የሲዳማን ሕዝብ ማስቸገሩ አልቀረም:: ዛሬ እንኳን የወጣቱ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ችግር አይታይበትም::

አንድ ሰው የምጣኔ ሀብትና የገንዘብ ልውውጥ ከፈለገ በጊዜው የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ያስፈልገዋል:: ከቤተሰብ ትስስር የተነሳ ጥቂት ሰዎች ብቻ በዚያ ማህበራዊ እንቅስቃሴ መንገድ ለማለፍ ችለዋል::

የሕዝቡ የምጣኔ ሀብት ደግሞ የከተማውን ሕዝብ እንዲለይ አድርጉታል:: በከተማዎች ምጣኔ ሀብት ተሰራጭቷል:: ሰዎች ይሠራሉ ጥሬ ገንዘብ ይከፈላቸዋል፣ አንዱ ለሌላው ከሠራ ገንዘብ ወይም የሚፈልገው ነገር ይከፈለዋል:: በገጠር ግን በህብረትና በደቦ አንዳችን ለሌላው በመሥራት እንተጋገዛለን እንጂ ከፍለን አናሠራም፣ ተከፍሎንም አንሠራም:: በሁሉም አቅጣጫ በገጠር የምንኖር ከከተማ ነዋሪዎች በብዙ ነገሮች እንለያለን:: የእኛ የገቢ ምንጭ ከእርሻችን የምናገኘው ምርት ሲሆን፣ የከተማ ነዋሪዎች በንግድና በወር ደሞዝ ይተዳደራሉ::

## የግል ምርጫ

የእኔ የአገልግሎት መስክ ገጠር ነበር:: በአፋራራ ስኖር ከይርጋለም እና አዋሣ ከተሞች ብዙ አልርቅም፣ ነገር ግን ቃሉን ለመስበክ ወደነዚያ ከተሞች የመሄድ ፍላጎት አልነበረኝም:: እግዚአብሔር የጠራኝ በከተማ ሳይሆን በገጠር እንድሰብክ ስለነበረ ነው::

በእርግጥ በከተማ ብሰብክ ፍርሃት የለኝም፣ በትረካዬ ከወደኋላ ትደርሱበታላችሁ፣ አንዳንድ ምዕመናን ታስረው በነበሩ ጊዜ ልንጠይቃቸው ስንሄድ በእሥር ቤትና በአካባቢው ላሉት ሁሉ በሰፋት እሰብክ ነበር:: የቋንቋ እጥረትና የገንዘብ ማጣት ወደ ከተማው እንዳልገባ ቢያደርገኝም፣ የቃሉ እውነት በውስጤ የጋለ ስለነበረ በድፍረት እሰብክ ነበር::

በአገልግሎቴ ውስጥ እግዚአብሔር ከሚመራቸው መንገዶች አንዱ ጥሪ ነበር:: በከተማ ሄጄ እንድሰብክ ማንም ጋብዞኝ አያውቅም፣ ምናልባት ሌሎች አገልጋዮች ተጋብዘው ይሆናል:: ነገር ግን ለእኔ ጥሪ የሚደርሰኝ ከገጠር ሰዎች ወደ አካባቢያቸው ሄጄ እንድሰብክ ነው:: በእርግጥ እንደ ገጠር በነፃነት

ወንጌልን ለመስበክ ከተማው የሚመቸኝ አልነበረም። አብዛኛዎቹ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ስለነበሩ ልባቸውን አይከፍቱልንም ነበር።

በሕይወቴ ዘመን በሚቀጥለው ጊዜ ምን እሠራለሁ? ብዬ ተጨንቄ አላውቅም፡- በገጠሩ አካባቢ ብዙ የምሠራው ሥራ ነበረኝ። ስለዚህም በከተማው ውስጥ ሄጄ ለመስበክ አስቤም አላውቅም።

በማንኛውም የገጠሩ አካባቢ ሄጄ ብሰብክ ሰዎች ይሰማሉ። ወዲያውኑ ባያምኑና ቢያፈገፍጉ እኔ አልጨነቅም። ከግብርና ሙያዬ የተዘራው ዘር ጊዜውን ጠብቆ እንደሚበቅል አውቃለሁ። በከተማውም ተመሳሳይ እንደሚሆን ባልጠራጠርም የእኔ ጥሪ ግን ለከተማው እንዳልሆነ አስባለሁ።

ከአብዮታዊው ለውጥ በፊት በከተማ መስበክ አነስተኛ ግምት የሚሰጠውና አልፎ አልፎም ትንኮሳ የሚታይበት ነበር። ሙስሊሞች የራሳቸውንና የእኛን መልዕክት ለይተው ስለሚያውቁ ችግር አላስከተሉብንም። ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ግን እንዲህ አልነበረም። እኛ የምንሰብከውን እውነት በቅንነት ባለመተርጐም የእነርሱን ሃይማኖት እንደተጋፋን በመቁጠር ካህናቱና ዲያቆናቱ የአማርኛን መጽሐፍ ቅዱስ በመጠቀማችን በወቅቱ ሳያቋርጡ ጠብ ይጭሩብን ነበር።

## የከተማው ነዋሪዎች ባህሪ

አስቀድሜ እንዳልኩት የከተማ ነዋሪዎች ከተለያዩ ማህበራዊ ክፍሎች ቢሆኑም፣ ብዙውን ጊዜ የገጠር ነዋሪዎችን ይንቁ ነበር። ይህም የሆነው እነርሱ ከገጠር ነዋሪዎች የበለጠ ዘመናዊ አኗኗር ስላላቸው ነው። የገጠር ነዋሪዎች ሁሉም አሥር ዓመት ያህል ወደኋላ መቅረታቸውና ማንኛውንም ለውጥ ለመቀዘል ዳተኞች መሆናቸው እውነት ነው። ለገጠር ነዋሪዎች ዋናው መሻሻልና ዕድገት በገጠር አካባቢ የቆርቆሮ ክዳን ቤት ለመሥራት መቻላቸው አንዱ ነው። የቆርቆሮ ክዳን ቤት ከሲዳማዎች የባህል ቤት የበለጠ የማይመች ቢሆንም፣ ከህብረተሰቡ መሻሻል ጋር የተቀናጀ በመሆኑ የተሳካ ሆኖላቸዋል።

አብዛኛውን ጊዜ በከተማ የሚኖሩ ሕዝቦች በዘመኑ የራሳቸውን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ወይም አባላት ያደርጋሉ። ምክንያቱም ኦርቶዶክስን በመላው አገር የበላይ አድርገው ይቆጥሩ ስለነበር ነበር። የከተማ ሰዎችም እኛን አማኞችን «ሚሽን» ብለው ይጠሩናል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ከውጪ አገር ለመጡ ሚስዮናውያን እንደተሸጥን አድርገው ያገምቱናል።

የከተማ ነዋሪዎች ክርስቲያን ያልሆኑትን የሲዳማ ሕዝቦች ምንም ሃይማኖት እንደሌላቸው አድርገው ይገምቱ ነበር። በባሕላዊ አስተሳሰባቸው



የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሁለት ሃይማኖትን ማለትም የክርስቲያንን ሃይማኖትንና የእስልምና ሃይማኖትን ብቻ ያውቁ ነበር።

አንድ ሰው በእምነታቸው ሥር ካልተጠመቀ ወይም እስላም ካልሆነ «ሃይማኖት የለሽ» ይሉታል። ሃይማኖት የለሽ ሲባል ኢ-ሰብአዊ እንደመሆን ይገመታል። እኛ ግን ሃይማኖታዊያን ብቻ ሳንሆን እግዚአብሔርን በየግላችን የምናውቅ ጠንካራ ክርስቲያኖች ነን። እግዚአብሔር ይመስገን!።

በዚሁ አስተሳሰብ መካከል ለእኛ ዘልቆ የገባው ብሔራዊ የሃይማኖት ክፍል የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ነበር። ይህ ሁኔታ የከተማው ሕዝብም ለእኛ አስፈላጊ መሆኑን እንድንገነዘብና እንድናቀርባቸው አድርጐናል።

## በኦርቶዶክስ የተከለለ ሰፍራ

ከተማዎች ብዙውን ጊዜ ለኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምቹና ብቸኛ የማምለኪያ ስፍራዎች ናቸው። የእኛም ስሜት በጊዜው እንዲህ ነበር።

የከተማ ቦታዎች በሙሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመለለን ጊዜ ነበር። በተለይም በ1942 አካባቢ በጣም ጥቂት የሆኑ ሲዳማዎች የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ነበሩ። የዚህ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ብዙውን ጊዜ ከሌላ ክፍለ ሀገር የመጡ ናቸው።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ካህናትና ዲያቆናት ለከተማው ብቻ ትኩረት ይሰጡ ነበር። ከተማው የአንድ መልክአ ምድር አካባቢ ሲሆን ለዚያ አካባቢ ብቻ ይታገላሉ። ከ1942 - 1950 አካባቢ ብዙ አማኞች በከተማው ክልል ውስጥ ለመኖር ፍቃደኛ አይሆኑም ነበር።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በዘመኑ በመላው አገሪቱ የተስፋፋ በመሆኑ እስላም ያልሆነ ሰው ሁሉ የእነርሱ እምነት ተከታይ እንዲሆን ይሻሉ። በተለያዩ ጊዜያት ብዛት ያላቸው የሲዳማ ሕዝቦች በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ካህናት ተጠምቀዋል። የተጠመቁት ሰዎች ጠለቅ ብለው የሚያውቁት ነገር ባይኖራቸውም፣ ካህናቶቹ ግን የተለወጡ ናቸው ብለው ይሰብኩ ነበር። የሆነ ሆኖ በእነርሱ የተጠመቁት ሰዎች የመለወጣቸውን ምልክት ማህተብ /ክር/ በአንገታቸው ላይ በማሰር እና ፊታቸውን ወደ ቤተክርስቲያን መልሰው በመሳለም ያረጋግጣሉ።

## የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን መሪዎች ባህርይ

እኛ የሃይማኖት ክፍል እንደመሆናችን ከዓመት እስከ ዓመት ማንኛውንም ግጭት ማስወገድ ዋናው ስልታችን ነበር። በትክክለኛው መንገድ ብንጓዝ እንኳን መብታችን የሚነካበት አጋጣሚዎች ነበሩብን። እኛም በዳኛና በጠበቃ ፊት ባለመቆም ችግሮችን እናስወግዳለን።

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ግን አክራሪዎች ስለነበሩ ከእነርሱ ጋር መጋጨት ስለማንፈልግ ያን ጊዜ ወደ ከተማ ገብተን አንሰብክም:: ወደ መጀመሪያ ግድም የገጠር አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ብዙውን ሕዝብ በቃል ከመድረስ ይልቅ ከተማን ሁሉ የተቃውሞ ማዕከል አድርገው ለማየት ይገደዳሉ:: በገጠር መልካሙን ዜና ሰምተው ለመቀበል የሚችሉ በጣም ብዙ ሕዝቦች እያሉ መልካም አቀባበል ወደማያደርግልን አካባቢ ለመሄድ ለምን እንጨነቃለን? ይባባሉ ነበር:: በእርግጥም ወደ ገጠር ወጥተን ወንጌልን ስንሰብክ ነፍሳትን በቀላሉ ማርከን እንመለሳለን::

አብዮታዊው የመንግሥት ለውጥ ለከተማዎች አዲስ እይታ እንዲያገኙ ረድቷል::ወጣቶችም መካከለኛ ደረጃን ወለዱ ብዙ ወጣቶች ጠንካራ አማኞች ነበሩ የማይቻላቸው ነገርም አልነበረም:: በከተማ ውስጥ በስፋት ለማገልገል ምርጫቸው ነበርና ነገሮች በፍጥነት ተለወጡ::

## አብዮታዊ ለውጥ

ከ1966-1983 ዓ.ም በአብዮታዊ ለውጥ ጊዜ ከተማዎች በፖለቲካ ትኩሳት ይራወጡ ጀመር:: አብዛኛዎቹ የለውጡ ተቃዋሚዎችም በከተማ የሚኖሩ ነበሩ እናም ተከሩፍለውና ተበታትነው የሚሰለጥኑበትም እዚያው ነበር::

አዳዲስ የፖለቲካ መሪዎች አክርረው ሃይማኖትን ባይቃወሙም ማንኛ ውም የመንግሥት ሠራተኛ ሃይማኖትን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረበት::

ይህም ማለት ፖለቲካው ሶሻሊዝምን የሚደግፍ በመሆኑ አብዛኛዎቹ ፖለቲከኞች በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑ ስለነበሩ የክህደትን መንፈስ ያስፋፉ ነበር ማለት ነው::

በጊዜው ሃይማኖትን ለማስፋፋት በቤተክርስቲያንና በመስጊድ ካልሆነ በስተቀር በሌላ ቦታዎች መስበክ አይቻልም:: ሃይማኖተኛ መሆን ይቻላል፣ ነገር ግን ከራስ አልፎ ለሌላው ማስተላለፍ አይፈቀድም ተባለ:: በተለይም የመንግሥት ት/ቤቶች መምህራንና ሰራተኞች ባለስልጣኖችም ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው:: የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች የነበሩ ዛሬ በህይወት የሉም፣ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ግን ይኸው አለን:: እግዚአብሔር ይመስገን::

## ይህ ያለፈ ታሪክ ለምን አስፈለገ?

በሕዝባዊ ንቅናቄ ወይም በለውጥ ጊዜ በከተማ ውስጥ ወንጌልን መስበክ በእኔ ዕድሜ ክልል ላሉት ሰዎች የሚያስመኝ ምርጫ አልነበረም፣ በባህላዊና በፖለቲካዊም መስክ ፈታኝ ነበር::



እግዚአብሔር የጠራኝ ወንጌላዊ ሆኜ ሥራዬን እንድቀጥል ነው:: እናም ወደ ከተማ ገብቼ የደህንነትን ወንጌል መስበክ ነበረብኝ ምክንያቱም አዳዲስ አማኞች ቤተክርስቲያንን ለመመሥረት እንዲችሉ ለማድረግ ነበር:: የወቅቱ ሁኔታ የማይመች ከመሆኑ የተነሳ ይህን ለማድረግ መሞከር አስቸጋሪ ውሳኔ ሆኖብኛል::

በጊዜው የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን መሪዎች የምሠራውን ባይደግፉም አልተደነቅሁም:: ለእነርሱ ትልቅ ለውጥ ቢሆንም በሰዎች አስተሳሰብ ወደ ከተማ ገብቶ ወንጌልን መስበክ ጥሩ መስሎ አይታይም ነበር::

## የሁለተኛው ለኩ ቃለ ሕይወት ማህበር

በለኩ ከተማው ዳር የሚኖሩ ሁለት ሰዎች በቅርቡ ክርስቶስን ተቀብለው ነበር:: ምናልባት ይህ ቦታ ከአንደኛው ለኩ ከተማ በግማሽ ሰዓት በእግር ያስኬዳል:: እነዚያ ሁለት ሰዎች አንድ ቀን ከለኩ ወደ መኖሪያ ቤቴ መጡና በከተማው ውስጥ በእኛ አካባቢ ብዙ ሰዎች አሉ ወደ ቤታችን መጥተው ሊፀልዩ ይችላሉ? ብለው ጠየቁኝ::

በባሕሉ አዲስ ማህበር ሲመሠረት ተሰብስቦ በመፀለይ ይጀመራል:: እሁድና ሐሙስም የመሰብሰቢያ ቀኖቻችን ናቸው:: አዳዲስ አማኞች አዲስ ቤተክርስቲያን ለመትከል ሲያስቡ ሐሙስ ቀን ተሰብስበው በመፀለይ ይጀምራሉ:: በሃሳባቸው ተስማምቼ ሐሙስ ጠዋት አብረን ለፀሎት ተሰብስበን ነገሮችም እየተሳኩልን ሄዱ:: ሰዎቹም ሃላፊነት የሚሰማቸው በሳሎች መሆናቸውን በተግባር አሳይተዋል:: በአካባቢው እየሄድን እሁድ ጠዋት ተሰብስበን እንድናመልክ እንነግራቸዋለን፣ በእሽታ ሲንቀሳቀሱ በየእሁድ ልንሰበሰብ የምንችልበትን ትንሽ ቤት ተከራየን::

ወንጌላዊ እንደመሆኔ አዳዲስ አማኞች የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን እስኪመርጡ ድረስ ለእነርሱ የተለየ ሃላፊነት ይሰማኛል:: በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጠንክረው በእግራቸው መቆም ሲችሉ የራሳቸውን ሽማግሌዎች ያመርጣሉ እኔም ወደሌላ አካባቢ ተዘዋውሬ ማገልገሌን እቀጥላለሁ:: እሁድ ተሰብስበን ከምንፈጽማቸው ነገሮች አንዱ ፀሎት ቤት ልናቆም የምንችልበትን መሬት ለመግዛት ገንዘብ መሰብሰብ ነበር:: እኔ በ1993 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ወደ ካናዳ ስሄድ 560 ብር አዋጥተናል:: አማኞችም ጥሩ ዕድገት እያሳዩ ናቸው:: ወደኋላ ልመለስና የሁለተኛው ለኩ ቤተክርስቲያን ከመመሥረቷ በፊት በለኩ ከተማ ውስጥ ብዙ ነገሮች ተከናውነዋል::

## አራት መምህራኖች

በአብዮታዊ ለውጥ ጊዜ ከሌሎች ክፍለ ሀገራት አራት አማኞች የሆኑ በመንግሥት ት/ቤት ለማስተማር የተመደቡትን መምህራን እግዚአብሔር

አመጣልን:: በደረሱም ጊዜ በከተማ ውስጥ አጥጋቢ የሆነ መንፈሳዊ ሕብረት ወይም አገልግሎት ይኖራል የሚል ተስፋ እንዳልነበራቸው እርግጠኛ ነኝ:: እነርሱ እስከሚያውቁት ድረስ በከተማው ውስጥ ምንም ክርስቲያኖች አልነበሩም:: ስለዚህም ወቅቱ የሃይማኖት ተቃውሞ የበዛበት በመሆኑ አላስፈላጊ ግጭትን ለማስወገድ በራሳቸው ተወስነው መቆየትን መረጡ:: ከሌሎች መምህራን እና ከተማሪዎቹ ጋር ስለ እምነት ምንም አይናገሩም ነበር:: ነገር ግን ዝም ብለው የራሳቸውን ሕይወት መኖር ጀመሩ:: ከምስክርነታቸው ጠቃሚው ነገር ቢኖር በየሳምንቱ እሁድ የሚሰበሰቡበት ልዩ ጊዜ ነበራቸው::

በየእሁድ ጠዋት በድብቅ እየተሰበሰቡ የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ በህብረት ይፀልዩ ነበር:: አንድ ቀን ከሲዳማ አማኞች የሆነ ሰው ከመምህራኖቹ አንዱን እንዲህ አሰው:: «ለምን አቶ ሶርሳ ሱማሞን አትጋብዟቸውም? ምናልባት እርሳቸውም በየእሁዱ አብረዋችሁ ለመሰብሰብ ይፈልጋሉ» አለው:: ስለዚህም በአብዮቱ ንቅናቄ ወቅት በከተማው አገልግሎት እንድሳተፍ ግብዣ ተቀበልኩ::

## ግብዣ

በከተማው ውስጥ በአገልግሎታቸው እንዴት ፍሬያማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከተወያዩ በኋላ ከመካከላቸው ሁለቱን መምህራን ወክሰው ወደ አፋራራ ወደ እኔ ላኩ:: እኛ እስከምናውቀው በከተማው ውስጥ አራት ብቻ ነበርን:: በየእሁዱ ተራ በሆነች በትንሽ ክፍል እንሰበሰባለን:- በጣም ገዛ ብለን እንዘምራለን:: ቃሉንም እንብበን በጋራ እንፀልያለን:: ወደ ለኩ መጥተው ከእኛ ጋር መሰብሰብ ይችላሉ ወይ? ብለው ጠየቁኝ:- ያ ጊዜ 1970-1971 ዓ.ም አካባቢ ነበር:: በየሳምንቱ እሁድ ጠዋት በትንሿ ክፍል ቤት አብሬአቸው ለመሰብሰብ ተስማማሁ::

በመጀመሪያው እሁድ አብረን ስንሰበሰብ አምስት ሰዎች ብቻ ነበርን:: ከሳምንት በኋላ አንድ ሰው ተጨመረልንና ስድስት ሆነን:: በድብቅ ተሰብስበን ስንፀልይ ለእኔ የመጀመሪያዬ ነበር:: በተለያየ ጊዜ ለየብቻችን እንመጣ ነበር:: ምክንያቱም ለአምልኮት በይፋ መሰብሰባችን ከታወቀ በእንጭጩ ሊቀጩን ስለሚችሉ ነው::

በእንደዚያ ሁኔታ መሰብሰብ ለእነርሱ አስገራሚና የሚያበረታታቸው ነበር:: በዚያ ዓይነት ለተወሰኑ ሳምንታት ስንሰበሰብ ቆየን:: ከቀን ወደ ቀን ራዕያቸውና ብርታታቸው እያደገ ይሄድ ጀመር:: አንድ ወይም ሁለት ሰዎች አብረው በየእሁዱ ለማምለክ ፍላጐት እንዳላቸው አመለከቱ:: የእኛ መሰብሰብ በግልጽ የሚካሄድ ባለመሆኑ ነገሮችን በግልጽ ከማስራጨት በጥንቃቄ



መመርመርን መረጥን:: እንደዚህ ዓይነት ስብሰባ አደጋ ነበረውና ለሰርጎ ገቦች በር ላለመክፈት እንፈልግ ነበር::

አንዳንዶች ሰዎች ምናልባት በከተማው ውስጥ ሰወር ወዳለው አካባቢ መቀየር አለብን፣ እዚሁ ሆነን ሰዎች ዝማሬአችንን ከሰሙ አላስፈላጊ ትኩረት እንዳይሰጡ ይሉን ነበር:: አንዳንዶች ደግሞ አሁን ቁጥራችን ስድስት በመድረሱ እየፀለይን እንደቆየን አስበንበት ወደሌላ አካባቢ እንዛወር በማለት ተስማሙ:: በከተማው ዳር ሰዎች ብዙም በማያተኩሩበት አካባቢ አንዲት አነስተኛ ክፍል ቤት ተከራየንና በየሳምንቱ እሁድ ጠዋት መሰብሰብ ጀመርን::

## ፀሎት

ለተወሰኑ ወራቶች ከአፋራራ ወደ ለኩ በየሳምንቱ እሄዳለሁ:: በአዲሱ ፀሎት ቤታችን አብረን በዝግታ እንዘምራለን፣ የእግዚአብሔርን ቃል እናነባለን፣ በህብረትም እንፀልያለን፣ ከዚያም ቡና እየጠጣን እናወጋለን:: ከህብረታችን አንድነትና አብሮ መሰብሰባችን የተነሳ ብዙ ጥንካሬ አካበትናል:: ጥሩ የፍቅር ህይወትም እየጨመረና እያደገ ይሄድ ነበር::

በዚህ ትንሽ መንጋ እግዚአብሔር ምን እንደሚሠራ ላይ እደነቃለሁ:: በወቅቱ በከተማው ውስጥ ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውጪ ሌላ አሰመኖሩ ሌሎችን ለመሳብና አላስፈላጊ ትኩረት እንዳይደረግብን ረድቶናል::

እኛ እስከምናውቀው ድረስ በክፋ የሚፈልጉን አልነበሩም፣ ከሕግ ውጪ ስለማንመላለስ ምናልባት የሚከታተሉን አይመስለንም:: የእኔ አብሬአቸው መሰብሰብ ዋነኛው ዓላማ መልካሙን ዜና ለሌሎች ለመስበክ ነው:: ቃሉን መስበክና መፀለይ አዳዲስ አማኞችን ሊያመርት እንደሚችል አምናለሁ:: ይህንንም ስለሚያውቁ አማኞቹ የሚመጣውን ለመቀበል ፈቃደኞች ነበሩ::

በሕይወቴ እግዚአብሔርን ያመሰገንኩት ያን ጊዜ የማያስፈራ አቀራረብ ስለሰጠኝ ነበር:: ቢሆንም በስብከቱ ጥንቃቄ ከማድረግ አልቦዘንኩም ነበር:: በከተማው ውስጥ ወዲያ ወዲህ እየተዘዋወርኩ በሳምንት አንድና ሁለት ጊዜ ሰዎች ያዩኝ ጀመር:: እግዚአብሔር ሰላምን ወደሚፈልጉ ሰዎች እንዲመራኝ እፀልይ ነበርና እግዚአብሔርም ወደ እነርሱ መርቶኛል::

## የተለወጡ ሰዎች

በየሳምንቱ ከመምህራኖቹ አንደኛው ወይም ሌላኛው እንዲህ ይለኝ ነበር:: ከተማሪዎቻችን አንዱና ተለቅ ያለው ዳንሳሞ ወንጌልን ለመስማትና በክርስቶስ ለማመን ፍላጐት አለው:: እኛ መምህራን ሆነን ለእርሱ ብንሰብክ መልካም አይሆንልንምና ከእርስዎ ጋር እንዲገናኝ ብናደርገው ምን ይመስልዎታል? አሉኝ:: እግዚአብሔር ያመጣኝ ለዚህ እኮ ነው አልኳቸው፡ ከዚያም ከልጁ ጋር

ለመገናኘት ቀጠሮ ተያዘ። ተገናኝተንም ለዳንሳሞ ስለ ጌታ ኢየሱስ መሰከርኩለትና አመነ።

በከተማው ውስጥ ለሕዝቡና ለተማሪዎቹ ወንጌልን ስሰብክ ከጊዜ ወደጊዜ አንድ ባንድ አመኑ። እግዚአብሔርም በሰዎቹ ሕይወት በኃይል ይሠራ ነበር።

## ቀጣይ ደረጃ

በአንድ እሁድ ጧት ከአገልግሎት በኋላ ቡና እየጠጣን ስናወጋ አንዱ ከመካከላቸው እንዲህ አለ፡-

«ከአፋራራ እስከ ለኩ ደርሶ መልስ እስከ መቼ ተመላልሰው ይዘልቃሉ? ቃሉን ለመማር ፍላጎት ያላቸው ብዙ ሰዎች አሉና እዚህ ይሁኑ» አለኝ። እነርሱ የሚሉት ነገር ትክክል እንደሆነ ተረዳሁ፣ ዳሩ ግን እርሻዬንም መንከባከብ ነበረብኝ፡- በለኩ ስሰብክ ማንም የሚከፍለኝ የለም። በጉዳዩ ለጥቂት ቀናት ከፀለይኩበት በኋላ ቤተሰቤን እዚያው አፋራራ ለመተውና አንዳንዴ ብቻ እየሄድኩ ለመጎብኘት በመወሰን ወደ ለኩ ተዛወርኩ።

ከዚያም አልጋና ጠረጴዛ የሚዘረጋበትና እሳት ማንደጃ ቦታ ያለው ትንሽ ክፍል ቤት በከተማ ተከራየሁ። መጽሐፍ ቅዱሴንና የብርድ ልብሴን በማምጣት በለኩ መኖር ጀመርኩ።

## መኖሪያ ማበጀት

አንዳንድ በገጠር ያሉ አማኞች ምን ነካዎ? በዕድሜዎ እየገፉ ነዎት። እንዴት በትንሿ ቤት ራስዎ ምግብ እያበሰሉ መኖር ይችላሉ? ይሉኝ ነበር። ወደ ለኩ በተዛወርኩ ጊዜ በቅድሚያ መኖር የጀመርኩት ከነቢያ ከሁለት መምህራን ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ነበር። ነገር ግን አብረን መሆኑ ለእኔም ለእነርሱም የሚመችን አልነበረምና አልቀጠልንም። በእርግጥ በአፋራራ የራሴ ቤትና እርሻ ነበረኝ። ልጄ ሣራና ቤተሰቧ እንዲሁም ልጄ ሳሙኤል ንብረቴንና እርሻዬን ይንከባከቡልኛል።

በለኩ ጥቂት ወራት ከቆየሁ በኋላ የጳውሎስ እናት ለኩ በመዛወር አብራኝ ለመኖር ወሰነች። ስለዚህም ሰፋ ያለ ቦታ መፈለግ አለብኝ ማለት ነው አልኩኝ። በዓመታት ውስጥ ልጄ ጳውሎስና ባለቤቱ አምሳለ ባደረጉልን እርዳታ በለኩ ትንሽ መሬት ገዝተን ቤት ሠራን።

ከአፋራራ ወደ ለኩ በተዛወርንበት ወቅት የአንደኛ ለኩ ቤተክርስቲያን እያደገ ነበር። በተጨማሪም ክርስቲያኖቹ መሬት ገዝተው ቤት መሥራት ይፈልጋሉ፣ በዚያን ጊዜ ነበር ወደ ለኩ የተዛወርነው። የቤተክርስቲያኗ የእድገት አቅጣጫው በቁጥርም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወት በጣም ደስ የሚልበት ወቅት ነበር።



## የእሁድ አገልግሎት

ክፍላችን እየጠበበ ሄደ፣ ሌላ ሰፊ ቤት የምንፈልግበት ጊዜ የደረሰ አይመስላችሁም? እሁድ ጧት ከምዕመናኑ አንዱ ጠየቀን። አንድ ተራ አማኝ እንዲህ ዓይነት ሃሳብ ሲያቀርብና የሚቀጥለውን እርምጃ ለመራመድ ሲነሳሳ በሰማሁ ጊዜ በደስታ ተነቃቃሁ። በይፋ ልንሠራ ስለምንችልበት ሁኔታ ለአያሌ ሳምንታት ስንወያይ ቆየን። መሬት ገዝተን ቤት ለመሥራት ፍቃድ ብንጠይቅ ሁለመናውን ነገር እንደሚዘጉብን እናውቃለን። ከዚያ ይልቅ አምልኮአችንና በከተማው ውስጥ መኖራችን በግልጽ ለማሳየት ጊዜው አሁን ነው ብለን ወሰንን።

ትንሽ የሚረብሽንና የሚያስጨንቀን ነገር ቢኖር እስከዚያ ድረስ በከተማ ስንመላለስ በሥራ ምክንያት ከተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች ከመጡ ሰዎች በስተቀር የአካባቢው ተወላጆች የሆኑ ሲዳማዎች መጥተው በክርስቶስ አምነው ማህበርተኛ አለመሆናቸው ነው።

የፀሎታችን መልስ መሆኑንና እግዚአብሔር እንዳረጋገጠልን የተረዳነው ከከተማው አንድ ወጣት በኢየሱስ አምኖ የዳነ ሰው በቤቱ እንድንሰበሰብ ወስኖ ፈቃደኛነቱን ሲገልጽልን ነበር። ይህም በከተማ ምን ያህል ተቀባይነት እንደሚኖረን ለመፈተን ይረዳናል። የእሁድ አገልግሎት በቤቱ ስንጀምር አንድም ተቃውሞ አላጋጠመንም።

## ሕልም

አሁን በለኩ ከተማ ቤተክርስቲያን መመሥረታችንን አረጋገጥን። ለምን ከተማውን ሁሉ አናዳርስም? በሚል መንፈሴ ተነሳሳ። ከተማውን ሁሉ መድረስ ማለት ለእኔ ማህበራችንና ዋና ጽህፈት ቤታችንን ከአፋራራ ወደ ለኩ ማዛወር ማለት ነው። ለኩ ለአካባቢው የከተማ ማዕከል ነበረች። ለዋናው ቢሮአችንና ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤታችንም አመቺ ቦታ ነው። በ1969 ዓ.ም በአፋራራ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከከፈትን ወዲህ የማህበሩ ዋና ጽህፈት ቤታችን ነው። በአብዮታዊው ለውጥ ወቅት ሁሉ ፍፁም የሚስማማ ቦታ ነበር። ነገር ግን ከተማውን የራሳችን ለማድረግ ያልቻልነው ቦታ ባለመኖሩ ስለሆነ አሁን በተከፈተልን በር ለመግባት መትጋት አለብን ብዬ አሰብኩ።

የጽህፈት ቤታችንን ወደ ከተማ አዛውረን ብንመጣ ለንብረታችንና ለትምህርት ቤታችን የበለጠ ችግር ያጋጥመን ይሆናል፣ ነገር ግን እዚያ አፋራራ መቆየት ደግሞ ብዙ ጥቅሞችን ያሳጣናል መብራት፣ ስልክ፣ ፖስታ

ቤት፣ እንዲሁም የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ሁሉ ስለሌሉበት ማለት ነው:: ታዲያ በከተማ የሚጠብቀንን ተቃውሞ ሁሉ ተቋቁመን ማለፍ ይቻለን ይሆን?

## አዲሱ ጽ/ቤት

ሕልሜን ለማህበሩ መሪዎች ለማካፈል ወሰንኩ፣ የማይታሰብ መልስ አገኘሁ፤ የምናገረውን ሲያዳምጡኝ አልፈለጉም:: በእርግጥ በሰኩ ስለተቋቋመችው ቤተክርስቲያንና አማኞች ሁሉ ሰምተዋል:: ነገር ግን በሩቅ ሆነው ለማየት ነበር የፈለጉት::

በማህበሩ የውስጥ ጉዳይ ስሳተፍ የመጀመሪያዬ ነበር:: በሌላ ጊዜ የምሠራው እንደማገኛውም አባል ነበር:: አሁን ግን ለመገፋፋት የተነሳሳሁበት ምክንያት ሰላለኝ ነው:: እነርሱ ያልተረዱትን መልካም አጋጣሚ እኔ የተረዳሁ ይመስለኛል::

ጊዜው ተለወጠ፣ እኔም ሙከራዬን ቀጠልኩ:: መንግሥት በይርጋለም ከተማ ውስጥ ለመካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ሰፊ መሬት ሰጥቷቸዋል:: ለእኛ ግን መንግሥት ለጽህፈት ቤታችን ማሠሪያ ምንም መሬት አልሰጠንም፤ ምክንያቱም አልጠየቅንም ነበርና ነው::

አሁን ኑና ጽህፈት ቤትና የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የምንሠራበትን መሬት መንግሥት እንዲሰጠን ማመልከቻ እናቅርብ የምናጣው ነገር የለም ብዬ ለመንኳቸው::

የማህበሩ ሽማግሌዎች ለብዙ ወራት ሃሳቤን ፈጽመው ተቃወሙት፣ በሃሳባቸው ውስጥ እንኳን ለማስገባት አልፈለጉም:: በየጊዜው ስብሰባ በሚኖራቸው ወቅት ቀጠሮ ይዘው እንዲያነጋግሩኝ ልለምናቸው እሞክር ነበር:: ሃሳቤን እንደማይደግፉ እያወቅሁ ተስፋ ሳልቆርጥ እከታተል ጀመር::

በመጨረሻ ግን ለሚመለከተው የመንግሥት መ/ቤት ማመልከቻ አቅርበው መሬት እንዲሰጣቸው ለመጠየቅ ወሰኑ:: የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን እራሱን የቻለ የሃይማኖት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን በማዕከላዊ መንግሥት መታወቁ ለእኛ ትልቅ ጥቅም ነበረው:: በኋላም የጠየቅነውን መሬት መንግሥት በሰኩ ከተማ ውስጥ ሰጠን፣ ወዲያውም ለከተማው አማኞች የጸሎት ቤት፣ ለማህበሩ ጽ/ቤትና ለመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የሚሆኑ ቤቶችን ሠራን:: ሌሎች ተጨማሪ ቤቶችንም ሠራን:: የማኅበሩ መሪዎች ማመልከቻዎቻቸውን ወደተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በማቅረብ ብዙ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን በተግባር ተጠቅመዋል::

በተለያዩ ደረጃዎች ሽማግሌዎቹ መሬቱን ለማግኘት ስላደረጉት ጥረት ሊሸልሟቸው ይፈልጋሉ:: ያ ሃሳብ ጠቃሚ መሆኑን ሁሉም



እንደሚስማሙበት አልጠራጠርም:: የከተማ ሰዎች ባህርይ፣ የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን መሪዎች ባህርይና የማህበሩ ባህርይ በከፍተኛ ሁኔታ ተለውጧል::

## ወንጌልን በስፋት ማዳረስ

በሰኩ ለተመሠረተው ለአዲሱ ቤተክርስቲያን ሽማግሌ ወይም እረኛ ሆኜ አላውቅም:: ክርስቲያኖቹ የራሳቸውን መሪዎች እስኪመርጡ ድረስ ግን በምችለው ሁሉ እረዳቸዋለሁ:: በተመሳሳዩም በሌላ ሥፍራዎች እየሄድኩኝ ስለምሰብክ በቂ ጊዜ አልነበረኝም::

ላለፉት ከስምንት እስከ አሥር ዓመታት ለእኔ በሰኩ አዲስ የወንጌል ሥርጭቱ አገልግሎት መሠረት ሆኖልኛል:: በአፋራራ አደርግ እንደነበረው በሰኩም በተመሳሳይ ሁኔታ ሳገለግል ቆይቻለሁ:: ቃሉን በማስፋፋትና በማሠራጨት በኩል ባለፉት 50 ዓመታት ከማደርገው ጋር ተመሳሳይ ነው:: ይኸውም በሰኩ ወንጌልን «መስበክ» የአገልግሎቴ መሠረታዊ ቦታ ከሆነ ወዲህ ለተመሠረቱት ለአዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ዕውቅና አልጠይቅም ነበር:: ምክንያቱም የእኔ ተግባር ወንጌልን መስበክ ብቻ ስለነበር ነው::

እግዚአብሔር የሰዎችን ሕይወት ቀይሯል እኛም ዓላማችን የተለወጡ ሰዎች አዳዲስ ቤተክርስቲያኖችን እንዲመሠርቱ ነው:: በሐዌላና ጋርቢቾ ብዙ ጊዜ አሳልፌአለሁ ሂደቱ ምንጊዜም ተመሳሳይ ነው:: በአቦስቶ አጠገብ ሁለት ቤተክርስቲያን በማቋቋሙ ሂደት፣ የእኔ ተሳትፎ ነበረበት:: በቱላና በአቤቾም እንዲሁ ነበር:: ከዚያ በኋላም አንደኛና ሁለተኛ ፍራ ቤተክርስቲያን ተመሠረቱ:: እነዚህ ሁለቱ ቦታዎች በጣም ይርቃሉ:: ወደ ቱላ ለመጀመሪያ በሄድኩኝ ጊዜ ምንም አማኞች የነበሩ አይመስለኝም፣ ካሉም በጣም ጥቂት ይሆናሉ የሚል ግምት አለኝ::

በአቤቾም ጥቂት አማኞች ነበሩ:: በአንድ ቦታ እየሰበክሁ ብዙ ጊዜ ቆይቼ አላውቅም እሰብካለሁ፣ ወደሌላ ቦታ እንቀሳቀሳለሁ:: ለመጀመሪያ ወደ ቱላ የሄድኩት አንድ ሰው መጥቶ እዚያ ሄጄ እንድሰብክ ስለጠየቀኝ ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መጥተው ሰባኪ ይለምናሉ:: እኔ እየተለመንኩ አላስቸግርም፤ ሄጄ እሰብካለሁ፣ ብዙ ሰዎችም ስለሚያምኑ ደስ ይለኛል::

እዚያ በነበርኩ ጊዜ አንዳንድ ሰዎችን ከሌላ ቦታ አገኛለሁና አብሬአቸው ሄጄ መስበክ ጀመርኩ:: አንዳንዶቹ ቦታዎች ግን ከሰኩ ከ5-6 ሰዓት በእግር የሚያስኬዱ ናቸው:: ስለዚህ በአገልግሎቴ ላይ የተወሰነ የጊዜ ገደብ የለኝም፤ በአንዳንድ ቦታ አንድ ቀን፣ በሌላ ቦታ ሁለትና ሦስት ቀናት ልቆይ እችላለሁ::

ለመጀመሪያ ወደ ይርባ በሄድኩኝ ጊዜ ምንም ክርስቲያኖች አልነበሩም፤ አሁን ግን ብዙ አማኞች አሉ:: ይርባ ትልቅ ከተማ እየሆነ ነው:: በአሁኑ ጊዜ

በአካባቢው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተመሥርተዋል፤ የአንድ አዲስ ወረዳ ዋና ከተማም ሆኗል።

## የጡረታ ጊዜ

በቅርቡ የሲዳማ ማህበር መሪዎች ጡረታ እንድወጣ ጠየቁኝ፣ «የሚበቃዎትን ሥራ ሠርተዋል፤ አሁን ጡረታ ለመውጣት ጊዜዎ ነውና ቁጭ ብለው ዕረፍት እያደረጉ ይደሰቱ» አሉኝ። እኔም «የምትፈልጉትን አድርጋችኋል» አልኳቸው። በእኔ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አለኝ። ቃል ኪዳኔም እስክሞት ድረስ ስብከቴን እንዳላቆም ነው አልኳቸው። ስለዚህም ነው በለኩ ከተማ ዳር ያለችዋን ቤተክርስቲያን ለመመሥረት ከህብረቱ ጉን የተሰለፍኩት።

ስለዚህ በካናዳ ቆይታዬ ሰውነቴ በምቾት ቢቆይም ልቤ ግን ዕረፍት አልነበረውም።

## ወደ ጅምር ልመለስ

ታሪኬን ከመጨረሻው የጀመርኩት ልዩ ምክንያት ስላለኝ ነው። አስቀድመህ በጀመርከው ጥያቄ ልነሳ፦

እንደ ወንጌላዊ ስምን ያህል ጊዜ ሠሩ? ከ50 ዓመት በኋላ ዛሬም ራዕዩን እንደ ጥንቱ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናቸው? ጥያቄዎቹን እንደመለስኩ ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን ከ50 ዓመት በላይ ወደ ኋላ እወስድህና ጅማሬው እንዴት እንደነበረ ለመግለጽ እፈልጋለሁ። የሚቀጥለው ታሪክ በቅደም ተከተል ይቀርባል።

# ምዕራፍ ሁለት

# የእንጀራ እናቴ

## የእኔ መነሻ

እኔ የተወለድኩት በወላይታ ውስጥ ዱጉና በሚባል ቦታ ነው። ስለ ዱጉና ከተነሣ ዛሬ ሁሉም ነገር ተለውጧል። ምናልባት ዛሬ ወደ 50 ፐርሰንት ሕዝብ አማኝ ሆኗል። በወላይታ ውስጥ ከዚያ አካባቢ ብዙ ወንጌላውያን እየተላኩ መልካሙን ዜና ሰብከዋል። በአካባቢው ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትቤቶች ያሉበት ሲሆን፣ የወላይታ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን የተስፋፋበት ትልቁ ወረዳ ነው። እናቴ የሞተችብኝ እኔ በጣም ትንሽ ልጅ ሳለሁ ነበር። የእናቴ መሞት በሕይወቴ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሮብኛል። እናቴ በጣም ወጣት ሴት ነበረች ምን እንደምትመስል አስታውሳለሁ።



መሞቷን ባወቅሁ ጊዜ ወንጌልን ሳትሰማ በመሞቷ በጣም አዝኜ ነበር፣ የእርሷ መሞት ግን እኔ መልካሙን ዜና እንድሰማ አዘጋጅቶኛል። ከሞተች በኋላም ልቤ ጥያቄውን አላቆመም። ለሕይወት ከዚህ በላይ ያለ ነገር ምን ይሆን? በጠቅላላው ሕይወት ምንድን ነው? እል ነበር። ሽምግል ያሉ ሰዎች እርስ በርስ ሲነጋገሩ እሰማ ነበርና አስፈላጊ መስሎ ሲታየኝም ጥያቄ አቀርብላቸው ነበር። ነገር ግን አጥጋቢ መልስ ሊሰጠኝ የቻለ አልነበረም።

## የወላጆቼ ሃይማኖት

እኔ በተወለድኩ ጊዜ ቤተሰቦቼ የወላይታን ሕዝብ ባህላዊ ሃይማኖት የሚከተሉ ነበሩ። በወላይታ የጥንት አማኞች ሕዝቡን በአራት የሃይማኖታዊ ክፍል መድቧቸው ነበር። በጊዜው ክርስቲያን የሚሉዋቸው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ብቻ ነው። ቀጥሎም የእስልምና እምነት ተከታዮች፣ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉትና ከነዚህ ውጪ በአራተኛው ምድብ ውስጥ የነበሩት ግን እኛ ሰይጣንን እናመልካለን ብለው አይናገሩም።

ምክንያቱም ሰይጣን ማን እንደነበረ ስለማያውቁ ነው። ሰይጣን ብለው ያስተዋወቁት ከምዕተ ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ካህናት ነበሩ።

የባሕል ሃይማኖት ተከታዮች በወላይታና በሲዳማ ባለውቃቢ ተብለው በከፍተኛ ደረጃ የሚከበሩ ነበሩ። ይህ ውቃቢ የሚባለው ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ ማለት ስለ ሳይንስ ምንም ዕውቀት የሌለውን ሰው «ውኃ ምንድን ነው?» ብሎ እንደ መጠየቅ ይቆጠራል።

ስለ ውቃቢ የሚያውቁት በጣም አስፈላጊው ነገር የሚደመስስ ትልቅ ኃይል ያለው መሆኑን ነው። በማያምኑት ሰዎች አዕምሮ ውስጥ የቀረ አንድ ጥያቄ ነበር።

“ አባቶቻችን ውቃቢ ይቆጣል ወይም አይቆጣም? ” የሚል ሲሆን ይህ ጥያቄ ከፍርሃት የመነጨ ነው። ጥያቄው አንድ ተግባራዊ ፈተና ያዘለ ይመስላል። ምክንያቱም ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት እጅግ አስፈላጊ በመሆኑና በሁለት ቡድን የተከፈሉ ሰዎች ስላሉ ነበር፣ ለዋጋ ወይም ለክፍያ ሲመልሱ የሚችሉ ሠራተኞች ናቸው ማለት ነው።

አንዱ ቡድን ጥያቄዎቹን ለመመለስ የሚሞክር ሲሆን፣ ሌላኛው ቡድን ደግሞ ሰዎችን የሚረግሙትን ለመቅጣት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ነው። ብዙውን ጊዜ ሁለቱም ቡድን የሰዎችን ፍርሃት ምክንያት በማድረግ ገንዘብ የሚሰበስቡ አልነበሩም።

ወደነዚያ ሠራተኞች ወይም ባለውቃቢ ሰዎች ለመረጃ ከመጡ መልሳቸው ፈጽሞ የማይለዋወጥ ይሆናል:: ይኸውም፣ «ይህንና ይህን ካላደረግክ ወይም የሆነ ነገር ባታደርግ አንዳች ክፉ ነገር ያጋጥምሃል» ይሉና መልካም ነገር እንዲያጋጥማቸው ከፈለጉ ስጦታ እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ:: ያ ስጦታ ከሌለ የመንፈሱ ኃይል የሚፈጥረው ሞትን በሽታን፣ ድህነትንና ጉዳትን ይሆናል::

ስለዚህም ሰዎች ማንኛውንም ያላቸውን ነገር ይሰጣሉ:: ይህ ባሕላዊ ሃይማኖት ሰዎች እንስሳትን እንዲያርዱ ወይም ለባለውቃቢዎቹ እንዲያበረክቱ ይገፋፋል::

## የባለቤትነት መንፈስ

ለማሳጠር ያህል፣ እናቴ ከሞተች በኋላ አባቴ ሌላ ሴት አገባ:: እንጀራ እናቴ አንዳንዴ እንደ ባለውቃቢ ስለምትሆን በመጀመሪያ የምትሠራቸውን አንዳንድ ሥራዎች አይቼ ነበር፣ ትዘፍናለች ታዜማለች እንደ ልዩ ሰው ትሆናለች:: ከወደኋላ ይህን ተግባሯን ስንመለከት በሰይጣን እንደ ተወሰደች ቆጠርናት፤ ለተወሰኑ ሰዓቶች ከዘፈነችና ካፏጨች በኋላ ራዕይና ህልም እንዳላት ትናገር ጀመር::

ያልተለመደ ድምፅ ታሰማለች፣ ከዚያም ሰዎች ይጠይቋታል:: እርሷም መመሪያ ትሰጣቸው ነበር:: እርሷ ሙሉ ጊዜያቸውን በዚህ ተግባር እንደሚያባክኑ ሰዎች አልነበረችም:: እንደ እርሷ አባባል ይህ የትንቢት መንፈስ የሚመጣላት በዓመት ውስጥ ልዩ በሆነ ጊዜ ነው:: እርሷ የምትሰጠው መመሪያ በአፋጣኝ ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ለሰዎች ትናገር ነበር:: የእርሷ ነገር እውነተኛ መሆኑንና አለመሆኑን ለመመርመር ሰዎች ጊዜ አልነበራቸውም::

ሰዎች ለእርሷ ካልታዘዙ በሞት እንደምትቀጣቸው ታስፈራራቸዋለች:: ለእርሷ ምክንያታዊ በሚሆን ጊዜ ሰዎች ለየት ያለ ምግብና መጠጥ እንዲያዘጋጁ ትነግራቸውም ነበር:: አንድና ሁለት ሰዎች ከበሮ እየመቱ እርሷ እየተሽከረከረች ትዘፍናለች::ይህን አድራጎቷን በቤት ውስጥ እንዳታደርግ አባቴ ይከለክላት ነበር:: እርሷም መንፈሱ ያንን እንድታደርግ እንደሚነግራትና ሌላ ምርጫ እንደሌላትም ትገልጽ ነበር::

በአንድ ጊዜ አባቴ ሰባት ወይፈኖችን እንዲያርድና እንዲሰዋ በነገረችው ወቅት እኔ ያልተረዳሁት ነገር ቢኖር አባቴ የተባለውን ቢፈጽምም ባይፈጽምም፣ በገጠር ውስጥ ብዙ ሰዎች የእንስሳትን አንጀት ወይም ሞራ የሚገልጡና ስለ ውቃቢ መልስ ለመስጠት የሚሞክሩ መሆናቸውን ነበር::

ቤተሰቤ በዚህ ዓይነት መንፈስ የሚሰቃዩ መሆናቸውን ሳይ በጣም ፈራሁና ተረበሽኩ:: በጊዜው እያንዳንዱ ሰው ጥያቄ ቢኖረውም መልስ ያገኝ



አይመስልም:: እግዚአብሔር ግን ለእንጀራ እናቴ ልዩ የሆነ ነገር አዘጋጅቶላታል::

## የሶዶ ሆስፒታል

በዚያን ወቅት የእንጀራ እናቴ በሞቃትና በደረቅ አየር ምክንያት በሚፈጠር ቁስል እግሯን ታመመች:: የባላገር ሰዎች የባሕል መድኃኒት እያሰሩላት ብዙ ቢሞክሩም፣ ቁስሏ በስፋትና በጥልቀት እያደገባት ይሄድ ጀመር:: በመጨረሻም አባቴ በእግር የአንድ ቀን ጉዞ በማድረግ ወደሚያደርስበትና ደህና ሐኪም ወደሚገኝበት፣ ወደ ሶዶ ሆስፒታል ወሰዳት:: እዚያ ሆና አንድ ሰው ወንጌልን ሲሰብክ ሰማች:: ሰባኪውም "በፍርሃት ውስጥ መኖር የለባችሁም፣ ነፃ መውጣት አለባችሁ:: ፈጣሪያችን በጣም ስለወደደን ልጁን ልኮልናል፤ ስለ ኃጢአታችን እንዲሞትልን አድርጓል:: ወንጌላዊውም ሲሰብክ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንን ከፍርሃትና ከሚመጣው ፍርድ ነፃ እንወጣለን" እያለ በሐኪም ቤቱ ማረፊያ ክፍል ለነበሩት ሁሉ ወንጌልን ይሰብክ ነበር::

የእንጀራ እናቴ በሐኪም ቤት በቆየችባቸው ቀናቶች ውስጥ ለእግር ቁስል ሕክምና እየተደረገላት በተመሳሳይ ጊዜም ስብከቱን ለብዙ ጊዜ ታዳምጥ ነበር:: በተደጋጋሚ ከመስማቷ የተነሳ የተባለውን ሁሉ በቃሏ ይዛለች:: እርሷም በሐኪም ቤቱ ማረፊያ ክፍል ውስጥ ከነበሩትና ከሚያምኑት ወገን አልነበረችም:: ነገር ግን ስብከቱ ሊጠፉ የማይችል ትዝታና ግንዛቤ በመስጠት ቃሉን በአዕምሮዋ ውስጥ ቀርጾላታል::

የሰማችው ቃል ለእርስዋ በጣም አስፈላጊ ነበር፣ የተቀረጸባትም እውነት የሰማቸውን ስብከት እንዳለ በቃል እንድትይዘው አድርጓታል ወይም ረድቷታል:: የሰማችውን እውነት በአእምሮዋ ውስጥ አጥብቃ ይዛለች:: ወደ ቤት በምትመለስበት ጊዜ የሰማችውን ሁሉ ለጎረቤቶችዋ በትክክልና በአድናቆት ልታሰማቸው ችላለች:: እኔም ይህን መልካም ዜና ለመጀመሪያ ጊዜ ካልተለወጠች እንጀራ እናቴ ሰማሁ::

## ለመጀመሪያ ጊዜ መስማት

አንድ ቀን ጠዋት በቤቴ ተቀምጬ እሳት እሞቅ ነበር:: የእንጀራ እናቴ ከደጅ ሆና በከፍተኛ ድምጽ የሞቀ ወሬ ታወራለች:: የምትናገረውን እያንዳንዱን ቃል ከቤት ሆኜ እንደምሰማት እርሷ አታውቅም ነበር:: ለእኔ ለመስበክ ግን ቅን አስተሳሰብ አልነበራትም:: ቢሆንም እኔ በቂ መልዕክት ተቀብያለሁ:: በውስጤም ፍላጐት አሳድሮብኛል::

ጥቂት የጐረቤት ሴቶች ከብበዋት በሶዶ ሆስፒታል የሰማችውን ሁሉ ትነግራቸው ጀመር:: ያ ሰው ትልቅ መጽሐፍ ከፍቶ እያነበበ፣ «እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮ እንዲሞትልን አድርጓል:: እርሱ የሞተልን እኛ ስለሠራነው ኃጢአት ነው:: ሞቶ ከተቀበረም በኋላ ከሞት ተነስቷል:: ከሞት ሊያድነን የሚችል እርሱ ብቻ ነው:: በእርግጥ ብናምን በአዲስ ሕይወት ውስጥ እንኖራለን እናም አይፈረድብንም» ትላቸው ነበር::

በእርግጥ በጽሑፍ ያየችው ነገር አልነበረም:: ነገር ግን በሶዶ ሆስፒታል ማረፊያ ክፍል ውስጥ በለባኪው የተነገረውን ስብከት ቃል በቃል እየዘረዘረችና እየደጋገመች ትነግራቸው ነበር::

ይህን ስሰማ አእምሮዬን መጠቆጣጠር አልቻልኩም:: ዓለምን የፈጠረ እግዚአብሔር ስለ እኔ ያውቅ ይሆን? እናም ይወደኛል? ስለምንድን ነው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ኃጢአት የሞተልኝ? ከሞተስ በኋላ በሦስተኛው ቀን ተነሳ በእርሱ ካመንኩ ከፍርሃት ነፃ ሆኜ በአዲስ ሕይወት መኖር እችላለሁ? እያልኩ ራሴን እጠይቅ ጀመር::

ወደ ውጪ እየወጣሁና እየገባሁ የእንጀራ እናቴ ስትናገር የነበረውን አሰላስል ጀመር:: እንደዚህ ዓይነት መልዕክት ስሰማ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር:: የእንጀራ እናቴን ምንም አልጠየኳትም፣ ለእርሷም ሆነ ለሌሎች የቤተሰብ አባላት አንዳች አልተናገርኩም:: ይህንን የእንጀራ እናቴ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሰምታ የነበረውን እኔም ለብቻዬ ሆኜ በዘዴ ለመከተል ፈለግሁ::

## የወንጌላውያን መድረስ

ከሁለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ አቶ ታደሰና አቶ ሶርሳ የሚባሉ ወንጌላውያን ቅርባችን በሆነ አካባቢ ደርሰው እየሰበኩ መሆናቸውን ሰማሁ::

ማሌኮ የሚባል ሰው በኢየሱስ አመነ:: ጐረቤቴ የሆነ ሰው መጥቶ ከእኛ በእግር 10 ደቂቃ በሚያስኬድ ርቀት ላይ የሚገኘው ማሌኮ ወደ ወንጌላውያኑ ሄዶ ስብከታቸውን እንደሰማና እንዳመነ ነገረኝ:: ያ ጐረቤቴ አክሎም ሁለቱ ወንጌላውያን ያረፉት በማሌኮ ቤት መሆኑም ይወራል አለኝ::

አጫጭር እግሮቼ እንዳፋጠኑኝ ወደ ማሌኮ ቤት ገሠገሥኩ:: እውነትም ወንጌላውያኑ እዚያ ነበሩ፣ በወቅቱም ብዙ ሰዎች ከደጁ ተሰብስበው ነበር::

አቶ ታደሰና አቶ ሶርሳ እያንዳንዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነበራቸው:: እነርሱም ይሰብኩ የነበረው ከእንጀራ እናቴ የሰማሁትን ተመሳሳይ መልዕክት ነበር:: ከስብከታቸው መጨረሻም በኢየሱስ ለማመን የሚፈልግ ማን ነው? ብለው ጠየቁ:: በወቅቱ ብዙ ሰዎች መልስ ባይሰጡም እኔ ግን ፈቃደኛ ሆኜ ቆምኩ::



ከወንጌላውያኑ አንዱ በኢየሱስ ለማመን ትፈልጋለህ? አለኝ እኔም ፈራሁና «ኢየሱስ ከፍርሃት ሁሉ ነፃ ካወጣኝና እንደሰማሁትም ከሞት በኋላ ሕይወት የሚሰጠኝ ከሆነ በእርሱ ለማመን እፈልጋለሁ» ብዬ እንደቆምኩኝ ነገርኩት:: እርሱም ድንቅ ነው እግዚአብሔር ይባርክህ፣ እንፀልይልሃለን አለኝና እንድቀመጥ አዘዘኝ:: ወደኋላዬ ስመለከት በሆነው ሁሉ በጣም ተደነቅኩ:: እጄን አንስቼ ከእነርሱ ቃል በኋላ የደጋገምኩት ነገር አልነበረም:: ወደ እኔ ቀርቦ ያነጋገረኝም አልነበረም:: በሚቀጥሉትም ቀናቶች ብዙ ሰዎች አመኑ:: የዱጉና ፋንጎ ቤተክርስቲያን በዚሁ አገልግሎት ሳቢያ አደገች::

በአካባቢው የመጀመሪያ የነበረውን ቤተ ክርስቲያን ስጐበኝ የመጀመሪያ ጊዜዬ ሲሆን፣ ለተወሰነ ጊዜም ከእነርሱ ጋር ስካፈል ቆይቻለሁ::

## የመጀመሪያ ስብከቴ

ወደ ቤት እንደተመለስኩ ለአባቴና ለእንጀራ እናቴ በኢየሱስ ማመኔን ነገርኳቸው፣ ግን አልተደሰቱም አላዘኑም:: ያ ያንተ ምርጫ ነው አሉኝ:: እነርሱም እንደ እኔ እንዲያምኑ ነገርኳቸው:: ከአንድና ከሁለት ሰዓት በፊት ከወንጌላውያኑ ሰምቼ የነበረውን በሰፊው ገለጽኩላቸው:: ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ሁሉም አመኑ:: አሁን ወደኋላዬ ስመለከት ያ የመጀመሪያ ስብከቴ እንደነበር እገምታለሁ::

አባቴና የእንጀራ እናቴ ሁለቱም ቃሉን ለመስማት ወደ ወንጌላውያኑ ሄዱ፣ ከዚያም ወንጌላውያኑ ወደ እኛ ቤት መጥተው ለጐረቤቶቻችን ሁሉ ሰበኩ::

እናቴ አራት ልጆች ብትወልድም የመጀመሪያዋ በህፃንነቷ ሞታለች:: የእንጀራ እናቴም አራት ልጆች ወልዳለች፣ እንዲሁም አባቴ ከሌላይቱ ሚስቱ አራት ልጆች የወሰደ ሲሆን፣ በአጠቃላይ በቤተሰባችን አሥራ አንድ ልጆች ነበሩ:: ታላቅ እህቴ በህፃንነቷ ስለሞተች ለአሥሩ ልጆች ታላቅ እኔ ነኝ:: ታላቅና ወንድ ልጅ መሆኔ በቤተሰቡ ውስጥ በአክብሮት እንድታይ አድርጐኛል::

በአጭር ጊዜ ውስጥ አባቴ፣ የእንጀራ እናቴን ፣ የአባቴ ሌላኛዋ ሚስቱ ሁሉም ወንድሞቼና እህቶቼ አንድም ሳይቀሩ ጌታ ብዙ የሩቅ ዘመዶቻችን ሁሉ ሳይቀሩ ክርስቲያኖች ሆኑ:: ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገንኩ:: አጐቴ አቶ ሶማኖ በወቅቱ ለአንድ አማራ ተቀጥሮ ይሠራ ነበረ:: እርሱ ባያምንም እንኳን ምንም ተቃውሞ አላሰማም:: ነገር ግን ታላቅ ወንድሙም ከቤተሰቡ ሁሉ ጋር በክርስቶስ አመነ:: ከጥቂት ዓመታት በኋላ የሶማኖ ቤተሰቦች ብዙዎች አምነዋል:: ሁሉም በዱጉና ፋንጎ ቤተክርስቲያን የጌታን ቃል ይካፈሉ ነበር::

## የተለወጠ ቤት

የእንጀራ እናቴ ባመነች ጊዜ በቤት ውስጥ የነበረውን ከባዕድ አምልኮዋ ጋር የተያያዘውን ትርኪምርኪ ሁሉ ከቤት ጠርገን አወጣን። የሚጐበኙን ወንጌላውያንም እንደዚያ ዓይነት ነገሮችን ሁሉም ከየቤቱ እንዲያስወግድ ይወተውቱ ነበር። የእንጀራ እናቴ ሕይወቷን በቅድስና እንድትመራና ለኢየሱስ እንድትገዛ እግዚአብሔር አስችሏታል። ክርስቶስን በመቀበሏም ደስተኛ ሆነች፣ ሰይጣንን ካደች፣ ቤታችን ከፍርሃት ይልቅ በዝማሬና በደስታ የተሞላ ሆነ።

የእንጀራ እናቴ አስቀድማ የምታመልክባቸውን ባዕድ ነገሮች ሁሉ እርግፍ አድርጋ በመተው በአዲስ ሕይወት መመላለስ ጀመረች። አስቀድማ ትጠቀምባቸው ስለነበሩ ባዕድ ነገሮችም እያነሳች ትነግረን ጀመረች። ሁሉንም ከቤት አውጥተን ጥለናል እና ቤታችን የክርስቶስ እና የእኛ ሆኗል።

## በቤተ ክርስቲያን ሕይወት የመጀመሪያ ሙከራዬ

የዱጉና ኦፋ ቤተ ክርስቲያን ከእኔ ቤት አጭር ርቀት ነበረው። ስለዚህም አንዳንዴ ከቤት ወደ ቤት እንደገባሁ እቆጥራለሁ። በየምሽቱ ወደ ቤተክርስቲያን እሄዳለሁ፣ በአማርኛ መጻፍና ማንበብ እዚያው ከመማሬም በላይ የመዝሙር ጥናቶችና የፀሎት ጊዜያቶችም ነበሩኝ።

ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ያነባሉ፣ ስላነበቡት ክፍልም ይወያዩበታል። በጊዜው የነበረን መጽሐፍ ቅዱስ ለሁላችንም የሁለተኛ ቋንቋችን በሆነው በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈ ነው። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳንጠቀም እንቅፋት አልተደረገብንም፣ ይህም ምናልባት አንዱ ዘመዳችን አማራ ለሆኑትና በዘመኑ የመሬት ከበርቴ ለነበሩት ስለሚሠራ መከታ ስለሆነልን ይመስለኛል።

በአማርኛ መናገር ፈለግን ቻልን። ክርስቲያኖች ከሆንን በኋላ ግን የአማርኛ ን መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ፈለግን። <u>የዱጉና ኦፋ</u> ቤተ ክርስቲያን አዲስ እንደመሆኑ ሁሉም ሰው ጉጉት ነበረው። እያንዳንዱ አማኝ ወንጌላዊ ነበር። ሰዎች ስለ ኢየሱስ ሳይሰሙና ሳያምኑ አንድ ቀን እንኳ አያሳልፉም ነበር፣ እያንዳንዱ ሰው በክርስቶስ ላገኘው አዲስ ሕይወት ይደነቅ ነበር።

እሁድ ሁልጊዜ ለእኛ ልዩ ቀን ነበር፣ ነገር ግን መስበክና መፀለይ እሁድ ብቻ አለመሆኑን ከግምት ውስጥ ያስገባ አልነበረም። በእያንዳንዱ ቀን ቃሉን መስበክና መፀለይ ይቻላል። በተለይም በወላይታ አማኞች ዘንድ በየሳምንቱ ሐሙስ ጧት ለተወሰኑ ሰዓቶች ተሰብስበው መዘመርና መፀለይ የተለመደ ሆኗል።

እሁድና ሐሙስ እንደ ሠርግ ሥነ ሥርዓት ይታያል። በተጨማሪም ሐሙስ ቀን ልዩ የሴቶች ስብሰባ የሚካሄድበት ቀን ነበር። <u>የዱጉና ኦፋ</u>



ቤተክርስቲያን መጀመሪያ ስትመሠረት ብዙ የሚጐበኙን ወንጌላውያን ነበሩ። አንዳንዶቹ ከሩቅ አቶና እየመጡ ይሰብኩና ያስተምሩ ነበር። ከእነርሱም አንዱ የአቶ ሶሪሳ ወንድም ሲሆን፣ የሴቶች ቡድንም እንዲሁ ከሶዶ ቤተክርስቲያን ለመዘመር ይመጡ ነበር። እነዚያ ጐብኚ ወንጌላውያንና የኳየር መዘምራን ብዙውን የአካባቢውን ሕዝብ ይስቡ ነበር። ጐብኚዎችና መዘምራንን ለመመልከት የሚመጡ ሰዎች በክርስቶስ አምነው ይመለሳሉ።

እንደ አስደናቂ ጅምሩ ከሆነ የዱጉና ኦፋ ቤተክርስቲያን ብዙ ወንጌላውያንና ሰባኪዎችን ወደ ሌላ አካባቢ አልሰደደችም። በጊዜው የነበሩት የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ቃሉን ወደ ውጪ ለማሰራጨት ትክክለኛ ራዕይ አልነበራቸውም። ለእግዚአብሔር ጥሪ መልስ ለመስጠትና ወደ ሲዳማ ለመሄድ ወንጌላዊ ሆኜ ስነሳ ያደረጉልኝ ዕርዳታ በጣም ትንሽ ነበር። አንዳቸውም ወደ ሲዳማ መጥተው አልጐበኙኝም። አንድ ጊዜ ልጐበኛቸው ከሲዳማ ወደ ወላይታ በሄድኩኝ ጊዜ ለምግብህ ብለው አንድ ብር ሰጥተውኛል። ድርጊታቸው አሳዛኝ ቢሆንም፣ እኔ ግን ከመቆጣት ይልቅ በሳቅ አሳልፌአለሁኝ።

## የመጀመሪያው ጥምቀት

በዱጉና አካባቢ የመጀመሪያው ጥምቀት የተፈፀመው ምናልባት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ካመኑ ከሁለት ወር በኋላ ይሆናል። ቃሉን ለመስበክና አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ለመመሥረት በጊዜው ተቃውሞ አልጠፋም። ከዚህም የተነሳ ብዙ ስብሰባዎችን በየምሽት እናካሂድ ነበር። እራታችንንና የብርድ ልብሶቻችንን ይዘን እንሄድና እዚያው በቤተክርስቲያን በልተን እየፀለይን እናድራለን።የመኝታ ጊዜያቶቻችንም አጭር ነበሩ።

ከመጀመሪያ ጀምሮ ፀሎታችን ለማህበሩ ዋና ዋና ነገሮችን አጠቃልሎ የያዘ ሕይወት ነበር። በተለይም በእሥር ቤት ለነበሩት አጥብቀን እንፀልይላቸዋለን። ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ለወንጌላውያን እንዲሁም ደግሞ ስታመሙትና ልጅ ለሌላቸው ሁሉ ተግተን እንፀልይ ነበር።

አቶ ብሩ በወቅቱ የአብያተ ክርስቲያናት ኀሬዝዳንት ነበሩና አንዳንዴ እየመጡ ይጐበኙናል። አቶ ጉዳዩ በኋላ ከዋና መሪዎች አንዱ ወንጌላዊም ነበሩና እርሳቸውም ይጐበኙናል። አንዳንድ ወንጌላውያን ሊጐበኙን በሚመጡበት ጊዜ ለሳምንታት ይቆዩና በአካባቢው እየዞሩ በመስበክ አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን ለመመሥረት ይረዳሉ፣ ነገር ግን በአንድ ስፍራ ለረዥም ጊዜ አይቆዩም።

አስታውሳለሁ የመጀመሪያው ጥምቀት የተፈፀመው በምሽት ከእኔ ቤት የአራት ሰዓት መንገድ በእግር በሚያስኬድ ቦታ ላይ በሚገኝ ወንዝ ውስጥ ነበር። በአካባቢያችን ወንዝ ባለመኖሩ ነበር ያን ያህል ርቀት የተጓዝነው።

የወንዙን ስም አሁን ባላስታውስም በዳሞታ ተራራ አቅጣጫ ነበር:: በመጀመሪያው ጥምቀት ከዱጉና አካባቢ ብዙ ሰዎች ተጠምቀዋል:: ምን ያህል እንደነበሩ ግን በትክክል አላስታውስም:: በጊዜው የወንጌላውያኑ ማጥመቅ የወላይታ ባህል ባይሆንም ወንጌላውያኑ ግን ያጠምቁ ነበር:: ጥምቀት በሌሊት ይፈፀም የነበረበት ምክንያት የጣሊያን ወታደሮች ስለሚቆጣጠሩና የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳይመስላቸው ስለተፈራ ነበር::

## ሁለት ሚስቶች

ከመጀመሪያው ጥምቀት በኋላ አባቴ ለመጠመቅ ፈለገ:: ቢሆንም ሊጠመቅ አልቻለም:: ከመጠመቅ የታገደበት ምክንያት እርሱ ሁለት ሚስቶች ስለነበሩት ነው:: ሁለት ሚስቶች እስካሉት ወንጌላውያኑ እንደማያጠምቁት እርሱም ያውቅ ነበር:: ለእርሱ ነገሩ ግራ የሚያጋባው የሆነበት ምክንያት ከሚቿ እናቴ ሦስት ልጆች ወልደዋል፣ ስለዚህ አባቴ ሦስት ሙሉ ሰዎችና አሥራ አንድ ልጆች መመገብ ነበረበት::

እኔ ታላቅ ልጁ እንደመሆኔ አባቴ ሁልጊዜ አሳቤን እንዳካፍለው ይጠይቀኛል:: አንድ ቀን እንዲህ አለኝ፣«ሶርሳ ምን ባደርግ ይሻለኛል? ለመጠመቅ እፈልጋለሁ፣ ሁለተኛ ሚስቴን እንዴት ላድርጋት? ምንስ ብዬ ልተውሽ ነው ልበላት? የመጀመሪያ ሚስቴስ አሥራ አንድ ልጆችን ለብቻዋ እንዴት አድርጋ ማሳደግ ትችላለች?» አለኝ:: እኔም «እግዚአብሔር ይቆጣጠራል ብዬ አስታወስኩት፣ እግዚአብሔር ልንሰራ የፈለገውን እንሥራ ብለን ከተነሳን ለእኛ የሚያስፈልገንን ሁሉ አንድ በአንድ ሊያከናውንልን እርሱ ይችላል:: እርሱ አንድ ነገር እንድናደርግ ከነገረን ለእኛ የሚበጀውን እንዴት አድርጐ እንደሚያስተካክል እራሱ ያውቃል» አልኩት::

የነገርኩትን ሃሳብ አባቴ ለጥቂት ጊዜ አሰበ:: የእኔ አሳብ ትክክል እንደሆነ ተረዳና ተስማማ:: ምክሬም እግዚአብሔር የፈለገውን መፈፀም እንዳለበት ነበርና በደስታ ተቀበለ::

ሁለቱ ሚስቶቹም አምነዋልና አባቴ መልካም የሆነውን እንዲያደርግ ያፈልጋሉ:: ሁለቱም ደግሞ መጠመቅ ይፈልጋሉ:: ሁለተኛዋን ሚስቱን አባቴ ባነጋገራት ጊዜ ወደ ቤተሰቦቿ ለመመለስ ፈቃደኛ መሆንዋን ገለፀችለት:: ምናልባት ታንገራግራለች ወይም ትቆጣለች የሚል ግምት ነበረውና በባህርይዋ መለወጥ አባቴ በጣም ተደንቋል::

ይህን ሁኔታ እንደወሰነች አንድ ሰው መጥቶ ሊያገባት ጠየቃት፣ እርሷም ተስማምታ አንድ ልጇን ይዛ ሄደችና አገባችው:: ሦስቱ ልጆቿ ግን ከአባቴ ዘንድ ቀሩ:: አባቴ ከተጠመቀ በኋላ ለጥቂት ጊዜ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሆኖ ነበር፣ ነገር ግን በሕይወት ብዙ አልቆየም ታመመና ወዲያው ሞተ:: ወላጆቼ



በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ እንደ ወላይታ ባህል ታላቅ ልጅ እንደመሆኔ በአጠገባቸው ሆኜ በስተእርጅናቸው የመንከባከብ ሃላፊነት ይኖርብኝ ነበር:: እግዚአብሔር ግን ከዚያ ሃላፊነት ገላግሎኝ ሌላ የወንጌል ሃላፊነት ሸክም ሰጠኝ::

## ንባብ መማር

ያን ጊዜ ብዙ ሰዎች በተለይም ወጣቶች ክርስቲያኖች እንደሆኑ ወዲያው ንባብ ለመማር ይፈልጋሉ:: በዚያን ጊዜ በወላይታ ብዙ ሰዎች አማርኛ በደንብ ለመናገር ቢችሉም መፃፍና ማንበብ አይችሉም :: ስለዚህ መጻፍና ማንበብ መቻል ክብር ነበረው::

በአቶ ማሌኮ ቤት አማርኛ ማንበብ የምትችል ልጃገረድ ነበረች፣ ቦታው ከእኔ ቤት የአሥር ደቂቃ እርምጃ ይርቃል:: ማንበብ በመቻሏ እኔ በጣም አከብራታለሁ:: እርሷ ትረዳኝ ስለነበር ፊደሎችን ለመለየትና ለማንበብ ሞክሬአለሁ:: የተቀላቀሉ ፊደላትን በጊዜው አቡጊዳ የሚባሉትን በማጥናት ወደ ንባብ እንደርስ ነበር::

በዚያን ጊዜ በወንጌላውያን እጅ መጽሐፍ እየሁና አንድ ፈለግሁ:: አንድ መጽሐፍ እንደሚያስፈልገኝ አውቅ ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብም የአማርኛ ፊደላትን ለመማር ፈለግኩኝ፣ ጌታ ረድቶኝ ተማርኩም:: በኋላም ሰዎች አማርኛ ማንበብ እንዲችሉ ማስተማር ዋነኛው ተግባሬ ሆነ:: ማንበብ እና መፃፍ የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት መግቢያ መንገድ ነው:: እንደገናም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል መግቢያ መንገድ እንዲያገኙ ለማድረግ አንድ መንገድ ብቻ ነበር፤ ያውም የአማርኛን መጽሐፍ ቅዱስ ማግኘት ነው::

## የመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱሴ

«በግድ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ያስፈልገኛል::» ይህ ሃሳቤ የመጣልኝ ለመጀመሪያ ጊዜ አቶ ታደለ የሚባሉ ወንጌላዊ ከአንድ ትልቅ መጽሐፍ ሲሰብኩ ባየሁ ጊዜ ነበር:: ነገር ግን ገንዘብ እማገኘው እስከገዛ ከዓመት በላይ መቆየት ነበረብኝ:: በቤተሰባችን ውስጥ እኔ ታላቅ ልጅ በመሆኔ አባቴ ብዙ ነገሮችን ለጥቶኛል:: አንዲት ላም በቤት ጥጃ ስትወልድ ጥጃዋን ለእኔ ሰጠኝ:: በዓለም ውስጥ የነበረኝና ልሸጠውም የምችለው ሀብቴ ያ ጥጃ ብቻ ነበር:: ወጣት በነበርኩ ጊዜ በገጠር ገንዘብ ከፍሎ የሚያሰራኝ ሰው አልነበረም፣ ምክንያቱም በጊዜው ያኔ ለገንዘብ ተብሎ ስለማይሠራ ነው::

ስለዚህ ጊደሬን በ5 ብር ሸጬ መጽሐፍ ቅዱስ ገዛሁ:: ከዱጉና እፋ ቤተክርስቲያን አንዳንድ አማኞች ወደ ሶዶ ሲሄዱ መጽሐፍ ቅዱስ እያመጡ ይሸጡ ነበር:: ይህንን ትልቅ መጽሐፍ ቅዱስ ይዤ በአካባቢው ስዞር አባቴ

ኮራብኝ /አደነቀኝም/። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖረኝ እርሱም ሲመኝልኝ ኖሯል። አማርኛ ማንበብ በመቻሌም አባቴ በጣም ደስ ብሎታል። ጥቂት አማኞች አዲስ ኪዳን ቢገዙም የሁሉም ሰው ምርጫ ግን ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ መግዛት ነበር።

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አንዳንድ ካህናትና ዲያቆናት መጽሐፍ ቅዱስ ነበራቸው፣ የእኛው ዓይነት ግን አልነበረም። እኛ እናገኝ የነበረው በኤስ አይ ኤም ድርጅት በኩል ነበር።

በዚያን ጊዜ ከዱጉና ፋንጎ ቤተክርስቲያን አንድም ሰው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የገባ አልነበረም። ስለዚህም ቋሚ የሆነ የማስተማር ስልት አልነበረንም። እኛው እያነበብን እንማማራለን። ስላነበብነውም ከፍል እንወያያለን። አሳብ ለአሳብ እንለዋወጣለን፣ የሚያስደንቀው ነገር ቢኖር ስለ ክርስትና እምነት ፈሩን አንስትም ነበር።

የአማርኛ ቋንቋ በብዛት የተማርነው መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ነው። በወቅቱ የተወሰኑ ሰዎች አማርኛ በደንብ የሚናገሩ በአካባቢው ነበሩ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገባንን ከባድ ቃላት እነርሱን እየጠየቅን እንረዳ ነበር።

## የስብከት መግቢያ

የግል መጽሐፍ ቅዱስ ማግኘት በአስገራሚ ሁኔታ እኛን ለስብከት የሚገፋፋን ሆነ። በእኔ ዕድሜ የነበሩት በወላይታ በጣም ጥቂት ሰዎች የግላቸው የሆነ ትልቅ መጽሐፍ ነበራቸው። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ወደ ወላይትኛ ቋንቋ በመተርጐም መስበክ በመቻሌ መንፈሴ ይረካል።

የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት ሕይወቴን ስለሰወጠው፣ እኔም የሰዎች ሕይወት ይለወጥ ዘንድ ወንጌልን መስበክ እፈልግ ነበር።



# ምዕራፍ ሦስት

## በወላይታ መተከል

ወንጌልን መስበክ በጀመርኩ ጊዜ በዕድሜዬ ወጣት ነበርኩ። በስብሰባ መካከል ቆሜ፣ ወንጌላዊ መሆን እፈልጋለሁ ብዬ አላውቅም፣ እግዚአብሔርም በስሜ ሲጠራኝ አልሰማሁም። ግን ውስጤ በወንጌል ቃል ከተቀላቀለ በኋላ ስብከትን ምርጫዬ አደረግኩኝ፣ማለትም የወንጌሉ ቃል በውስጤ ስር የሰደደበት ወቅት ነበር።

በየትኛውም የወላይታ ክፍል ዓመታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስብሰባ ሳልካፈል እግዚአብሔር ግን አደረገልኝ። እንደ እውነቱ ከሆነ እኔ ወጣት ነበርኩ፣ የምሰብክላቸው ሰዎች ግን ከእኔ በዕድሜ በጣም የሚበልጡኝ ቢሆኑም አልጨነቅም። መልዕክቱ ከእግዚአብሔር ስለሆነ የተሰጠውም ለሁሉም ሰው እንደሆነ አመንኩ። በክርስቶስ እንዳመንኩ ወዲያው ለሕዝብ መናገር ጀምሬአለሁ። ለወላጆቼ ነግሬአለሁ፣ ለወንድሞቼና ለእህቶቼ ነግሬአለሁ፣ ለጐረቤቶቼ ነግሬአለሁ፣ ለሚሰማኝ ሁሉ ነግሬአለሁ።

## መንግሥተ ሰማይ ወይም ሲዖል

በዘመኑ በወላይታ ውስጥ በሕዝቡ አዕምሮ ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ፍርድ ምንም ጥያቄ አይነሳም። ምናልባት ይህ የሆነው በወላይታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ያበረከተችው ውርስ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በወላይታ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወዲህ ከ13ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ቃሉን በምሥጢር ይዛለች። ከሞት በኋላ ፍርድ እንደሚኖር በወላይታ ማንም አይክድም። ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ፍርድ የተነገረው ማስጠንቀቂያ ስለ መንግሥተ ሰማያትና ስለ ሲዖል በቀላሉ እንድንሰብክ አስችሎናል።

በወላይታ ሰዎች እንዲያምኑ እንጋብዛለን፣ የተወሰነ መግለጫችንን ብቻ ሰምተው እንዲደግፉ አንጠይቃቸውም። ማመን ማለት ክርስቶስን መቀበል ማለት ነው፣ ከፍርድ ለመዳን እርሱን ወደ ልብ መጋበዝ ማለት ነው። በኢየሱስ ማመንን ሰዎች አልፈሩም፤ አስቀድሞ የሚያውቁትን እስታወስናቸው፣ ለመኖርና ለመሞት ሁለት መንገዶች እንዳሉም ገለጽንላቸው። አንዱ የፍርሃት መንገድ ሲሆን ወደ ፍርድ የሚመራ ነው። የነፃነት መንገድ ግን ወደ መንግሥተ ሰማይ ይመራል። ከፍርድ ሊያድን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ይህ የዘወትር ስብከቴ ነው። ነገር ግን ስብከትህን ሰምቶ ለማመን የመጀመሪያው ሰው ማን ነው? ብለህ ትጠይቀኝ ይሆናል፣ አላስታውስም!

ለቤተሰቦቼ የእግዚአብሔርን ቃል በሰበኩኝ ጊዜ አባቴ ትኩረት ሰጥቶ ያዳምጠኝ ነበር፣ የእንጀራ እናቴም እንዲሁ። ወንድሞቼና እህቶቼ ሁሉም ሰምተዋል፣ እናም ይህ አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ ለማወቅ ፈልገዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተናገረውን ሁሉ እሺ ተስማምቻለሁ እንዲሉ እንጠይቃቸዋለን። መስማማታቸውን ከገለጹ በኋላ በመጀመሪያ ወንጌላዊው እኔ ሳምን ያለኝን ቃል እነግራቸዋለሁ፣ «እግዚአብሔር ይባርካችሁ»፣ «እግዚአብሔር ይርዳችሁ» ብዬ፣ በኋላም እፀልይላቸዋለሁ። ከዚያም በየሳምንቱ በተወሰኑ ቀናት ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድና ቃሉን በማጥናት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አድገዋል፣ ለአካባቢያቸውም መልካም ምሳሌ ሆነዋል።

እኔ ካመንኩ ከትንሽ ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር ተናግሯል በሚል ርዕስ በወላይታ ቋንቋ የተጻፈውን ትንሽ መጽሔት አግኝቼ ነበር፣ መጽሔቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ስብስብ ነበር።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳነብላቸው ይጠይቁኛል፣ ወዲያውም እሰብክላቸዋለሁ፣ በኢየሱስ እንዲያምኑም እጠይቃቸዋለሁ።

## የስብከት ጥሪ

መስበክ የጀመርኩት ገና በክርስቶስ እንዳመንኩ ነበር። አስቀድሜ ለቤተሰቦቼ ቀጥዬም ለጎረቤቶቼ ሰብኬአለሁ። በዚያን ጊዜ ብዙ ማህበራት በህብረት ይሰበሰቡ ነበርና እኔም ከሌሎች ጋር እየሄድኩ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን እጎበኛቸው ነበር። በአንድ በኩል ለሰዎች ወንጌልን እየሰበክሁ በሌላ በኩል ለአዳዲስ አማኞችም የአማርኛ ፊደል አስተምራቸው ነበር።

በሃያዎቹ ዕድሜዬ አካባቢ በነበርኩ ጊዜ ለቀረው ሕይወቴ የሚበቃኝን የኑሮ ንድፍና ምሳሌነት አካብቻለሁ። በየቀኑ አባቴን ምን መሥራት እንዳለብኝ እጠይቀዋለሁ፣ ሥራው እንዳለቀም ወደ ስብከቴ እስማራለሁ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለስ ስብከት ከተነሳ በሁለት ነገሮች ፍላጎት የለኝም፦ ይኸውም ገንዘብና ዕውቅና ማግኘት አልፈልግም።

ስብከት የጀመርኩት ገንዘብ ስለተከፈለኝ አልነበረም። በዚህ ረገድም የአገልግሎት ሙያዬ ደመወዝ እንዲከፈለኝ ጠይቄ አላውቅም፣ ወይንም ዕውቅና እንዲሰጠኝ በፍፁም አልጠይቅም።

«ወንጌልን ብሰብክ እንኳን የምመካበት የለኝም፣ ግድ ደርሶብኝ ነውና ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ» (1 ቆሮ. 9፥16)።

ወንጌልን ለመስበክ ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበረኝ ማንም አብሮኝ ባይሄድና ባያጅበኝ አልጨነቅም። ብዙውን ጊዜ ለብቻዬ እሄዳለሁ፣ አንዳንዶች ሁልጊዜ



አብረውኝ ሊሄዱ ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን ከእነርሱ ጋራ መሄድ ለእኔ አስፈላጊዬ አልነበረም። እግዚአብሔር ምን ላደርግ እንደፈለገኝ አውቃለሁና ሄጄ እሠራለሁ። በዘመኔ ሁሉ በወላይታ አካባቢ ስዘዋወር ሰባኪ ጓደኛ ፈጽሞ አልነበረኝም፣ ምክንያቱም ሰዎች አብረውኝ ለአገልግሎት እንዲወጡ ከመጠየቅ ይልቅ ራሴ ተንቀሳቅሼ ማገልገልን ስለምመርጥ ነው።

ዘወትር የእግዚአብሔርን ቃል ያዘለውና «እግዚአብሔር ተናግሯል» በሚል ርዕስ ተጽፎ በወላይትኛ የተተረጐመውን ትንሹን መጽሔት ከመጽሐፍ ቅዱሴ ጋር ይዤ እዞር ነበር። የሰዎችን ሕይወት የሚነካውና የሚለውጠው የእኔ ስብከት ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ነው። በምሰብክበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል ጥቅስ አነብባለሁ፣ ከዚያም እስረዳቸዋለሁ።

የእኔ መግለጫ ቃል ምን ጊዜም ተመሳሳይ ነው። ያውም «መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው» የሚለው ነው። ይህ መጽሐፍ ምን እንደሆነ ሰዎች ያላቸው ሀሳብ ምን ይሆን? ማንም አያውቅም! ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው እውነት መሆኑን ልባቸው ነግሯቸዋል።

## ከተለመደው አካባቢ ራቅ ብሎ መሄድ

በወላይታ ውስጥ አካባቢውን ቆላና ደጋ ብለን በሁለት እንከፍለዋለን። እኔ በሁለቱም እካባቢ እየዞርኩ ቃሉን እሰብካለሁ። ጉዞዬን በስተምዕራብ እስከ ጊቤ ወንዝ አሰፋለሁ ያም የኩሎ ኮንታ አውራጃ ነው። አንድ የወላይታ ወንጌላዊ በኩሎ ኮንታ ነበርና እኔ ወደዚያ አልሄድኩም። ያ ቦታ ከቤቴ በእግር የሁለት ቀን መንገድ ነበር።

ከታሪክ እንደምናወዳድረው ከእኛ ከወላይታ አካባቢ ይልቅ በኩሎ ኮንታ የሰይጣን አምልኮት የበዛበት መሆኑን እናውቅ ነበር። እኔ እንደምገምተው በኩሎ ኮንታ ሰዎች ምን ይደርስብን ይሆን በሚል ፍርሃት የሚኖሩ ይመስላሉ።

ምን ጊዜም ከቤቴ ሩቅ ወደሆነው ቦታ ስሄድ ብዙውን ጊዜ ሌሎችን ሰዎች አስከትዬ እሄዳለሁ። አንድ ጊዜ ከወንጌላዊ ኮላ ጋር ለመስበክ ወደ ኮይሻ ሄድን፤ እዚያ ስንደርስ አስቀድመው የተቋቋሙ ማህበራት ነበሩ። ከዚያም ማህበራቱን ጐብኝተን እንደተመለስን አስታውሳለሁ። በየቀኑ ብዙ ርቀት እየተጓዝን ለሚሰሙን ሁሉ ቃሉን እንሰብክ ነበር። በየእሁዱ ደግሞ በአካባቢው ላሉት ቤተክርስቲያኖች ወንጌልን እንሰብክ ነበር።

ሁልጊዜ በየሄድንበት እናድር የነበረው በፀሎት ቤት ሲሆን፣ ክርስቲያኖች ምግብ ስለሚሰጡን ለምግብ ገንዘብ እናወጣም። በዚሁ ሁኔታ ምዕመናን የሥራው ተካፋይ ይሆኑ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ለአገልግሎት በምንዘዋወርበት አካባቢ ከሦስት ሳምንት እስከ ወር ድረስ የምንቆይበት ጊዜም ይገጥመናል።

በሃያዎቹ ዕድሜዬ ውስጥ በነበርኩ ጊዜ በዚህ ዓይነት ሁለትና ሦስት ረዣዥም ጉዞዎች እያደረኩ እሰብክ ነበር:: ያንን ረዥም ጉዞ እንዳስታውስ የሚያደርገኝ ነገር ቢኖር ትልቁን መጽሐፍ ቅዱሴን ተሸክሜ መዞሬ ነው:: መጽሐፍ ቅዱሴን ተሸክሜ መመላለስ በጣም ያስደስተኛል፣ ወዲያውም ሰዎችን ባገኘሁበት እያነበብኩ አስረዳቸዋለሁ::

በየአካባቢው በምዘዋወርበት ጊዜ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ተረድቼ በጥልቀት ለማስተማርና ለመስበክ እፈልግ ነበር::

## አስፈላጊው ቀጠሮ

በእያንዳንዱ አካባቢ በወላይታ ልምድ ያላቸው የሐሰት ነቢያት ነበሩ፣ እነርሱም ቃልቻዎች ተብለው ይጠራሉ:: ክርስቲያኖች ባልሆኑት ሰዎች አካባቢ በጣም የሚከበሩና ሁልጊዜ ከብዙ ሰዎች ስጦታ ስለሚሰበስቡ ሀብታሞች ናቸው::የአገሩንም ሕዝብ ልብ እጅግ የሚስቡ ነበሩ::

ወደ አዲስ አካባቢ ስንደርስ ቃልቻ በዬት እንደሚኖር እንጠይቃለን:: ከዚያም ወደ ቤቱ በመሄድ ቀጠሮ እንይዛለን:: በጣም አስፈላጊ ስለሆነው ነገር ልንነጋገር እንደሄድን እንነግራቸውም ነበር::

እንደ ሌሎች ሰዎች ስጦታ ይዘን ስለማንሄድ ከቃልቻው ምክር ለመጠየቅና ውቃቢውን ለማባበል እንዳልሄድን ያውቃሉ:: በዚሁ መንገድ መልካም አጋጣሚ ፈጥረን ወንጌልን እንሰብክላቸው ነበር፣ ጥቂቶቹም በኢየሱስ አምነዋል::

## ሱዳን ኢንተርየር ሚስዮን ወይም ኤስ ኣይ ኤም

የኤስ ኣይ ኤም. ሚስዮናውያን ወደ ወላይታ የመጡት በ1921 ዓ.ም የመጀመሪያ ወራት አካባቢ ነበር:: የወላይታን ቋንቋ ከተማሩ በኋላ ለስምንት ዓመት ወንጌልን ሰብከዋል:: ከዚያም በሶዶ አካባቢ ኦቶና በሚባለው ቦታ ሆስፒታል ገንብተዋል:: በ1929 ዓ.ም የጣሊያን ኃይል ሚስዮናውያኑ ወላይታን ለቀቀው እንዲወጡ አስገደዳቸው:: የመጨረሻዎቹ ሚስዮናውያን ኢትዮጵያን ለቀው የወጡት ጣሊያን ከገባ ከአንድ ዓመት በኋላ ነበር::

ከነሐሴ 1929-1937 ዓ.ም ድረስ የወላይታ ክርስቲያኖች ከውጪ ሚስዮናውያን ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም:: ነገር ግን ቤተክርስቲያን በወላይታ የበለጠ ያደገችው በነዚያ ዓመታት ውስጥ ነበር::

አንዳንድ የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት በ1934 ዓ.ም ላይ ነበር:: በ1935 ዓ.ም ጥቂቶቹ ወላይታን ጉብኝተው



ተመልሰዋል:: በ1937 ዓ.ም ጥቂቶች ደግሞ ወደ ወላይታ ተመልሰው ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ተፈቅዶላቸዋል::

በ1921 ዓ.ም ወደ ወላይታ ከገቡት የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን መካከል ዋልተርና ማርሴላ ኦህማን የሚባሉ ነበሩ:: ከ1928-1933 ጣሊያን አገራችንን በወረረ ጊዜ እነዚያ ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት በሱዳን ሲሰብኩ ቆይተው ነው:: ወደ ወላይታ ሶዶ የደረሱትም በ1937 ዓ.ም ላይ ነበር:: በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩ ጊዜ ሚስዮናውያኑ እንደ ልጃቸው አድርገው ይንከባከቡኝ ነበር:: በ1934 ዓ.ም አካባቢ ጣሊያን ከተመለሰ በኋላ ወደ ወላይታ ተመልሰው የሠሩት ሚስስ ሴልማ በርግስተን የሚባሉ ሴት ነበሩ::

## የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና

በግንቦት ወር 1937 ዓ.ም የውጪ ሚስዮናውያን ወደ ወላይታ በተመለሱ ጊዜ አስቀድመው ይሠሩ በነበሩበት ንብረታቸው ላይ ተመልሰው እንዲሠፍሩ መንግሥት አልፈቀደላቸውም ነበር:: የኦቶና ሆስፒታል በምን መልኩ እንደሚተዳደር ነገሮችን ለማመቻቸት በጊዜው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ረዥም ጊዜ ወስዶበት ነበር:: ዋልተርና ማርሴላ ኦህማንና ሴልማ በርግስተን ወደ ኦቶና ለመመለስ በሶዶ ከተማ እየኖሩ ይጠባበቁ የነበር ሲሆን፤ ሚስተር ኦህማንን ለመጀመሪያ ያገኘሁትም ያን ጊዜ ነበር::

ሚስተር ኦህማን በእያንዳንዱ ወረዳ ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ማስታወሻ እየጻፉ ሶዶ በሚገኘው ቤታቸው በመሄድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዲያጠኑ ይጋብዙ ነበር:: የዱጉና ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች እኔን መርጠው ሲልኩኝ፣ በደስታ ተሞልቼ ነበር የሄድኩት::

ሶዶ ከእኔ ቤት በእግር ለቀናት የሚያስኬድ ርቀት ቢኖረውም፣ በእግሬ በደስታ እጓዝ ነበር፣ ብዙም ሳይቆይ መኪና መምጣት ጀመረ፣ ለመጀመሪያ ኦህማንንና ሚስዮኑን የተገናኘሁት በዚያን ጊዜ ነበር::

## የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት

የኤስ አይ ኤም ሚስዮን ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር ውል ተፈራርሞ ብዙ ሳይቆይ የውጪ ሚስዮናውያን ኦቶና ወደሚገኘው ወደ ቀድሞ ቤቶቻቸው ተመለሱ:: ኦቶና ከሶዶ በስተሰሜን የግማሽ ሰዓት የእግር መንገድ ነው:: ሚስዮናውያኑ በኦቶና ከተደራጁ በኋላ ሚስተር ኦህማን የሙሉ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት እንደሚከፍቱ አስታወቁ::

ለሁለት ዓመት ጊዜ ኦቶና እንደ ቤቴ ሆነልኝ:: በወላይታ የሚስዮኑን ሥራ በሃላፊነት ይመሩ የነበሩት ሚስተር ኦህማን እንደ አባት ሆኑኝ:: እርሳቸውና

ባለቤታቸው የወላይትኛ ቋንቋ አሳምረው ስለሚናገሩ ከነርሱ ጋር ለመጫወትና ለመቃለድ በጣም ይቀልለኝ ነበር።

ሰባኪ ለመሆን እፈልግ ነበርና ያንን ለመተግበር ደግሞ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መግባት ነበረብኝ። ከቤቱ ወደ ኦቶና ከ7-8 ሰዓት በእግር ያስኬደኛል። እሁድ ከሰዓት በኋላ ከቤት እነሳና በጓደኛዬ ቤት አድራለሁ። ከዚያም ተነስቼ ሰኞ ጧት ወደ ት/ቤት ደርሼ ትምህርቴን እቀጥላለሁ።

በሳምንቱ መጨረሻ ከት/ቤቴ ዓርብ ከሰዓት በኋላ እንነሳለን፣ ከዚያም ሌሊቱን በጓደኛዬ ቤት እናድራለን። ወደ ቤታችንም ቅዳሜ ጧት እንደርሳለን። በኦቶና የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ሲከፈት ተማሪዎች ሙሉ ሳምንት ይማሩ ነበር።

ወደ ትምህርት ቤቱ ከሚገቡት ብዙዎቹ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ነበሩ። ሌሎቹ ወንጌላውያን ሲሆኑ፣ ሌሎቹም መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት ለማወቅ የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው።

ሚስዮኑ ማደሪያ ቤት፣ ኪሽ፣ ደብተሮችና እርሳስ ይሰጠን ነበር። የግላችን የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖረን ይጠበቅብናል። ምግባችንን የምናበስልበት ምጣድና የብረት ድስት የሚሰጠን ሲሆን፣ የማገዶ እንጨት ግን እራሳችን ገዝተን እንጠቀማለን። ምግባችንንም የምንችለው ራሳችን ነበርን። እኔ ምግቤን በየሳምንቱ እየተሸከምኩ እወስዳለሁ። የሚጠበስ በቆሎና፣ ቂጣ ለመጋገር የበቆሎ ዱቄት እወስድ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ጥቂት ተማሪዎች ምግባቸውን ከገበያ ቢገዙም ብዙውን ጊዜ የምንፈልገውን ምግብ እንወስድ የነበረው ከየቤታችን ነው።

ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ለመግባትና ለመማር ካላቸው ዝቅተኛ ፍላጎት የተነሳ አንዳንድ ሰዎች ልዩ ልዩ ምክንያት እያቀረቡ በሳምንት ሦስት ቀን ተከትል ብቻ እየሄዱ ይማሩና በሌሎች ቀናት ግን ሳይመጡ ይቀራሉ።

በጅምሩ ግን እንዲህ አልነበረም። በኦቶና ኤስ አይ ኤም ግቢ ውስጥ ለመጀመሪያ ት/ቤቱ በተከፈተ ጊዜ 100-150 ሰዎች ይመዘገቡ ነበር። በጊዜው ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት አይሳተፉም ነበር።

በማስተማር ሂደት የሚሳተፉት ብዙ ሰዎች ናቸው። ጊዜው ረዥም በመሆኑ ከሚስተር ኦህማን በስተቀር የሌሎቹን ስም ዘንግቻለሁ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውጪ የቀለም ትምህርት ለመከታተል ዕድል ያገኘነው ጥቂቶች ነበርን። የተማርነውም ሂሳብ፣ መጻፍና ማንበብ እንዲሁም አማርኛ ለዋስው ነበር። ከዚህም የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ እንድንረዳ አድርጎናል።



የወላይትኛ ቋንቋ የሚችሉት አስተማሪ ሚስተር ኦህማን ብቻ ነበሩ። አማርኛ ስለማይናገሩና ስለማያነቡ የአማርኛን መጽሐፍ ቅዱስ አይጠቀሙም። እራሳቸው የራሳቸውን የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቀማሉ። በወላይትኛ ም ቋንቋ ያስተምሩናል። እኛም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሳችንን እየተጠቀምን እንማራለን።

ወዲያም ሆነ ወዲህ በተቀላቀሉ ሦስት ቋንቋዎች መካከል አንዳንድ ነገሮችን ለመማር በቅተናል። ሌሎቹ አስተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ያስተምሩን ነበር። ኢትዮጵያውያን አስተማሪዎች ስለመኖራቸው እርግጠኛ አይደለሁም፣ ስማቸውንም ለማስታወስ አልቻልኩም።

## በምሳሌ ማስተማር

የውጪ አገር ሚስዮናውያን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በማስተማር ሲሆን፣ በየአብያተ ክርስቲያናት በብዛት እየተዘዋወሩ ጉብኝት ማድረግ ይወዳሉ። ሚስስ በርገስተን ለወላይታ ለየት ያለ ነገር አድርገዋል። ይኸውም በየቤተክርስቲያን እየተዘዋወሩ ሴቶችን ያስተምሩ ነበር። በ1940 ዓ.ም ሚስስ ማርቲን የሚባሉ ሌላዋ ሴት ለወጣት ልጆች የቀለም ትምህርት ቤት ለመጀመር መጡ።

## የመጀመሪያ የስብከት ጉዞ

በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በነበርኩ ወቅት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ወደ አርሲ ጉዞ አድርጌአለሁ። ያም በክረምቱ ት/ቤት ስለተዘጋልን ነበር፣ የሄድኩትም በሽማግሌዎች ተልኬ ይመስለኛል።

በዚያን ጊዜ የውጪ አገር ሚስዮናውያን ወንጌላውያንን ወደ ሌላ አካባቢ በመላክ አይሳተፉም ነበር። ብዙዎቻችን ወደፈለግንበት ቦታ በፈቃዳችን እንሄዳለን። አንዳንድ ጊዜ ግን ቤተክርስቲያን ጥቂት ገንዘብ ትሰጠናለች። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ያለገንዘብ እየተጓዝን እንለብካለን።

ወደ አርሲ ለመጀመሪያ በሄድኩኝ ጊዜ ምናልባት ለሁለትና ለሦስት ሳምንት የቆየሁ መሰለኝ። የሄድነው አስቀድመው እዚያ የነበሩትን ወንጌላውያን ሀዳሮ እና መና የሚባሉትን ለመጎብኘት ሲሆን፣ እነርሱ እዚያ በአርሲ ለረዥም ጊዜ የኖሩ ናቸው። በዚያን ጊዜ በአርሲ የነበሩት የወላይታ ወንጌላውያን ማላ፣አዴና፣ ቆርጋ የሚባሉ ናቸው። እኛም በወቅቱ ገንዘብ ስላልነበረን በእግራችን ልንጓዝ ተገደድን።

ያኔ እኛ እንሄድበት ወደነበረው የአርሲ ክፍል ምንም መኪና አይገባም ነበር። ቦታው ከሻሸመኔ በጣም የሚርቅ ሲሆን፣ በዚያን ጊዜ ሻሸመኔ

የሚባለውን ስም እንኳን አናውቅም:: አራት ሆነን ገና ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ወጥተን ነበር የሄድነው::

ለሁለተኛ ጊዜ አርሲን ለመጎብኘት ስንሄድ በቡድን ነበርን፣ ምክንያቱም በስፍራው ሆነን እዚያ ያሉትን ወንጌላውያን ለመርዳትና አርሬ በሚባለው ቦታ ቤተክርስቲያንን ለመመሥረት ስላሰብን ነው:: ከጫካ እንጨት እየቆረጥንና እየተሸከምን ፀሎት ቤቱ ሲሠራ ወደታቀደበት ሥፍራ እናጓጉዝ ነበር::

ወደ አርሲ ሦስተኛ ጉዞም አድርጌአለሁ ግን ለአጭር ጉብኝት ብቻ ነበር፤ እኔ በጎበኘሁበት ቦታ ጥቂት የአርሲ ሰዎች ብቻ በኢየሱስ ያምኑ ነበር:: አብዛኛዎቹ አማኞች ከሌላ አካባቢ ማለትም ከከምባታና ከወላይታ መሬት ለማረስ የሄዱ ነበሩ::

ለሙስሊሞች መስበክም ለእኔ አዲስ ነገር ነበር:: በዚያን ጊዜ ስለ እስልምና የማውቀው በጣም ትንሹን ነው:: በተራ እየተነሳን ለምናገኛቸው ሰዎች በቡድን እንሰብክ ነበር:: በአርሲ የምንሰብከው ቃል በወላይታ ከምንሰብከው ጋር ተመሳሳይ ነው:: የባላገር ሰዎች የአማርኛ ቋንቋ ስለማይሰሙ በምንሰብክበት ጊዜ አስተርጓሚ እቁመን ነው:: በጊዜው በአርሲ ከሚገኙት የእስልምና እምነት ተከታዮች ምንም ዓይነት ተቃውሞ አላስነሱብንም:: እንዲሁም የሄድንበት አካባቢ ለሲዳማ ቅርብ ቢሆንም፣ በአርሲ በነበርኩ ጊዜ አንድም የሲዳማ ሰው አልተገናኘሁም ነበር::

## ለመቆየት አለመቻል

አርሲ ለአንዳንድ ወንጌላውያን የተመቸ ቢሆንም፣ ለእኔ ግን አልተመቸኝም:: እግዚአብሔር በአርሲ ቆይቼ እንድሰብክ እንዳልፈለገኝ አወቅሁ:: ስለ ሁኔታው ብዙ ብፀልይበትም፣ በልቤ ግን አርሲ ለአገልግሎቴ የተወሰነልኝ ቦታ አለመሆኑን ተረድቻለሁ::

እግዚአብሔር ወንጌላዊ እንድሆን መፈለጉን አውቅ ነበር፣ ግን የት ቦታ እንደማገለግል አላውቅም፣ ምናልባት ሲዳማ ይሆናል ብዬም አሰብኩኝ::



# ምዕራፍ አራት
# የሲዳማ ሕዝብ

እግዚአብሔር ወንጌላዊ እንድሆን መፈለጉን በተረዳሁ ጊዜ ስለ ሲዳማ ሕዝብ ብዙ የማውቀው ነገር አልነበረም:: ወደ አርሲ ሦስት ጊዜ በመሄድ አገልግዬም ነበር:: ዳሩ ግን በልቤ አርሲ እግዚአብሔር የወሰነልኝ ቦታ አለመሆኑን ተረዳሁ:: ወደ ጋሞ ጐፋም ሄጄ ለመስበክ ጥረት ባደርግም፣ ግቡን የመታ ውጤት ግን አልነበረም::

ሲዳማ ከወላይታ በስተምሥራቅ የሚገኝ የኢትዮጵያ ክፍልና የሲዳማ ሕዝብ መኖሪያ ነው:: ይህ ዞን በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ በአርሲና በባሌ፣ በደቡብ በጌዲኦ የሚዋሰን ነው::

የወላይታና የሲዳማ ሕዝቦች ጦርነት ገጥመው አያውቁም:: ደንቶ በሚባል የእሮብ ገበያ ሁለቱም ወገኖች በሚገበያዩበት ወቅት አልፎ አልፎ የተለመደው የጠጪዎች ረብሻ ከሚከሰት በስተቀር የጎላ ግጭት አልነበረም:: ነገር ግን የወላይታ ሰዎች በሲዳማዎች ላይ ንቀት ያሳዩ ስለነበር፣ ከፍተኛ ጥላቻ እንዲፈጠር ምክንያት ከመሆኑ የተነሳ፣ ሲዳማዎቹ ለመበቀል የወላይታን ንፁሐን ሰዎች ይገድሉ ነበር::

ገዳዩ የሚገድለውን ሰው አያውቀውም ስለዚህ መግደል ከሟቹ ቤተሰብ ጋር ምንም ፀብ የተቀላቀለበት አልነበረም:: ብቀላን ለመቀነስ በሁለቱም ወገኖች መካከል ጠበቅ ያለ የንግድ እንቅስቃሴ ይካሄድ ነበር:: በመልክአ ምድርና በምጣኔ ሀብት የሲዳማና የወላይታ ነጋዴዎች ጐረቤታሞች በመሆናቸው ወደ ሁለቱም ዞኖች እየተዘዋወሩ ያለምንም ጠብ መነገድ ችለው ይገበያያሉ::

በ1940ዎቹ አካባቢ ሰው መግደል የሲዳማ ባህል ሆኖ የኖረ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ይመስገንና በአሁኑ ጊዜ ያ ጐጂ ባህል በሲዳማ ፈጽሞ አይታይም::

## ባሕላዊ ግድያ

በሲዳማ ባህል በድሮ ጊዜ አንድ ወጣት ረዥም መንገድ ተጉዞ ሌላ ሰው ወይም አንበሳ ቢገድል በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ክብር ይሰጠው ነበር:: ሰውን ወይም አራዊትን መግደል መልካም ባይሆንም፣ ያ ባህል ግን በወቅቱ በአገሩ ሽማግሌዎችም ዘንድ ተቀባይነት ነበረው::

በ1940ዎቹ የኢትዮጵያ መንግሥት ባህላዊ ግድያ እንዲቆምና ሕግ እንዲከበር ቢደነግግም፣ በጊዜው የነበሩት የመንግሥት ባለሥልጣኖች

መመሪያቸው የላላ ስለነበር ባህላዊውን ግድያ ለመግታት አልቻሉም፡፡ ይህ ሁኔታ ድርጊቱን የሚፈጽሙትን ሰዎች የበለጠ አጠናክሮአቸዋል፡፡ ገዳዮቹን ለመቅጣት ፖሊስ ምንም ዓይነት እርምጃ እንደማይወስድ ሲገነዘቡ፣ በቡድን እየዘመቱ ርቀው በመሄድ ንፁሐን ሰዎችን እየገደሉ ይመለሱ ነበር፡፡

አደጋ በሚጥሉበት ጊዜ ሙከራቸውን ስኬታማ ለማድረግ ማለትም ቢያንስ አንድ ሰው እንኳን ሳይገድሉ እንዳይመለሱ በጣም ተጠንቅቀው በማድፈጥ ግድያ የሚፈጽሙ ቢሆንም፣ እነዚያ ሰዎች ግን የራሳቸውን ወገንና እንዲሁም ሴቶችንና ልጆችን አይገድሉም፡፡

ለምሳሌ አንድ የወላይታ ነጋዴ ከሲዳማ ነጋዴዎች ጋር የተጐዳኘ እንደሆነ ይገድሉኛል ብሎ አይሰጋም፣ የሚያስጥለው ጓደኛው አብሮት ስለሆነ አይነካውም፡፡ ግድያው በወላይታዎች በኩል ስለማይፈፀም የሲዳማ ጦረኞች የብላቴን ወንዝ ተሻግረው ለመግደል አይሄዱም፡፡ በእርሻ ላይ ያሉትን ሰዎች መግደል መሬትን እንደ መበከል ተደርጐ ስለሚታመን ሰዎችን እያረሱ አይገድሏቸውም፡፡

ግድያው የሚበዛው በቆላማው ጫካ ውስጥ ሲሆን፣ በአካባቢ የሚኀዙ ሰዎች ያለጥንቃቄ አይንቀዋለሉም፡፡ አጥቂዎቹ ሁለትና ሦስት ሆነው በቆላማው አካባቢ ከሳምንት በላይ ወዲያ ወዲህ በመዘዋወር የአደጋ ሰለባ የሚያደርጉትን ሰው ይጠባበቃሉ፡፡ ምግባቸውንና ውሃቸውን ይዘው በመሄድ ዓላማቸውን እስኪያሳኩ ድረስ ለረዥም ጊዜ ወደ ቤታቸው ሳይመለሱ ይቆያሉ፡፡

አጥቂዎቹ ሰውየውን ገድለው ከሰለቡት በኋላ ጮክ ብለው እየፎከሩ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ፣ ይህ የሚያሳየው ወጣቶቹ ያሰቡትን ግድያ ከግብ ማድረሳቸውንና ጉብዝናቸውን ለገጠሩ ሕዝብ ሁሉ ማሳወቃቸው ነበር፡፡ የአካባቢያቸውም ሰዎች ወደ ቤታቸው በመሄድ የእንኳን ደስ አላችሁ ሰላምታ ያቀርቡላቸዋል፡፡

ነገር ግን የወላይታ ሕዝብ ተመሳሳይ ባሕላዊ ልማድ ስለሌለው የሲዳማን ሕዝብ ለመግደል የሚፈጥረው ሁኔታ አልነበረም፡፡ የሲዳማ ሰዎች ለንግዳቸው ወደ ወላይታ ሲሄዱ በወላይታዎቹ ቤት አድረው ተስተናግደው ይመለሳሉ፡፡ የግድያው ተግባር ለሲዳማ ህዝብ ባህላዊ ባህርይ ስለነበረው የወላይታ ሕዝብ የብቀላ እርምጃ አይወስድም ነበር፡፡

## ጥቃቶች!!

ሰዎች ሁልጊዜ በአጉል ቦታና በአጉል ጊዜ የሚዘዋወሩ ከሆነ የጥቃት ሰለባ ከመሆን አያመልጡም፡፡ ከምሥራቃዊው የብላቴ ወንዝ ዳርቻ እስከ ሲዳማ



እርሻማ አካባቢ ድረስ የሦስት ሰዓት ያህል መንገድ በእግር ያስኬዳል፡፡ ገዳዮቹ ጥቃት የሚያደርሱትም በዚያ ቆላማ አካባቢ ነበር፡፡ ከቆላማው አካባቢ ወደ እርሻማው አካባቢ ከተደረሰ ሰላም ይሆናል፡፡ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለው የቆላማው ክፍል 50 ኪሎ ሜትር ያህል ይሸፍናል፡፡

ይህ ባሕላዊ ግድያ የሚፈጸመው ሁልጊዜ አልነበረም፡፡ እያንዳንዱ የሲዳማ ወጣትም ሰውን ለመግደል አይሄድም፡፡ ብዙውን ጊዜ ለወደፊት ሊፈጸም የሚችል ግድያ ወላይታዎቹን አያገኛቸውም፡፡ ወላይታዎች በሲዳማ ቆላማ አካባቢ አቋርጠው ያለመሪና ያለጠባቂ ይሄዳሉ፣ ያለችግርም ይደርሳሉ፡፡

ሲዳማዎች ወላይታዎቹን ይገድሉ የነበሩት በተለይም በሲዳማ ፋንጐ ወደሚባል ገበያ ሲሄዱ ነበር፡፡ የወላይታ ነጋዴዎች ዕቃዎቻቸውን በአካባቢያቸው በዲንቶ ገበያ ከመሸጥ ይልቅ ቡልኮአቸውን ወደ ሲዳማ ወስደው በመሸጥ ከዚያ ቡና በማምጣት ይነግዱ ነበር፡፡

እኔ የወላይታ ሰው ብሆንም፣ ለ50 ዓመት ሙሉ በሲዳማ ውስጥ ስኖር ተጨንቄና ተረብሼ አላውቅም፡፡ ሁሉም የወላይታ ሰው መሆኔን በሚገባ ቢያውቁም በስብከቱ ላይ አንዳች መሰናክል አላጋጠመኝም፡፡

## አሰቃቂ ትዝታ

የሲዳማ ጦረኞች የወላይታን ሰው ከገደሉ በኋላ የተወሰነ የአካል ክፍሉን ወይም ብልቱን ቆርጠው በመውሰድ ለባልንጀሮቻቸውና ለቤተሰባቸው በማሳየት የረዥም ጊዜ ጉዞአቸውን ውጤትና ድል ያረጋግጡላቸዋል፡፡ የቀረውን በድን የወላይታ ነጋዴዎች አሞራ ወይም ጅብ እንዳያጠናቅቀው አንስተው ይቀብሩታል፡፡

ሰዎቹ የሚመጡት ብዙውን ጊዜ ገሶና ድጅኖ የመሳሰሉትን መቆፈሪያዎችና አካፋ ይዘው ሲሆን፣ የማያስደስተውን ሥራ ማለትም በዚያ በአሸዋማና በድንጋያማ መሬት ቆፍረው በመቅበር በመቃብሩም ላይ ድንጋይ በመከመር አሞራና ጅብ እንዳይበላው ያደርጋሉ፡፡ እነዚያ የመንገድ ዳር ቀባሪዎች ለእንግዳው መንገደኛ ቆላማውን አካባቢ ማቋረጥ ለደህንነታቸው አስተማማኝ እንዳልሆነ ይነግራሉ፡፡

## የጦረኛው ክብር

ወጣቶቹ ወደ ቆላማው አካባቢ ተጉዘው አንድ ሰው የመግደላቸውን ማስረጃ ይዘው ከተመለሱ ባልንጀሮቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ታላቅ ግብዣ ያዘጋጁና ገዳዮቹ ጀግና ጦረኞች መሆናቸው ይታወቅላቸዋል ወይም ይረጋገጥላቸዋል፡፡

በማንኛውም ባሕላዊ ሥነ-ሥርዓትና ግብዣ ላይ ልዩ ዕውቅና የተሰጣቸው ባለመብት ይሆናሉ:: በማንኛውም የግብዣ ቦታ ቢሄዱ በታላቅ ክብር ይስተናገዳሉ፣ በቆላማው አካባቢ ንፁህ ደም በማፍሰሳቸው በጀግንነት ይታወቃሉ:: የታወቁ የወላይታ ሰባኪ ወንጌላውያን በነዚያ ጦረኞች ተገድለዋል፣ ከተገደሉትም አንዱ አቶ ታደሰ ወታንጐ ነበሩ::

## ታደሰ ወታንጐ

አቶ ታደሰ ወደ ጌዴኦ ሄደው ወንጌላዊ እንዲሆኑ ከውጪ ሚስዮናውያን በአልበርትና ኤቭሊን ብራንት ተጋብዘው ነበር:: አቶ ታደሰ ከወላይታ ወደ ዲላ ሰብዙ ጊዜ ተመላልሰዋል:: የሚመላለሱትም ሁለትና ሦስት ሆነው በሲዳማ ቆላማ መሬት አካባቢ አቋርጠው ነው::

በተደጋጋሚ ያለምንም ችግር ከመመላለሳቸው የተነሳ በመዘናጋታቸው ይመስለኛል አንድ ቀን በድንገት ጥቃት ደረሰባቸው:: ሰውየው ረዥምና ጠንካራ ነበሩ፤ የሚደርስባቸውን ጥቃት ለመከላከል ብቁ ነኝ ብለው በጉልበታቸው የሚተማመኑ ኃይለኛም ነበሩ:: አንድ ጊዜ ከዲላ ወደ ወላይታ በሲዳማ ቆላማ ምድር አቋርጠው ለመንዝ ወሰኑ:: ሌሎች ሁለት ሰዎች አቶ ተካ እና አቶ ሻኖ የሚባሉ አብረዋቸው ነበሩ::

አንዳንድ የሲዳማ ጦረኞች አስቀድመው በግራር ዛፍ ላይ ወጥተው በመሰለል የሚመጡትን መንገደኞች ይጠባበቁ ነበር:: በቆላማው ምድር መንገደኞቹን ለማጥቃት ወደሚያመቻቸው ቦታ እስኪደርሱ ይከታተሏቸው ነበር:: በኋላም አጥቂዎቹ ደርሰው ተረባርበው ያዟቸውና እጆቻቸውን ወደ ኋላ አስረው አረዱአቸው፣ አጥቂዎቹ አራት ወይም አምስት ይሆኑ ነበር::

እኔ በዚያን ጊዜ አርኬ በሚባል ቦታ ነበርኩ:: ስለነዚያ ሰዎች መሞት ለብዙ ሳምንታት አልሰማሁም ነበር:: አቶ ታደሰ እኔ ከመጣሁበት ከዱጉና ቤተክርስቲያን ስለነበረ ስለ ሁኔታው በጥልቀት ለመረዳት ወደ ወላይታ ተጓዝኩኝ:: እዚያም ስደርስ «ካንተ ጋር ስናወዳድረው ታደሰ ጉልያድን ያክል ነበር:: ሲዳማዎች ጉልያድን የሚያክል ሰው ከገደሉ፣ አንተን ለመግደል ምን ያቅታቸዋል? ምንስ ዋስትና አለህ? እባክህ ወደ ሲዳማ ተመልሰህ አትሂድ አሉኝ»:: ያን ጊዜ አንዳንድ የሲዳማ ሰዎች ክርስቲያኖች ሆነዋል::

ሲዳማዎች ለራሳቸው ሕዝብ ራሳቸው ይሰበኩ:: አንተ ወደ ሲዳማ ሄደህ ለምን ሕይወትህን አደጋ ላይ ትጥላለህ? ብለው የወላይታ ሰዎች ጠየቁኝ::

በተለያዩ መንገዶች እያስረዱኝ ወደ ሲዳማ እንዳልሄድ ብዙ ጥረት አድርገው ጐተጐቱኝ:: በሲዳማ ቆላማ መሬት የሞቱት ከወላይታ አቶ ታደሰ ብቻ አልነበሩም::



## አሞቼ ኡኩሎ

አቶ አሞቼ ኡኩሎ በጋሞ ጐፋ ወንጌላዊ ነበሩ:: ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ከጋሞ ጐፋ አንድ ልጅ ይዘው ወደ ወላይታ ይመለሳሉ:: ከልጁ ቤተሰብ ጋር የነበራቸው ስምምነት ልጃቸውን ወደ ወላይታ ወስደው ት/ቤት እንዲያስገቡት ነበር::

አቶ አሞቼ የዓመት በዓላቸውን አሳልፈው ስአልግሎታቸው ወደ ጋሞ ጐፋ በሚመለሱበት ጊዜ የልጁ ወላጆች እጅግ ተቆጡ:: ልጃችን የት አለ? ምናልባት ገድለኸዋል፣ በአስቸኳይ ሄደህ ካላመጣኸውና መኖሩን ካላረጋገጥክልን እንገድልሃለን አሉት::

ሌላ ምርጫ አልነበራቸውምና አሞቼ ወደ ወላይታ በመሄድ ልጁን ወደ ጋሞ ጐፋ መልሰው ለወላጆቹ ማስረከብ ነበረባቸው:: አቶ አሞቼ ወደ ወላይታ በደረሱ ጊዜ ሌላ ያላሰቡት ትልቅ ችግር ጠበቃቸው:: ጓደኛቸው የነበሩት አቶ መርኪና መጃ በሰሜናዊ ሲዳማ በይርጋለም ተማሪ ነበሩና ልጁን አቶ መርኪና ወደ ይርጋለም ወስደውታል:: እንግዲህ አቶ አሞቼ የነበራቸው ምርጫ ወደ ይርጋለም ተጉዘው ልጁን ወደ ጋሞ ጐፋ መመለስ ነበር :: በደቡባዊው ሲዳማ ቆላማው መሬት ልጁን ይዘው ሲመለሱ የሲዳማ ጦረኞች ሁለቱንም አግልለው ገደሏቸው፣ ጊዜውም 1947 ዓ.ም ነበር::

## ዛቻ

ለሜናዊ ሲዳማ ተስማምቶኝ በተቀመጥኩኝ ጊዜ ሰላም መሆኑን ስለማውቅ በራስ መተማመን በውስጤ ይሰማኝ ነበር:: የቆዩና ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችንም ማወቅ ጀመርኩኝ:: አንድ ጊዜ ብቻ በአቅራቢያዬ የነበሩ ሰዎች ባለቤቴን አፍነው ለመውሰድ ፈልገው ሲያጠቁኝ እንደተዘጋጁ ጭምጭምታ ተሰራጨ:: አንዳንድ ጊዜ እርስ በርሳቸው እየተነጋገሩ ፍርሃት ሊያሳድሩብኝ ይፈልጉ ነበር:: «እርሷ ውብ ነች:: የሚታደጋትም ዘመድ እዚህ የለም፣ ሰውየውን እንግደለውና ሴትየዋን እንውሰዳት:: ማንም የሚጠይቀን የለም» ይባባሉ ነበር::

ይህንን ጭምጭምታ በሰማሁኝ ጊዜ ምንም አልተደናገጥኩም፣ ምክንያቱም በአሳቻ ቦታና በመጥፎ ጊዜ ካላገኙኝ በስተቀር ባለቤቴን አፍነው ለመውሰድ አይገድሉኝም:: በእርግጥ የሲዳማው ደጋማ መሬት በዛፍ የተሸፈነ ስለነበረ ጫካውን ተገን በማድረግ የሚፈልጉትን ለመፈፀም ችግር አልነበረባቸውም::

## ጃላ

«ጃላ» የሚለው ቃል በኢትዮጵያ በብዙ ቋንቋዎች በየትርጉሙ ይታወቃል:: በሲዳሚኛ ጃላ ማለት ወዳጅ ማለት ነው:: ወዳጅ ሲባልም ከተራ ጓደኛ የበለጠ የሚመኩበት፣ የሚያምኑትና የሚተማመኑበት ማለት ነው:: በማንኛውም ጊዜ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ዋጋ የሚከፍል ማለት ነው::

ስወላይታ ነጋዴዎች ወዲያ ወዲህ እየተመላለሱ ያለሥጋት ለመነገድ የሚያስችላቸው ዓይነተኛው መንገድ የሲዳማ ጃላ ወይም ወዳጅ ማበጀት ነበር:: አንድ የወላይታ ነጋዴ ከሲዳማ ወዳጁ ወይም ጃላ ጋር ከሆነ በመንገድ ላይ አጥቂዎቹ ይገድሉኛል ብሎ አይሰጋም::

ጓደኝነታቸውም ሁልጊዜ አጸፋ በመመላለስ የፀና ይሆናል:: ይህም ማለት የሲዳማ ነጋዴዎች ወደ ወላይታ ዲንቶ ገበያ በሚሄዱበት ጊዜ ወላይታዎቹ በቤታቸው ተቀብለው በደንብ አስተናግደው ይሸኙአቸዋል:: ወላይታዎቹም ወደ ሲዳማ ሲመጡ በወዳጆቻቸው ቤት ተመሳሳይ መስተንግዶ ይደረግላቸዋል::

## ቃልቻዎች

የሲዳማና የወላይታ ነጋዴዎች ይነግሩን የነበረው በሲዳማ የነበሩት ሰዎች በቃልቻዎች ሥርዓት የተሳሠሩ መሆናቸውን ነው:: ከወላይታ ይበልጥ በሲዳማ ብዙ ቃልቻዎች እንደነበሩ ይነገራል::

ይህ ሁኔታ ከወላይታ ሰዎች ይበልጥ በሲዳማ በትልቅ ፍርሃት ውስጥ የነበሩትን ሰዎች እንድገናኛቸው አዘጋጅቶኛል:: ከልምድ እንደማውቀው ቃልቻዎች ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችሉ ስለምረዳ ሰዎችን በየቦታው ከፍርሃታቸው ለማስታገስ መቻል ነበረብኝ:: ፍርሃት ሲባል ሰዎች ሰይጣንን እንደሚፈሩ ስለማውቅ ከዚያ ፍርሃት ተላቅቀው በእግዚአብሔር እንዲያምኑ ለመመስከር ምቹ መንገድ ነው::

## ቀብር

ቀብርና ሥርዓቱ አብሮ የሚኖርና የሕዝብን ፍርሃት የሚያንፀባርቅ ከሞት በኋላ የሚጠብቁት ነው:: ስለ ሲዳማ የቀብር ሥርዓት በወላይታ በነበርን ጊዜ ብዙ ሰምተን ነበር:: ከወላይታ ባህላዊ የቀብር ሥርዓት የተለየ ነው::

በሲዳማ ሰው ሲሞት በሁለት የተለያዩ ጊዜያት ይለቀስ ነበር:: የመጀመሪያው ለቅሶ አጭርና ሟቹ ከተቀበረ በኋላ ለ3 ቀን ያህል የሚለቀስ ነው:: የሟቹን ቤተሰብ ማስተዛዘን ይቀጥላል:: ነገር ግን ለሟቹ የቅርብ ዘመዶች ሟቹን ለመጨረሻ የመሰናበቱ ሁኔታ አያበቃም:: ስለዚህም ቤተሰቡ



ለዳግም ለቅሶ ለመዘጋጀት ሰፊ ጊዜ ይፈልጋል:: ታዲያ ለአንድ ወር ካስፈለገም ለሁለት ወር ያህል ይቆያሉ:: ቃልቻው ተስማሚና ምቹ ጊዜ አረጋግጦ ቀኑን ይነግራቸዋል:: ከዚያም ሁለተኛው ለቅሶ በሲዳሚኛ «ዊላ ካይሳኖ» ማለትም ለቅሶ ይቀሰቅሳሉ ተብሎ ይጀመራል:: እየተለቀሰም ከ5 ቀን በላይ ይቆይ ነበር:: ያም የሟቹን መንፈስ ለማወደስና ቤተሰቡንና ዘመዶቹን ለማስደሰት የሚደረግ ነበር::

በዚያም የለቅሶ ቅስቀሳው ሥርዓት በተለያዩ የከበሮ ዓይነቶች ይጀመራል:: ከበሮ ሲመታ በአካባቢው ያለው ሰው ሁሉ ይሰበሰባል:: የከበሮ አመታቱ የለቅሶን ሥርዓት ያደምቃል ወይም ያሳምረዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው:: ስለ ሲዳማ ሕዝብ በጣም የሚያስደንቀኝ ነገር ቢኖር ለመንፈሳዊ ነገር ያላቸው ቅን ፍላጐት ነው:: በወቅቱ አንድ ወይም ሁለት የወላይታ ወንጌላውያን በሲዳማ ይሠሩ እንደነበር አውቃለሁ:: ነገር ግን ከነርሱ ጋር ለመነጋገር ምንም ጥረት አላደረግኩም ነበር::

## ሾንጋ ሳዴቦ

አቶ ሾንጋ የሚባሉ ወንጌላዊ የብላቴን ወንዝ ተሻግረው በሲዳማ ይሰብኩ እንደነበር ሰማሁ:: በሲዳማ ለ20 ዓመታት ያህል ማለትም ከ1939-1959 የሠሩ ቢሆንም፣ በጋራ ተገናኝተን ያደረግነው ነገር አልነበረም::

ወደ ሲዳማ ከመሄዴ በፊት አቶ ሾንጋን አልተገናኘሁም:: ስለ ሲዳማ ጉዞዬም ለማማከር አንዳች ጥረት አላደረግኩም:: እግዚአብሔር እንድሄድ የፈለገኝ መሆኑን ስለማውቅ ሄድኩኝ እንጂ ከማንም ጋር ተቀምጬ አልተመካከርኩም:: ምክንያቱም በጉዳዩ ላይ መነጋገር አስፈላጊ መስሎ ስላልታየኝ ነው:: አቶ ሾንጋ በብዙ በተለያዩ ቦታዎች ይሰብኩ እንደነበር አውቃለሁ:: ወደ ለሜናዊው ሲዳማ ከመሄዴ በፊት እርሳቸው በደቡባዊው ሲዳማ ይኖሩ ነበር:: ስለ እርሳቸው አልግሎት ብዙ መልካም ነገሮች ብሰማም፣ አብሬያቸው ለመሥራት ግን ምንም ዕቅድ አልነበረኝም::

እርሳቸው ደሞዝ ይከፈላቸው ስለነበር መሪዎቹ በሚያዟቸው ቦታ እየኖሩ ያገለግሉ ነበር:: አቶ ሾንጋ በደቡባዊው ሲዳማ ጥቂት አማኞች የነበሩ መሆናቸውን ገልጸው እንደነበር ሰምቼአለሁ::

## የሲዳማ አማኞች

ወደ ሰሜናዊው ሲዳማ ከመሻገሬ አስቀድሞ በዚያ አካባቢ ቢያንስ ሁለት ሰዎች በክርስቶስ አምነው እንደነበር ሰምቻለሁ:: አቶ ብራሞና አቶ ጅፋሮ ይባላሉ:: ከእኔ ጋር ከመገናኘታቸው በፊት እነርሱ በዚያ እኔ በምሠራበት አካባቢ በአገልግሎቱ ተሳታፊ ነበሩ:: በተጨማሪም አኖሌ በሚባለው አካባቢ

አንዳንድ አማኞች እንደሚኖሩ እገምት ነበር:: ሁለተኛ ቃሉ በተሰበከበትና አማኞች ባሉበት ቦታ ለመሄድ ፍላጐት አልነበረኝም::

የእኔ ብቸኛው ምክንያት ወደ ሲዳማ ሄጄ መልካሙን ዜና ምንም ክርስቲያኖች በሌሉበት አካባቢ መስበክና እነርሱም ተመሳሳይ አገልግሎት እንዲያከናውኑ ማበረታታት ነው:: በተጨማሪም በወርሃዊ ስብሰባ በሁሉም አካባቢ የነበርን ሁላችንም እንገናኝና እንተዋወቃለን:: ከሁሉም በላይ ያስጨንቀኝ የነበረው የቋንቋ ችግር ነው::

## ቋንቋ

የሲዳማ ቋንቋ በየቀኑ አብረን በመኖር የምንለማመደው መሆን አለበት:: የቋንቋ ተመራማሪዎች በሲዳማና በወላይታ ቋንቋዎች መካከል አንዳንድ ተመሳሳይ ቃላት አሉ ቢሉም እንኳን እኔና ባለቤቴ ግን አልተቀበልነውም:: ምክንያቱም ተመሳሳይ ቃላት ቢኖሩ ኖሮ ሲዳሚኛን ለመልመድ ብዙ ዓመት አይፈጅብንም ነበር::

ወደ ሲዳማ ከደረስኩ በኋላ ማከናወን ካሉብኝ ዓላማ አንዱ የቋንቋ ጥናት ጉዳይ ነው:: ለመጀመሪያ ወደ ሲዳማ እንደደረስን ሰዎች የሚናገሩት ምን እንደሆነ ፈፅሞ አይገባንም:: የአገሩ ነዋሪዎች በሚነጋገሩበት ጊዜ ሁሉ ነገር ለእኛ እንግዳ ሆኖብን ነበር:: ሁሉንም ለመጀመር በጣም ችግር ነበረብን:: ጓደኛዬ አቶ ዶዳ ሼሎ በሚባል ቦታ ይኖር ስለነበር እዚያ ሄደን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ወደ ሲዳሚኛ በመተርጐም ይረዳኝ ነበር:: ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን ለሕዝብ እናስተላልፍ የነበረው በዚሁ መልክ ሲሆን ጌታም ከጠበቅነው በላይ እኛንና ሕዝቡን ይባርክ ነበር::

## ቋንቋና ሴቶች

ከእኔ ይበልጥ ባለቤቴ ለመግባባት በጣም ችግር ነበረባት:: እንደ እኔ ቋንቋውን ለማወቅ የሚገፋፉት አጋጣሚ አልነበራትም:: እነሰም በዛም ትንሽ የምንሞክረው አማርኛ በአስደናቂ ሁኔታ ለመግባባት ረድቶናል::

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የአማርኛ ቋንቋ ይችሉ ነበር:: በአንድ ቦታ በምንሰብክበት ወቅት የሚያስተረጉምልንን አንድ ወይም ሁለት ሰው በምንፈልግበት ጊዜ ሲተረጉሙልን እኛ የምንለውን ያስተላልፉ ወይም ሌላ ቃል ይጨምሩ ምንም አይገባንም::

ነገር ግን የጳውሎስ እናት ማለትም ባለቤቴ ወደ ገበያ ለመሄድ የማፈር ስሜት ነበረባት:: ምክንያቱም በገበያው ቋንቋ ባለመቻልዋ ሴቶች ስለሚቀልዱባት ነው:: በለኩ አጠገብ ወደሚገኘው ወደ ይርባ ገበያ ስትሄድ ለመገበያያ በአማርኛ ቋንቋ ስትጠቀም ወደ ሼሎ ገበያ ስትሄድ ደግሞ



በወላይትኛ ቋንቋ ትገበያያለች:: ሼሎ ፤የሲዳማ ፣የወላይታና የጉጂ ጎሳዎች ያሉበት ቦታ ነው:: በሌሎች ቀናት ከጐረቤቶቿ ጋር ትገናኛለች፣ እነርሱም ይቀልዱባታል:: ወደ ጐረቤቶቿ ሄዳ ጐመን እንዲሰጧት ብትፈልግ የጐመኑን ቅጠል እያሳየቻቸው ትጠይቃቸው ነበር:: እዩዋት! ጐመን ስጡኝ ማለቷ ነው!ይሉና እሺ ውሰጂ ይሏት ነበር:: ቀስ በቀስ ባሕላቸውንም ቋንቋቸውንም ለመድንና ለሜናዊ ሲዳማ ቤታችን ሆነልን::

# ምዕራፍ አምስት

# ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ መሻገር

## የእግዚአብሔር ስጦታ

እንደ እኔ ለአገልግሎት የተሰጠች የትዳር ጓደኛ እንደምታስፈልገኝ ከእኔ የተሻለ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር:: እኔ ራሴ ባለቤቴን የመረጥኳት መስሎኝ ነበር፣ ነገር ግን ወደኋላ ሳስብ በትክክል እግዚአብሔር ራሱ ነበር የመረጠልኝ::

እግዚአብሔር ባለቤቴን ለአገልግሎት አዘጋጅቷታል:: በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ከእኔ የተሻለ ተግባር አከናውናለች፣ ብዙ ጊዜ ታበረታታኛለች፣ በሰዎች ዘንድ ተስፋ በማጣበት ጊዜ ለእርዳታው ወደ እግዚአብሔር እንድመለከት ትነግረኛለች፣ በምከፋበትም ጊዜ ታጽናናኛለች ስለዚህ የሁል ጊዜ ረዳቴ ነች፣በምንም ዓይነት አስቸጋሪ ነገር ውስጥ ተስፋ መቁረጥ እና ማስቆረጥ አታውቅም::

ልብስ እጣሁ ብላ አትማረርም፣ ወይም እንደ ሌሎቹ ልልበስ አትልም:: ብዙውን ጊዜ «እግዚአብሔር በእውነት ይወደናል» ትላለች ለምን ብዬ ስጠይቃት «ምክንያቱም እግዚአብሔር ወደ ሲዳማ ሲጠራን የሁለታችንም ወላጆች ሞተዋል:- የእኔ ወላጆች በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ በአንድ ቦታ በቅርባቸው ሆኜ መንከባከብ ይኖርብኝ ነበር» አለችኝ:: ባለቤቴ ሁልጊዜ የወላጆቻችንን አለመኖር ስጦታ ነው ብላ ትተረጉማለች፣ ከሃላፊነት ነፃ አድርጐናልም ትላለች::

## ቤተሰቦቿ

ባለቤቴ ለወላጆቿ ብቸኛ ልጅ ስትሆን አባቷ አማኝ ያልነበሩ ተሳዳቢና ባለቤታቸውን የሚደበድቡ ነበሩ:: በአንድ አጋጣሚ ባለቤታቸውን በመሬት ጥለዋቸው በክንዳቸው ክፉኛ ይመቱአቸዋል:: እጅግ በጣም ከመጐዳታቸው የተነሳ ከዚያ ጥቃት በኋላ አላገገሙም ጥቂት ጊዜ ቆይተው እኛ ከመጋባታችን

በፊት ሞቱ:: የባለቤቴ አባት ግን በድንገት ታመው ከባለቤታቸው እንኳን ቀድመው ሞተዋል::

እናቷ ከመሞታቸው በፊት ለወደፊት ባለቤቴ ፍላጐቴን ገለጽኩላት:: ወንጌላዊ መሆኔን እናቷ ያውቃሉ:: ራሳቸው ክርስቲያን ቢሆኑም እንኳን ልጃቸው ለጥያቄዬ መልስ እንዳትሰጠኝ ለማሰናከል ይጥሩ ነበር:: አንድ ቀን ለልጃቸው «እርሱ እንደሆነ እርሻውን አያርስም፣ ከቦታ ወደ ቦታ ሲዘዋወር ነው የሚውለው፣ ስለዚህም ደሃ ሆነሽ ትኖሪያለሽ :: ከእርሱ ጋር እንድትገናኚ አልፈልግም ብለው» ነገሯት::

የወደፊቷ ባለቤቴ ግን እግዚአብሔርን ትወዳለች፣ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ፍላጐቴ ወንጌልን መስበክ ብቻ መሆኑን ታውቃለች:: ያንንም በተግባር አረጋግጣለች:: ካመነችበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔርን ለማገልገል ትፈልግ ነበር:: በኢትዮጵያ ለሴቶች ያንን ማድረግ ቀላል አልነበረም:: ግን ብዙ ትርፍ ጊዜዋን በቤተክርስቲያን ታሳልፋለች:: በኳየር ዘማሪ ከመሆኗም በላይ እንግዶችን ለመቀበል ምንጊዜም ቀዳሚ ትሆናለች እንጂ ወደኋላ አትልም:: የእንግዶችን እግር ማጠብ፣ ምግብና የሚጠጣ ነገሮችን ማቅረብ የዘወትር ተግባሯ ነው::

እናቷ በጣም መታመማቸውን በተረዱና ቶሎ እንደሚሞቱ ባወቁ ጊዜ ባህርያቸው ተለወጠ ልጃቸውን እንዲህ አሏት:-

«እኔ ከሞትኩኝ በኋላ የትም እንዳትሄጂ፣ ነገር ግን እህቴ ቤት ሂጂና ከእነርሱ ዘንድ ተቀመጪ፣ ከማያምኑትም ጋር አትገናኚ፣ ከክርስቲያኖች ጋር ሁኚና ክርስቲያን የሆነ ሰውን አግቢ አሏት::

እናቷ ከሞቱ በኋላ ብዙ ዘመዶችዋ ከነርሱ ጋር እንድትቀመጥ እየገፋፉ ለእርሻቸው ተጨማሪ ሰው ቢፈልጉም ሃሳባቸውን ውድቅ አድርጋ በአጎቷ በአዴ ዘንድ ለመኖር ሄደች::

## እግዚአብሔር አንድ አደረገን

ወላጆቼ በቆላና በደጋ የእርሻ መሬት ነበራቸው:: ወደ ደጋው የእርሻ መሬታችን ለማረስ በምሄድበት ጊዜ ጎደኞቻችን ከሆኑት ከአዴ ቤተሰብ ዘንድ እቆያለሁ:: ይህ ሰው የባለቤቴ አጎት ነው::

የወደፊት ባለቤቴ ወላጆች ከሞቱ ጀምሮ አዴ /አጎቷ/ እንደ አባት ባለቤቱም ከእናትና ከአክስት የበለጠ ይንከባከቧታል:: እኔም በቤታቸው እቆይ ስለነበረ በደንብ ላውቃት ችያለሁ:: እርስ በርሳችን የተፋቀርን መሆናችንን ስረዳ እንዳገባት ነገሮችን እንዲያመቻችልኝ አዴን ጠየቅኩት::



አጐቷም እርሷን መጠየቅ ነበረበት:: በ1930ዎቹ አካባቢ በወላይታ ባሕል ሴትን ላግባሽ ብሎ መጠየቅ እንደ ነውር ይቆጠር ነበር:: ነገር ግን በቤተሰብ ውሳኔ ይፈፀም ስለነበር ነው እኔም ለአጐቷ ያሳወቅሁት:: ከዚያም የዱጉና አፋን ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋብቻችንን እንዲያፀድቁልን አሳወቅኩኝ:: ሽማግሌዎቹም ወደ አቶ አዴ ሄደው ጉዳዩን አጫወቱት:: የልጅቷ ሃላፊና አሳዳጊ በመሆኑ ልጅቷን ሲያነጋግር ልታገባኝ የተስማማች መሆኗን ገለፀችለት::

ቀጥለውም ሽማግሌዎቹ የሠርጉን ዝርዝር ሁኔታ አስተካከሉልን:: በዚያን ጊዜ የወላይታ ቤተክርስቲያን ለጋብቻ የሚያመቻቹት በዚሁ ዓይነት ነበር:: ባለቤቴ ልታገባኝ የተስማማች መሆኗን አማኞች ያልሆኑት ሰዎች በሰሙ ጊዜ ጠልፈው ሊያገቧት መነጋገር ጀመሩ:: በዘመኑ ለጋብቻ የደረሰችዋን ልጃገረድ ጠልፈው ካገቧትና አብረው መኖር ከጀመሩ በኋላ ወደ ወላጆችዋ ሽማግሌ ልኮ መስማማት ተቀባይነት ያለውና የተለመደ ነበር::

ይህንን ጉምጉምታ በሰማን ጊዜ ከቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ተነጋግረን ቀን ቀጠሮ ተያዘና ሠርጉ በምሥጢር እንዲደረግ ተወሰነ፣ ከተጋባን በኋላ ስለ ጥልፊያ የሚያሰጋን ነገር አልነበረም:: ያገባችዋን ሴት መጥለፍ በባህሉ የተወገዘ ነው::

አንድ ቀን በአራት ሰዓት ወደ ቤተክርስቲያን ታጅባ መጣችና የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሕግ ሰጡን:: ያም የጋብቻን ሥርዓት አስፈፀሙልን:: እኛም ባልና ሚስት ሆንን:: እግዚአብሔርንም ለማገልገል በቃሉ ተሳሰርን:: እግዚአብሔር ይመስገን!

## ወደ ሲዳማ ማምራት

መንፈስ ቅዱስ ወደ ሲዳማ እንደመራኝ አምናለሁ:: የትም ይሁን ወደ አንድ ቦታ ሄጄ ወንጌልን ለመስበክ ፈቃደኛና ዝግጁ ነኝ:: ወደ ጋሞ ጐፋ ለመሄድ አንድ ጊዜ ሃሳብ ነበረኝ:: ብዙ ሌላ ቦታዎችም ሞክሬ ነበር:: በእያንዳንዱ ጊዜ በሩ የተዘጋ ሆኖብኛል:: እነዚያ ቦታዎች ለእኔ የሚሆኑ እንዳልነበሩ አውቃለሁ:: ነገር ግን ወደ ሲዳማ ለመሄድ ባሰብኩኝ ጊዜ እግዚአብሔር መንገድ ከፍቶልኛል::

ወደ ሲዳማ ለመሄድ በመዘጋጀት ላይ በነበርኩ ጊዜ አባቴ ሞተብኝ:: ከሞተ በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ዓመት ነበር ወደ ሲዳማ ያቀናሁት:: በተመሳሳይ ጊዜ የቤተሰቤን ማሳ በማረስ ብዙ ጊዜዬን በስብከት አገልግሎት አሳልፋለሁ:: በነዚያ ዓመታት በወላይታ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተመሥርተዋል:: አሁንም ቢሆን ሰዎች በጌታ ያላመኑበት ብዙ ቦታዎች ይገኛሉ:: ስለዚህ በየሄድንበት ቦታ ሁሉ ወንጌልን እንሰብካለን::

በራሴ ቋንቋ ለወላይታ ሕዝብ ቃሉን መስበክ በጣም እደሰታለሁ፡፡ ቢሆንም እግዚአብሔር ከዚያ እንዲሄድ መፈለጉን አውቅ ነበር፡፡

## ሰማያዊ ጥሪ

እነዚህ ወንጌላውያን እንዳሉት ይህ መልዕክት በጣም አስፈላጊ ከሆነ በሚቻለኝ ሁሉ ለብዙ ሕዝብ መንገር አለብኝ ብዬ ያሰብኩት ወንጌልን ለመጀመሪያ በሰማሁበት ጊዜ ነበር፡፡

በክርስቶስ ባመንኩኝ ጊዜ ለሌሎች ሰዎች ይህንን የወንጌል እውነት ማስተላለፍ እንዳለብኝ በውስጤ ይሰማኝ ነበር፡፡ የእውነትን ቃል መስማት ለሚፈልጉት ለመንገር የመልክአ ምድር አቀጣጫ ለእኔ አስፈላጊዬ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር በትክክል ወደ ሲዳማ መርቶኛል፡፡ መቼ እንደምሄድ ግን አላውቅም ነበር፡፡ መቼስ ሁሉም ነገር በአንድ ጊዜ አይከናወንም፡፡ ነገር ግን ወደ ሲዳማ ለመሄድ የነበረኝን ከፍተኛ ፍላጎት ጊዜውን ጠብቆ እግዚአብሔር በሕይወቴ ፈፅሞልኛል፡፡

ሆኖም ግን የማውቀው ነገር ቢኖር ወደ ሲዳማ መሄድ እንደነበረብኝና ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን ለሕዝቡ መንገር ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ወደ ሌላ አካባቢ በመሄድ ወንጌልን ሰምተው ለማያውቁት ሰዎች መንገር እንደሚገባኝ ለሌሎች ሰዎች ማሳወቅ አልፈልግም፡፡ ከ50 ዓመት በላይ የአገልግሎት ዘመኔ እዚያ ሄጄ ልሰበክ? እዚህና እዚያ እንድሄድ ትፈቅድልኛለህ? በተመሳሳዩም ከመሄዴ በፊት የሆነ ሰው በገንዘብ እስኪደገመኝ ድረስ የመጠበቁ ነገር በእኔ ሕይወት ተከስቶ አያውቅም፡፡

ቃሉን ለመስበክ የትም ቦታ ስሄድ ማንንም የገንዘብ ድጐማ ጠይቄ አላውቅም፡፡ በብዙ የተለያዩ ቦታዎች ያሉ ሰዎች የሚረዱ ናቸው፡፡ የሚረዱት ግን እግዚአብሔር ስለሚያንቀሳቅሳቸው ነው እንጂ እኔ ስለጠየኳቸው አይደለም፡፡ ለእግዚአብሔር ታማኞች ከሆንን ለእኛ የሚያስፈልገንን ሁሉ ለማሟላት እግዚአብሔር የበለጠ ታማኝ መሆኑን አውቃለሁ፡፡

በእግዚአብሔር ፊት ሁሉን ካስቀመጥኩ ሁሉ ነገር በእርሱ እንደሚሟላልኝ እገነዘብ ዘንድ እግዚአብሔር ጽኑ እምነት ሰጥቶኛል፡፡ ሌሎች ወንጌላውያንና ሚስዮናውያን የራሳቸውን አገልግሎት በተለየ መንገድ ይሸከማሉ፡፡ የትም ይሂዱ በአገልግሎታቸው ገንዘብን እንዴት ያግኙ እኔን በፍፁም አይመለከተኝም፡፡ በመወዳደርም አንሠራም፡፡ ሌሎች የፈለጉትን ቢያደርጉ እኔም የእውነትን ቃል ወዳልሰሙት ሰዎች ሄጄ የወንጌልን እውነት እመሰክር ነበር፡፡ ገንዘብንና ሌሎች የሚያስፈልጉኝን ነገሮች እግዚአብሔር እንደሚያቀርብልኝ ተማምኜአለሁ፡፡ ከ50 ዓመት በላይ እርሱ ሁሉን አድርጐልኛል፣ እያደረገልኝም ነው፡፡



ወንጌላዊ እንደማልሆን መንፈስ ቅዱስ ነግሮኝ አያውቅም፡፡ በታሪኬ ደጋግሜ እንደገለጽኩት የወንጌልን ዜና ላልሰሙት እንድሰብክ ያስገደደኝ የእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ ነው፡፡ እንጂ የወንጌልን ስብከት እንዳቆም እና ጥሩ የገንዘብ በረከት ምንጭ አጠገብ እንድቀመጥ ልቤን አነሳስቶኝ አያውቅም፡፡ ስለዚህ እኛም ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር እንዲህ እንላለን፣ «እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን» (2 ቆሮ. 5÷20)፡፡

## መሄድና መቆየት

ወደ ሲዳማ ለመሄድ ስወስን ለረዥምም ጊዜ የመኖር ውሳኔዬ መሆኑን አውቅ ነበር፡፡ ብዙ ወንጌላውያን ከወላይታ ሄደው ስብከታቸውን አከናውነው ወደ ወላይታ ይመለሱ እንደነበር አውቃለሁ፡፡ የእኔ ውሳኔ ግን እንደዚያ ዓይነት አልነበረም፡፡ ወደምሄድበት አንዴ ከሄድኩ መክፈል የሚገባኝን ዋጋ እየከፈልኩ ቀሪ ሕይወቴን እዚያ ለማሳለፍ ወስኜ ነበር፡፡

ነገር ግን ወደ ሲዳማ ለመድረስ ከተግባሩ ይልቅ መናገሩ ይቀላል፡፡ እየሄዱ መመለስ በጊዜው እዚያ ከመኖር የበለጠ አደጋ ነበረው፡፡ ምክንያቱም ረዥም መንገድ መጓዝ አስተማማኝ አልነበረም፡፡ ለዝናቸው ብለው ከሚገድሉ ጀብደኞች መጠንቀቅ ያስፈልግ ነበር፡፡

የወላይታ ሰዎች ደግመው ደጋግመው የሚናገሩት ታሪክ ቢኖር በመንገድ ላይ ሕይወታቸውን ስላጡት ሰዎች ነው፡፡ ይህም ማለት ሁል ጊዜ በመንገድ ላይ ጦርነት ያጋጥማል ማለት አይደለም፡፡ በመልካም ቦታና ጊዜ የሲዳማና የወላይታ ሰዎች በሰላም የሚኖሩ ናቸው፡፡ አደገኛ የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው? ቢባል፣ የሲዳማ ባሕል በክፉል የወላይታን ሰዎች ሕይወት ለብዙ ዓመት ሁለት ወንጌላውያንን ጨምሮ ሲቀጥፍ የኖረ ስለነበረ ነው፡፡

## የሰላም መግቢያ

ለንግድ ሥራ በወላይታና በሲዳማ ድንበር ማቋረጥ የተለመደ ነው፡፡ የወላይታ ሰዎች ከሲዳማ እንዲሁም የሲዳማ ሰዎች ከወላይታ የሚፈልጓቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡

በመጀመሪያ ምዕራፍ እንደገለጽኩት የወላይታ ሰዎች ለንግድ ወደ ሲዳማ ክልል ሲንቀሳቀሱ የሲዳማን /ጃላ/ የልብ ወዳጅ ማበጀት ይገባቸዋል፡፡ ይህ ሰው በትክክል የሚተማመኑበትና ለማንኛውም ነገር የሚጋፈጥለት እውነተኛ ጓደኛ ነው፡፡ የሲዳማ ጉበኞች የራሳቸውን የሲዳማን ሰው ከወላይታዎቹ ጋር ሲሄድ በፍፁም አይገድሉትም፡፡

የልብ ወዳጅ የሚሆነውን የሲዳማ ሰው እግዚአብሔር እንዲሰጠኝና፣ በመንገድ ይገድሉኛል ብዬ ሳልሰጋ እንድሄድ ተግቼ እፀልይ ነበር።

## የዲንቶ ገበያ

የዲንቶ ገበያ ከብላቴ ወንዝ ማዶ በወላይታ በኩል የሚቆም ትልቅ ገበያ ሲሆን፣ የሲዳማና የወላይታ ሰዎች የሚገበያዩበት ነው። ገበያው ከእኔ መኖሪያ ብዙ የማይርቅ ሲሆን፣ ብዙ ሲዳማዎች ወደዚህ ገበያ እየመጡ የሚነግዱ መሆናቸውን አውቅ ነበር።

ሲዳማዎች ትልቁን ማርያ ትሬዛ ይባል የነበረውን የመገበያያ ገንዘብ በማምጣት ከወላይታ ጊደሮችና የወላይታ ሸማኔዎች በመሥራት የሚታወቁበትን ቡልኮ ገዝተው ይመለሳሉ። የሲዳማ ወይና ደጋማው አካባቢ ቡና በማምረት ይታወቃል። ስለዚህ ሰዎች ቡናቸውን እየሸጡ ገንዘብ የሚያገኙ ሲሆን፣ የቡልኮ ነጋዴዎችም ገዝተው በመውሰድ ይሸጣሉ።

ብዙ የሲዳማ ነጋዴዎች ወደ ዲንቶ ገበያ ሲመጡ ሌሊቱን በወላይታዎቹ ወዳጆቻቸው ቤት እያደሩ በነጋታው ወደ ሲዳማ ጉዞ ያደርጋሉ። ከደጋው ሲዳማ ወደ ዲንቶ ገበያ ደርሶ መልስ ለብዙዎቹ አራትና አምስት ቀን ይፈጅባቸዋል። እኔም ለረዥም ጊዜ ወደ ሲዳማ ለመሄድ እየተዘጋጀሁ እፀልይ ነበር። የምሄደውም ለንግድ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ነው፤ እናም የሚወስደኝን አንድ ወዳጅ ነጋዴ እፈልግ ነበር። ታዲያ በግሌ የወላይታንም ሆነ የሲዳማን ነጋዴዎች አንዳቸውንም አላውቅም።

እየፀለይኩ በነበርኩ ጊዜ አራት የሲዳማ ነጋዴዎች ሁልጊዜ እየመጡ በአንዱ ወላይታ ወዳጃቸው ቤት እያረፉ ይመለሱ እንደነበር አስተዋልኩ። ምናልባት በዚህ አጋጣሚ መጠቀም አለብኝ አልኩኝ፤ አብሬአቸውም እንደምሄድ ባሳምናቸውና እንደሚወስዱኝ ከፈቀዱልኝ አብሬአቸው ሄጄ በሲዳማ የማረፊያ ቦታዬን እመሠርታለሁ ብዬ ገመትኩኝ። ሲሆን የሚችለውንም መከታተል ጀመርኩ። ለሃላፊዎች አመልክቶ በቤተክርስቲያን ዕውቅና የሚደረግ የስብከት ጉዞ ዓይነት ለእኔ ፍላጐቴ አልነበረም።

## የገበያ ወንጌላዊነት

ምንም እንኳ በዲንቶ ገበያ ብዙ የሲዳማን ሰዎች ብገናኝም ገበያ ለስብከት አመቺ ቦታ አይደለም። በገበያው ሰዓት ሰዎች እየተገበያዩ ጆሮአቸውን ወደ ስብከት አይመልሱም። ምንም እንኳ በገበያ ለብዙ ሰዎች መናገር ብችልም፣ በሚገባ መስበክ ግን አልቻልኩም ነበር።

በተለይም ገበያ ከማይመጡት ቤተሰቦቻቸው ጋር ልገናኝ አልቻልኩም። በወላይታም ሆነ በሲዳማ የገበያው ወንጌላዊነት ጥሩ ውጤት አያስገኝም።



ወንጌልን ገበያ ውስጥ ማሰራጨት ውጤታማ ያልሆነበት ምክንያት የሰዎች ልብ ለንግድ የተሰጠ በመሆኑ ነው።

## ዶዳን መገናኘት

ዶዳና እኔ የረዥም ጊዜ ወዳጆች ሆነን ቆይተናል። ወንጌልን ለመስበክ ስለነበረን ምኞት ሃሳብ ለሃሳብ እንለዋወጥ ነበር፤ አብረንም በወላይታ አካባቢ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ተዘዋውረናል። ዘመዳሞችም አልነበርንም፣ እንዲያውም በዱጉና ፋንጎ ከተለያዩ ቤተክርስቲያኖች ነበር የወጣነው። የእኔ አፋ ሲሆን የእርሱ ደግሞ ዋሪዛ ይባላል። ነገር ግን ሁለታችንም ቃሉን ለመስበክ ጽኑ ምኞት ስለነበረን አብረን እየሄድን እንሰብክ ነበር። ጥሩ ጓደኞች ለመሆን የበቃነውም በዚሁ ምክንያት ነው።

## ነፃ ወንጌላዊነት

እኔና ዶዳ ለበርካታ ጊዜያቶች በገጠሩ ወላይታ አካባቢ እየተዘዋወርን ወንጌልን ስንሰብክ ሌሎች አማኞች ምንም አይሉንም። የምናመልክበት ቤተክርስቲያን ማህበርም ወንጌላዊነታችንን ብቻ የሚያውቀው ሲሆን፣ ሰዎች በየተሰበሰቡበት ሄደን የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ በጣም ያስደስተናል።

ወዴት እንደምንሄድና በምንሄድበትም ቦታ ምን እንደምንሠራ ለማንም አንናገርም፣ የማንንም ፍቃድ አንጠይቅም። እንሄዳለን እንሰብካለን በቃ! በእግዚአብሔር እንደተላክን ሆነን እንደሚሰማን ሀሳብ እንለዋወጥ ነበር።

ኢየሱስም ዳግመኛ «ሰላም ለእናንተ ይሁን አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» (ዮሐ. 20÷21) አለ።

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ይዘን ለስብከት በምንወጣበት ጊዜ ባልተለመደ ሁኔታ ወደ አካባቢው ማህበራት እንሄዳለን። የሁላችንም ስብከት በህብረተሰብ መካከል እንጂ በየፀሎት ቤት አልነበረም። ስለዚህም በየቤተክርስቲያኑና በእኛ ስብከት መካከል ምንም ፋክክር አልነበረም። እኛ የምንሰብከው ላላመኑት ሰዎች ሲሆን፣ ያንን ለማድረግ የቤተ ክርስቲያንን ፍቃድ አንጠይቅም።

## መፀለይ፣ መስበክና ማመስገን

ለስብከት በምንወጣበት ጊዜ የቤተክርስቲያናችንን ሰዎች እንዲፀልዩልን እንጠይቃለን። በምንመለስበትም ጊዜ በአገልግሎታችን እግዚአብሔር ምን እንደሠራ እንነግራቸዋለን። ስብከታችንን ለመጀመር በጣም ብዙ ርቀን አንሄድም። የቤተክርስቲያን አባሎች ያገለገልንበትን አካባቢና ሰዎቹን ስለሚያውቁ ማንን እንደተገናኘን፣ እንዴት እንደሰበክንና ምንስ ውጤት እንደተገኘ እንነግራቸዋለን።

ከዚያም እግዚአብሔርን ለማመስገንና መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ስለሠራው ሥራ ሰዎች ጌታን እንዲያመሰግኑ እንጋብዛለን። እኔ ወጣት በነበርኩ ጊዜ ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር የሚሰበክ ስብከት ብዙ ሰዎች የሚለማመዱበት ነበር። ሴቶችም ወንዶችም መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እየያዙ ሁለትና ሦስት አንዳንዴም ለየብቻቸው እየሆኑ በመሄድ የሚሰብኩላቸውን ሰዎች ይፈልጋሉ። ያም የክርስቲያኖች የየዕለት ተግባር ነበር።

## ሕልም መለዋወጥ

አንድ ቀን ለዶዳ እንዲህ አልኩት፡- ለሲዳማ ሕዝብ ለመስበክ ወደ ሲዳማ መሄዴ ነው፤ አንዳንድ የሲዳማ ነጋዴዎች እየመጡ በጓደኛህ ቤት እያደሩ እንደሚመለሱ ተገንዝቤአለሁ፤በሚቀጥለው ጊዜ እነዚያ ነጋዴዎች ሲመለሱ እንድታስተዋውቀኝ እፈልጋለሁ፣ የብላቴን ወንዝ አብሬአቸው ተሻግሬ ወደ ሲዳማ ለመሄድ እችል እንደሆነ እጠይቃቸዋለሁ፤ የእግዚአብሔርንም ቃል ለሲዳማ ሕዝብ እሰብካለሁ አልኩት።

ለእቅዴ ዶዳ ምን መልስ እንደሚሰጠኝ እርግጠኛ አልነበርኩም። ከእኔ ጋር ለመሄድ ይወስናል ብዬ ለአፍታም አላሰብኩም ዶዳ ግን «ትልቅ ሃሳብ ነው፤ እኔም አብሬህ ለመሄድ እፈልጋለሁና እንሂድ ሲለኝ» ወዳጃዊ አድናቆት ያዘኝ። አብሮኝ ለመሄድ በመፈለጉም ደስ አለኝ። እንደ እኔ ግን ወንጌላዊ ሆኖ ለመሄድ የተቃጠለ ጽኑ እምነት እንዳልነበረው አውቅ ነበር። ቢሆንም ለጊዜው ምንም አይደለም ብዬ ወሰንኩ። ምክንያቱም ለእርሱ ጉዞው የስብከት ሲሆን፣ ለእኔ ግን በጠቅላላው ሕይወቴን የምለውጥበት ስለነበር ነው።

## ወደ ሲዳማ

ጥር 3 ቀን 1943 ዓ.ም ለመጀመሪያ ከወላይታ ወደ ሲዳማ ለአገልግሎት ጉዞ አደረኩ። በምሄድበት ጊዜ በጫካው ውስጥ ለብቻዬ እየሄድኩ በውስጤ ግን ሲያገኙኝ እንደሚገድሉኝ አስብ ነበር።

በምሄድበት ቦታ ለእኔ ቋንቋው እንደማይገባኝ አውቃለሁ፤ ምክንያቱም በምሄድበት አገር ማንንም አላውቅም፣እዚያ ደግሞ የራሴ የሆነ መሬት የለኝም፣ ሥራም ሆነ ከብት ሁሉ አልነበሩኝም። እንዲሁም ደግሞ በምሄድበት ቦታ ምንም ክርስቲያኖች እንዳልነበሩ አውቃለሁ። ምናልባት አስቀድመው ሲዳማ ከነበሩት የወላይታ ወንጌላዊያን ጋር ለመሥራት ወይም የሲዳማን አማኞች ፈልጌ ወንጌላዊ እንዲሆኑ ለማገልገል ፍላጐት አልነበረኝም።

የእኔ ፍላጐት የእግዚአብሔር ቃል ባልተሰበከበት አካባቢ ሄጄ ለመስበክ ብቻ ነበር። ነገር ግን የማውቃቸው ነገሮች ብዙ ናቸው፣ እግዚአብሔር የሲዳማን ሕዝብ እንደወደደው አውቃለሁ። ወንጌላዊ እንድሆን እግዚአብሔር



እንደጠራኝ አውቃለሁ። ወንጌልን እንድሰብክ እግዚአብሔር እንደሚጠቀምብኝም አውቃለሁ። የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ የሰዎች ሕይወት ሊለወጥ እንደሚችልም አውቃለሁ። ሕይወታቸው የተለወጠ ሰዎች አዲስ ቤተክርስቲያን ሆነው ኢየሱስን እንደሚከተሉም አውቃለሁ።

መሄድህን ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ነግረሃል? በወንጌላዊነትህስ ዕውቅና አለህ? በማንኛውም መንገድ ቤተክርስቲያን ትረዳሃለች? እያሉ ሰዎች ይጠይቁኝ ነበር። ለሁሉም የእኔ መልስ «አይደለም» የሚል ነበር። እንድሄድ እግዚአብሔር ስላሳሰበኝ እሄዳለሁ አልኳቸው።

ወደ ሲዳማ ለመሄድ በምዘጋጅበት ጊዜ ማንም ይህንን ጥያቄ ቢጠይቀኝ የእኔ መልስ ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች መናገር ለምን አስፈለገኝ? ለምንስ ፍቃዳቸውን እጠይቃለሁ? ወደ ፈለግኩበት ሄጄ ወንጌልን ለመስበክ ዕውቅና እንዲኖረኝ ለምን ያስፈልጋል? ከማህበሬስ የገንዘብ እርዳታ ለምን እጠይቃለሁ? የሚል ጽኑ አቋም ነበረኝ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ከወላይታ ስሄድ የ26 ዓመት ወጣት የነበርኩ ይመስለኛል። በዚያን ጊዜ ስለ ዕድሜ ማነስ ምንም ትኩረት አይሰጥም ነበር። ገና ማግባቴ ነበርና ጉበዝ ሙሽራዬን እዚያው ወላይታ ትቼአት ወደ ለሜናዊው ሲዳማ ተጓዝኩኝ።

ዶዳና እኔ ለመንገዳችን ብዙ ምግብ መሸከም አልቻልንም። ሆኖም ግን ወደ ሲዳማ ስንሄድ የምንፈልገውን ምግብ መግዛት እንደምንችል እናውቃለን። በእንግድነት የተቀበሉን ሰዎችም ምግብ ይሰጡን ነበር። አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሲያስፈልገን ምግብ እንገዛ ነበር። ለዚህ ልዩ ጉዞዬ አሥር ማርያ ትሬዛ የነበረኝ ሲሆን፣ በሲዳማ ለመጀመሪያ ቆይታዬ ያ ገንዘብ ከበቂ በላይ እንደሚሆንልኝ አስልቼአለሁ።

የመጀመሪያ ዕቅዴ ለአራት ሳምንት ለመቆየትና ተመልሼም ባለቤቴን ወደ ሲዳማ ለመውሰድ ነበር። ከነበረኝ አሥሩ ማርያ ትሬዛ ብር ሌላ ገንዘብ አልነበረኝም። ወደ ሲዳማ የመጀመሪያዬን ጉዞ ሳደርግ በወላይታ የሚገኙትን አማኞች ምንም እርዳታ አልጠየቅኩም። እግዚአብሔር እንድሄድ ነግሮኛል። የነበረኝን ሁሉ የሰጠኝ እግዚአብሔር ነው። እዚያ በምኖርበት ጊዜም የሚያስፈልገኝን ሁሉ እንደሚያሟላልኝ አውቅ ነበርና ምንም ሳይጐድልብኝ ከሰዎች በታች ሳልሆን ኖሬአለሁ። እግዚአብሔር ይመስገን።

አባቴ ሲሞት የወረስኳቸው ሁለት ላሞች ነበሩኝ። ወደ ሲዳማ ለመሄድ ስነሳ ሃሳቤ እንዷን ላም ሸጬ ለተወሰነ ጊዜ የሚበቃኝን ገንዘብ ለመያዝ ነበር። ከዚያ በኋላ ማን ያውቃል? እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ላሜን ሳልሸጥ ገንዘብ ለማግኘት እችል ነበር። በወላይታም ሆነ በሲዳማ የወተት ላሞች በጣም

የሚያስፈልጉን ናቸው። ወተት መጠጣት እንወዳለን። ስለዚህ ላሞች ለእኛ እጅግ የሚፈለጉ ናቸው። ላሞቹን ለመሸጥ ትልቅ መሥዋዕትነት መክፈል ነበረብኝ።

## ከወንዙ ባሻገር

በዶዳ ጓደኛ ቤት የሚያርፉት የሲዳማ ነጋዴዎች አብረናቸው ወደ ሲዳማ እንድንሄድ ተስማሙ። ወሩ ጥር ቢሆንም እንኳ የብላቴ ወንዝ በጣም ሞልቶ ፈጥኖ ይፈስ ነበርና ለመሻገር አደገኛ ነበር። ጉዟችንንም እጅግ አደገኛ አደረገብን።

ከሲዳማው በኩል ከወንዙ እስከ ሸሎ የመጀመሪያ ማረፊያችን ድረስ በፈጣን እርምጃ ሦስት ሰዓት ይወስዳል። ለሦስት ሰዓት ሙሉ ስንጓዝ ውኃ፣ ቤትና የእርሻ መሬት አናይም ነበር። ጥንቃቄ የጐደላቸውን መንገደኞች ለማጥቃት ከሚዘዋወሩት አንዳንድ ሰዎች በስተቀር ምንም ሰው አይታይም።

ትላልቅ የግራር ዛፎች ለፀሐይ ሙቀት ጥሩ ጥላ ቢሆኑም በግራሩ ዛፍ ላይ ወጥተው ያለጥንቃቄ የሚጓዘውን መንገደኛ ተሰውረው ለሚቃኙት ሽፍታዎችም መጠለያ ነበሩ። በየመንገዱ ዳርና ዳር በሽፍታዎቹ የተገደሉት ሰዎች የተቀበሩበትን የድንጋይ ክምር ራሴ አይቻለሁ።

ከወላይታ ወደ ሲዳማ የሚጓዝ እያንዳንዱ መንገደኛ በዚያ መንገድ በሰላም ሲያልፍ በጣም ይደሰት ነበር። የመጀመሪያውን ምሽት በሲዳማ በሸሎ አሳለፍን። ለእኔ የውጪ አገር ወይም የባዕድ አገር ነበር፤ በተጨማሪም ቀሪ የሕይወት ዘመኔን የማሳልፍበት አገር፣ ሲዳማ!!

## አቅጣጫ መሳት

በአንድ አጋጣሚ ከአንድና ከሁለት ዓመት በኋላ የገጠሩን አካባቢና የሲዳማን ሕዝብ ተላምጄ ስለነበር ልበ ሙሉነትና በራስ መተማመን ቤተኛ ነትም ይሰማኝ የነበረ ቢሆንም፣ ከመንገዱ ዳር እኔም ተቀብሬ ድንጋይ ሲከመርብኝ ምንም አልቀረኝም ነበር። ታሪኩ እንዲህ ነው፡-

በዚያን ወቅት ሁላችንም ወደ ወላይታ ተመልሰን ለአንድ ወር ቆይተናል። ጊዜው በጋ በመሆኑ ጉዞአችን ግልጽና ያለችግር ቢሆንም፣ በወላይታ በቆየንበት ጊዜ በሲዳማ ዝናብ ይዘንብ ስለነበር ገጠሩ ሁሉ ለእኛ የተለየ ሆኖ ጠበቀን። ለካስ አቅጣጫችንን ስተን ኖሯል። የብላቴን ወንዝ እንደተሻገርን ሁሉም ነገር ልዩ ሆነብን። በዲንቶ ገበያ ከሲዳማ ወዳጆቻችን ጋር ተገናኝተን ስንጓዝ፣ ከእነርሱ፣ ከአህዮቻቸውና በቅሎቻቸው ጋር እኩል ለመራመድ አልቻልንም። እኛ ልጆቻችንን ይዘን ስለነበር እነርሱ በቀስታ ሲሄዱ ስላልፈለጉ በቆላማው ምድር ብቻችንን ጥለውን ነጐዱ። እኛም አቅጣጫው ጠፋብን።



የቆላው ምድር ሣር በጣም ከማደጉ የተነሳ ዱካቸውን እንኳ ለማግኘት አልቻልንም። በየቦታው ተዘዋወርን /ተንከራተትን/ ጊዜውም መምሸት ጀመረ።

ቀጥ ያለ ዳገት ወጥተን ቁልቁለቱን ልንወርድ ስንል ከፊታችን አንድ ቤት አየን ወዲያውም ተጣራንና የሲዳማ ሰዎች ሲወጡ ወደ ሰሜን ሲዳማ አቅጣጫ የሚያደርሰውን ጐዳና ጠየቅናቸው። ሰዎቹ ተቀምጠው ያወሩ ነበር። ሰላም አልናቸው በቀዝቃዛ ስሜት አጸፋውን መለሱልን። ሌሊቱን በቤታቸው ለማሳደር የመጋበዝ ፍላጐት እንደሌላቸው ግልጽ ነበር። ወደ ሰሜናዊው ሲዳማ የሚያመራውን መንገድ በማመላከት እንዲረዱን ጠየቅኋቸው እነርሱም፡- የመጣችሁት ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ በጣም ርቃችሁ ነው፣ ወደ ሰሜን አቅጣጫ የሚወስዳችሁ መንገድ ከወደኋላችሁ ቀርቷል። ስለዚህ ዋና መንገዳችሁን ለማግኘት ወደኋላችሁ መመለስ ይኖርባችኋል ብለው ወደመጣንበት አቅጣጫ ሲመልሱን ሞከሩ።

ብዙ ባላውቅም አነጋገራቸው እውነት አለመሆኑን ተረዳሁ። አቅጣጫ ስንስት የሲዳማን ቋንቋ ብዙ ስለማንችል የመግባባት ችግርም ነበረብን። የከፋ ነገር እንዳለም ጠረጠርኩ። ሰዎቹ ለትንሽ ጊዜ ንግግራቸውን አቆሙ፣ ሁለቱ ሰዎች ከሌሎቹ ተለይተው ቆሙና ለብቻቸው መነጋገር ጀመሩ። ከዚያም ቅርብ ወደ ሆነው መንደር እንወስዳችሁ አሉን ። ከኋላችን ወዳለው ጫካ ሊወስዱን መሞከራቸው ነበር። እኛም እንደማንሄድ ነገርናቸው። ጨለማው እያየለ በመምጣት ላይ ስለነበር በሣሩ ላይ ተቀመጥን። ሁለቱም ሰዎች ትተውን ወደ ቤት ሄዱ እንደገና እዚያ መነጋገር ጀመሩ።

ከነዚህ በግልጽ ሊረዱን ከማይፈልጉ ሰዎች እንድንርቅ ወሰንኩ። በዚያን አጋጣሚ የጨረቃ ብርሃን ወጣልን። ወዲያውም ትልቅ ጐዳና አገኘንና በአቋራጭ ሮጠን ገባን፣ ከዚያም መንገዱን ተውንና በትላልቅ ሣር የተሸፈነ ቦታ በማግኘታችን ወደዚያው ገባንና በዛፎች ሥር በሣሩ ውስጥ ሰፍረን ሌሊቱን እዚያው ተኝተን አደርን።

በነጋታው ስንነሳ ሌሎች የሚያርሱትን ሰዎች አገኘን። እነርሱም በሼሎ በኩል ወደ ይርጋለም ከሚሄዱ ነጋዴዎች ጋር አገናኙን። ከነርሱም ጋር ወደ ይርባ ገበያ ተጓዝን። ከዚያ ወደ ቤታችን የሚወስደንን መንገድ አገኘን። አምስት ሰዓት በሚሆን አካባቢ ወደ ሸሎ ደረስን። አቅጣጫችንን ብንስትም ወደ መጀመሪያው ጉዞአችን ለመመለስ ቻልን።

## የሁለተኛው ቀን ጉዞ

በሁለተኛው ቀን ከሸሎ ወደ አርኬ ተጓዝን። በኮረብታና ግራር ዛፎች በተሞላው በቆላማው መሬት ስንጓዝ መሬቱ ለም እየሆነና እርሻማ ወደሆነው አካባቢ ደረስን ሰዎችም በየማሳቸው ሲያርሱ እያየን አለፍን።

አስቀድመን አብረናቸው የነበሩት ነጋዴዎችም ወደ አንድ ዘመዳቸው ቤት ጉራ ብሰው ኖሮ ደረስንባቸው። የዘመዳቸው ስም ቦኮ ይባላል። ከነጋዴዎቹ ጋር ሌሊቱን በቦኮ ቤት እንድናሳልፍ ተጋበዝን። በኮንና ቤተሰቡን ስንገናኝ በሕይወታችን የመጀመሪያ ጊዜያችን ነበር።

በእርግጥ እኛ አናውቅም እንጂ በኮ በሲዳማ ካሉን ምርጥ ወዳጆቻችን አንዱ ሆኖልናል። እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ወደ ትክክለኛ ቦታ እንዳመጣን አየሁ። ያ ቤተሰብ ሁሉ ወንጌልን ይሰሙ ዘንድ እግዚአብሔር ያዘጋጀው አጋጣሚ ነበር እና ሁሉም ቃሉን ሰምተው ሳይዘገዩ ጌታን ተቀበሉ። በሰዎች አመለካከት የሚሆን ባይሆንም ለእግዚአብሔር ግን ጊዜው ሆነ። ለእርሱ የሚሳነው ነገር የለምና።

# ሌሎች ወንጌላውያን

ሾንጋ ሳዴቦ የሚባለው ሌላው የወላይታ ወንጌላዊ በሲዳማ ከ1939-1957 ዓ.ም ድረስ እንዳገለገለ ሰማሁ። እርሱ የመጣው በወላይታ ኮይሻ ከሚባለው ወረዳ ነበር። የሚሠራውም ሼሎ በሚባለው በቆላማው አካባቢ ሲሆን ያ ቦታ እኔ ለጊዜው ሄጄ ካረፍኩበት አንድ ሰዓት ተኩል ያህል በእግር ያስኬዳል። በሲዳማ በየትኛው ቦታ ሄጄ እንደምሰፍር የማውቀው ነገር አልነበረም። ብቻ ምንም ክርስቲያኖች በሌሉበት ቦታ ለመስፈር እፈልግ ነበር።

# ቋንቋዎች

ወደ ሲዳማ በደረስን ጊዜ እኔና ዶዳ ከሦስት ቋንቋ ጋር እንታገል ጀመር። የራሳችንን የወላይትኛ ቋንቋ እንናገራለን፣ በሰሜናዊ ሲዳማ ደግሞ ሰዎች በሲዳሚኛ ቋንቋ ይነጋገራሉ። ከቦታ ወደ ቦታ የሚዘዋወሩ ብዙ ሰዎች ትንሽ ትንሽ የአማርኛ ቋንቋ ይረዳሉ። ወላይትኛ ቋንቋችን ሲሆን፣ ከአማርኛና ሲዳሚኛ ቋንቋዎች ጋር እንታገል ነበር።

እግዚአብሔር ይመስገንና እኛም ሦስተኛውን ቋንቋ ተጠቅመናል። እንደ እውነቱ ከሆነ አንዳንድ ሰዎችን ለመግባባት ሲዳሚኛ ቋንቋ እስክንለማመድ አማርኛው ጠቅሞን ነበር። እግዚአብሔርም በሦስተኛው ቋንቋ ተጠቅመን ሰዎችም የምንናገረው መልዕክት ገብቷቸው የእውነትን ቃል እንዲሰሙ ረድቷቸዋል። ዘዴው የሚስማማ ባይሆንም እግዚአብሔር ግን ሁልጊዜ በሚስማማና በሚመች መንገድ ይጠቀማልና አድርጉልናልም!! ይህም ማለት እግዚአብሔር ስለረዳን ለቋንቋው ባይተዋር መሆናችን አገልግሎታችንን አላስተጓጉለብንም ማለት ነው።



# ሃይማኖት በሲዳማ ውስጥ

በሰሜናዊው ሲዳማ ሕዝቡ ሁለት ሃይማኖት ነበረው። አንዱ ባህላዊ ሲሆን፣ ሁለተኛው ሕዝባዊ ነበር። በአንድ መንገድ ወይም በሌላ እያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖረው ይፈልጋል።

የመጀመሪያው ባሕላዊው ሃይማኖት ሰዎች ከፈጣሪያቸው ጋር መልካም ግንኙነት ለማግኘት የሚፈልጉበት ነው። ኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር እንደለያቸው የምንነግራቸው አልነበረም። ያንን ራሳቸው ያውቁታል። ነገር ግን ከኃጢአታቸው የተነሳ፣ ሰዎች ከልባቸው መፍትሄ ሲፈልጉ ወደተሳሳተ አቅጣጫ የሚሄዱ መሆናቸውን ስለሚያውቁ በፍላጋቸው የሰዎችን እርዳታ ይሻሉ። እኛም ያ አቅጣጫ የሳተ ፍለጋቸው የሰይጣን አምልኮ መሆኑን እናስረዳቸዋለን።

ዝነኛው ሃይማኖት ክርስትና እምነትን በመሸፈን በሲዳማ ሕዝብ ላይ ጫና ይፈጥሩ የነበሩት የወቅቱ መንግሥትና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዩች ናቸው።

ከ1937-1938 ዓ.ም የገገር መደብ የነበረው የአማራው መንግሥት ሕዝብን ክርስትና ማስነሳት በማለት ለማስለጠን ያደረገው ጥረት ከባድ ነበር። ያ ስህተት አልነበረም፣ ዳሩ ግን የውኃ መርጨት የሕዝቡን ልብ ወደሚገባው እውነት አልለሰወጠም። ከፍርሃትም ነፃ አላወጣቸውም። የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩም አዲስ ኃይል እና ሕይወት አልሰጣቸውም ወይም በአዲስ ኃይል እና ሕይወት መራመድ አልቻሉም።

# ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር

በሰሜናዊ ሲዳማ በቀረን ወር ውስጥ ዶዳና እኔ በአካባቢ እየተዘዋወርን እንሰብክ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በኮ አብሮን ስለሚሄድ ሦስት እንሆናለን። እግዚአብሔር በመልካምነቱ አማርኛ መናገር ከሚችል ሰው ጋር አገናኝቶናል።

በኮ ከእኛ ጋር በሚሆንበት ጊዜ በአማርኛ እየሰበክን እርሱ ወደ ሲዳሚኛ ይተረጉምልን ነበር። ሁለታችን ብቻ በምንሆንበት ጊዜ ከአድማጩ ህዝብ መካከል የአማርኛ ቋንቋ የሚችል እንዳለ አረጋግጠን እንዲተረጉምልን እንጠይቃለን። በወቅቱ በየአካባቢው እየተዘዋወርን መስበክ ፍፁም የሚስማማ መንገድ ባይሆንም፣ ለጊዜው ማድረግ የምንችለው በዚያ ዓይነት መንገድ ቃሉን ማሰራጨት ነበር።

ዶዳና እኔ ዘሩን ከዘራን ወይም ወንጌልን ከሰበክን አንድ ቀን መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንዲበቅል ያደርገዋል ብለን እመንን። የሚቀበሉንን ሰዎች ፍለጋ ወደየአካባቢው አልሄድንም ወይንም ጊዜያችንን ከቦኮ ጋራ አላጠፋንም።

ሰዎች በሚያርሱበትና በሚያጭዱበት ቦታ ለገበያተኞችና በቀብር ቦታ ሁሉ ቃሉን እንሰብክ ነበር። የበለጠ ፍሬያማ ቦታ ግን በየቤታቸው መስበክ ነበር።

## የቀብር ክስተት

ምናልባት የተሻለ አጋጣሚያችን የቀብርና የለቅሶ ክስተት ሲፈጠር ነበር ለሲዳማ ሕዝብ ከቀብር መነሻ ጀምሮ ለ3 ቀናት የሚቆይ የለቅሶ ሥርዓት ነበራቸው። ከዚያ በኋላ ለዋናው ለቅሶ ቀነ ቀጠሮ ይያዛል፣ ያ ብዙውን ጊዜ ከቀብሩ በኋላ ጥቂት ሳምንቶች ቆይቶ የሚደረግ ነው። በህብረተሰቡ መካከል ያን ጊዜ ትልቅ የተቀናጀ ዝግጅት ይደረጋል።

ለሥርዓቱ ሃላፊ የሆኑ ሰዎች ከበሮ እየመቱ ድምፅ ሲያሰሙ ሁሉም ሰው ተሳታፊነቱን ያውቃል። የከበሮው ድምፅ ለእኛም ጆሮ እንደ ሙዚቃ ይሆንልን ነበር። ቃሉን አስምተን ወደ ጌታ የሚመጡትንና የምንማርካቸውን አድማጮችም እንደምናገኝ እናውቃለን።

በዚያን ጊዜ ሰዎች ትልቅ የዝግባ ዛፍ ቆርጠው በሜዳ ይተክላሉ የአካባቢውም ሰዎች ይሰበሰባሉ። የለቅሶውም ሥርዓት በሦስተኛው ቀን ያከትማል። በለቅሶው ሜዳ የሰው ብዛት ትልቅ ገበያ ያክል ነበር። በዚያን አጋጣሚ በሙቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች እንሰብካለን። በየቦታው ስንዘዋወር በአንድ ዳርቻ ላይ ቆመን መስበክ ስንጀምር ሕዝቡም እየተሰበሰበ ያዳምጠን ነበር።

የምንሰብከው ስብከትና የስብከታችንም ስልት ለህዝቡ አዲስ ነበር። የኦርቶዶክስ ወይም የእስላም ወይም የባህል እምነት ተከታዮች እንደኛ ተመሳሳይ ስብከት አይሰብኩም። ማናቸውም ቢሆኑ ከቤት ወደ ቤት እየሄዱ ወንጌልን አያስተምሩም።

እኛ በምንሰጠው አገልግሎት ላይ ስሜት የነበራቸው ቢሆንም ለእነርሱ ግን ነገር ሁሉ እንግዳ ነበር። ሰዎች ታዲያ መልካሙን ዜና መስማት ይፈልጋሉ። እኛም ለመስበክ እንፈልጋለን። ስለዚህ ያ ለእኛ ወርቃማ አጋጣሚ ነበር።

በባሕላቸው የሚያጋጭ ቢሆንም ሕዝቡ ግን ባልተለመደው ስልታችንና በምንሰብከው ስብከት አልተከፋም። ሰዎች ይሰማሉ ነገር ግን በመጀመሪያው ወር ከቦኮና ከባለቤቱ በስተቀር ማንም ያመነ አልነበረም። ያ ማለት እኛን ተስፋ የሚያስቆርጠን አልነበረም፣ ፍሬ የማፍሪያው ሰዓት በእግዚአብሔር እጅ እንዳለ እናምናለን።



## ተቃውሞ

ሰዎች ስብከታችንን ለምን እንደሚለሙ ምናልባት ያስደንቃችኋል። ለማን ሄደን እንደምንሰብክ ተጨንቀን አናውቅም። እያንዳንዱ ሰው በማንኛውም ቦታ ሊሰማን ይፈልጋል። ስለዚህ ምንም ዓይነት ተቃውሞ በፍፁም አላጋጠመንም። በነፃነት ቃሉን እንሰብካለን የሰዎችን ልብ የሚከፍተው ግን እግዚአብሔር ነው እንላለን።

ለመስበክ በምንሄድበት ቦታ ሁሉ ሰዎች ሲሰሙን ይፈቅዳሉ። የሚሰሙን ምክንያት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ከኃጢአታቸው ነፃ ሲወጡ እንደሚችሉ ስለምናስተምራቸው ነው።

ሁል ጊዜ የሚወስዱት እርምጃ «ይህ እውነት ይመስላል የሚል ቃል ሲሆን በየቀኑ በዳንትና በቁልቁለት እንዲሁም በጨለማ በመመላለስ ብናስተምርም በዚያ ወር ውስጥ አንድ ቤተሰብ ብቻ ክርስቶስን ተቀብሏል።»

ከሙቶ ለሚበልጡ ሰዎች እንሰብካለን፣ ወዲያውኑ ጌታን አለመቀበላቸው ግን ብዙም አያስጨንቀንም። እኛ የዘራነውን የቃሉን ዘር ለወደፊት ባሉት ዓመታት እኛ ልንሰቅም ወይም ሌሎች አገልጋዮች ሊለቅሙ ይችላሉ በማለት በራሳችን እንተማመናለን።

ከ50 ዓመት በኋላ በሰሜናዊ ሲዳማ 400 ማህበር ያህል ከቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ጋር ተጣምሯል። ከሌሎች የእምነት ተከታዮች ህብረት ጋር ደግሞ ብዙዎች ተጣምረዋል። በእያንዳንዱ ቀን ዶዳና እኔ በተሰያየ አቅጣጫ ተቀምጠን በተቻለን መጠን ብዙ ሰዎችን እናነጋግራቸው ነበር።

## የክፉ ሠራተኞች «የቃልቻዎቹ» ዕቅድ

የባህላዊ ሃይማኖት ባለውቃቢዎች እንደ ካህናትና እንደ ነቢያት የሚያስመስሉ ሰዎች በሕዝቡ ላይ ትልቅ ፍርሃት ይለቅቁባቸዋል። ስብከታቸው፡- ይህንንና ያንን ባታደርግ ከእንስሳቶችህ አንዱ ይሞታል፣ ወይም አንተ ራስህ ትታመማለህ፡- የሚል ነበር። ከባድ ማስጠንቀቂያ እና ማስፈራሪያ የተሞላ ስብከታቸው በሰዎች ልብ ውስጥ ፍርሐትን ለቅቋል።

ይህንን ሲናገሩ ሰዎች የሚሰሟቸው ለምንድን ነው? ብላችሁ ብትጠይቁኝ፡- ውሸታሞች መሆናቸውን የሚነግራቸው ባለመኖሩ ነው። ፍርሃት ከሞት ቀጥሎ የሚያስፈራ ነውና እነዚያ ባለውቃቢዎች ሰዎችን በፍርሃት ባርነት ውስጥ እንዲኖሩ አድርገዋቸዋል።

ስለዚህም ሰዎች የምናቀርብላቸውን ወንጌል ጠንክረው ይቀበሉ ነበር። ክርስቲያን የሆነው ሁሉ ባለውቃቢዎቹን እየተከራከረ የማታለያቸውን ዘዴ

ያቃልልባቸው ጀመር። እነዚያ ቃልቻዎች በሁብረተሰቡ መካከል የሚፈሩ ኃይለኞች ነበሩ። በተለይም በመርገም በመባረክ፣ በመተንበይና በመፈወስ ተቀባይነት የነበራቸው ሆነው ይከበሩ ነበር። ለንግግራቸው ትኩረት በመስጠት ግን በፍፁም አንፈራቸውም። እግዚአብሔር ፍርሃትን ከውስጣችን አውጥቶልናል። እንዲያውም ቃልቻዎቹን ለማነጋገር ቀጠሮ እናስይዝ ጀመር። አንዳንድ ጊዜ ቀጠሮ ይሰጡናል። ስለ ሁለት መንገዶችም እንነግራቸው ነበር። ሰፊው መንገድ ወደ ጥፋት የሚወስደው ሲሆን፣ ጠባቡ መንገድ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖር የሚያደርግ ነው። የምንናገረውን ቢቃወሙም፣ ሊጎዱን ግን አይቃጡም ነበር።

## ብራዶ

በዚያን ጊዜ በሰሜናዊ ሲዳማ ከነበሩት ቃልቻዎች በጣም ታዋቂውና በመካከለኛ ዕድሜ ውስጥ የነበረው ብራዶ ይባል ነበረ። ብራዶን በአካባቢው እያንዳንዱ ሰው ያውቀዋል። ብዙ የመንግሥት ባለሥልጣኖች እንኳን ሳይቀሩ ወደ እርሱ የሚመለከቱና የሕዝብ ተወካይ ወይም ተሿሚ አድርገው ለይተው የሚያዩት ነበሩ።

በሰሜናዊ ሲዳማ መሬቱ በሰፋት የተቆራረሰ እየመሰለ ከደጋው እስከ ቆላማው አካባቢ ይደርሳል። የተቆራረሰው አካባቢ ከወደኋላ መኖሪያችን የሆነው አፋራራ አካባቢ ባዳ ይባላል። የሕብረተሰቡ አካባቢ ስም ይመስላል። ብራዶ የተባለው ሰውዬም ባለዝና የነበረና ብዙ ቤቶች የነበሩበትን መሬት ለራሱ ያደረገ ነው።

በአካባቢው በጣም ሀብታም በመሆን ይታወቃል። በዘመኑ የአማራው መንግሥት የገገር መደብ ተወካይ የነበሩት ራስ አደፍርሰው ሁልጊዜ ብራዶን ይርጋለም እያስጠሩት ያማክሩት ነበር።

አንድ ቀን እኔና ዶዳ ዙሪያው በትላልቅ የጠርብ እንጨቶች ወደተሠራው ግቢ ደረስን። ብራዶ የክፍለ ሀገሩ ዋና ከተማ ወደነበረው ወደ ይርጋለም ለመሄድ ተሰናድቶ ነበር። በዚያን ቀን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በየቦታው ፈረሶችና በቅሎዎች ይዘው ቆመዋል። ደጃፉ ትልቅ ገበያ የቆመበት ቦታ ይመስላል።

ወደ ግቢውና ከዚያም ወደ ትልቁ ቤት ለመግባት ፈቃድ ጠየቅን የጥበቃ ሠራተኞቹም እነማን እንደሆንንና ለምን እንደመጣን ሲጠይቁን፣ ነገርናቸው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ መጥቷል፣ ሞቶም ተቀብሯል ፣ በሦስተኛው ውም ቀን ከሞት ተነስቷል። በእርሱ የሚያምን ሁሉም ይድናል። የማያምኑት ሁሉም ይፈረድባቸዋል። ገምቱ! የብራዶ ቀኝ እጅ የነበረውና የአማርኛ ቋንቋ መናገር የሚችለው ሰው በሰዎቹ መካከል ቆሞ ያዳምጠን ነበር።



የምንሰብከውን ሁሉ ወደ ሲዳሚኛ ቋንቋ እየተረጐመልን የምንለውን ሁሉ ለእያንዳንዱ ሰው ያሰማልን ነበር። አለባበሱም ሆነ አነጋገሩ የዘመኑን ባለሥልጣን ይመስል ነበርና አስደንቆንም ነበር።

ከዚያም ብራዶን ራሱን ማነጋገር እንደምንፈልግ ነገርነው። ባለሥልጣኑም ዛሬ ለእርሱ እንደ በዓል ቀን ስለሆነ ጐብኚዎችን ተቀብሎ ማነጋገር እንደማይችል ነገረን።

ነገር ግን የተባለውን ሁሉ ለብራዶ እንደሚነግር ቃል ገባልን። በዚያን ጊዜ በባለሥልጣኑ ገጽታ ላይ ሁለት ስሜት ይነበብ ነበር። አንዱ የአክብሮትና ወዳጅነት ስሜት ሲሆን፣ ሌላኛው ስሜቱ የግልፍተኝነትና የጨካኝነት ነበር። ፊት ለፊታችን አንድ ነገር ይናገራል፤ ከበስተኋላ ግን ተቃራኒ ገጽታ እንዳለው ያስታውቅበታል።

ያን ዓይነት ባህርይ ቢያሳዩንም ፊታቸውን አይተን ባለሥልጣኖቹን አልፈራናቸውም። ከግቢው እንደወጣን የብራዶ ቀኝ እጅ የሆነው ሰውዬ፣ ለተሰበሰበው ሕዝብ እንዲህ አላቸው። የወላይታ ሰባኪዎች ያሉትን ሰማችኋቸው አይደለም? ተከተሏቸውና የፈለጋችሁትን አድርጓቸው፣ ስለሚመጣው ነገር ሁሉ ሃላፊነቱን እኔ እወስዳለሁ። ችግር ይገጥመናል ብላችሁ አትጨነቁ እኔ አድናችኋለሁ በማለት እንዲደበድቡን ተናገራቸው።

እኛም እንደማንፈራ ነገርነው፣ እግዚአብሔር ልኮናልና እርሱ ይታደገናል አልነው። በዚያን ወቅት ምንም የደረሰብን ነገር አልነበረም።

## ሰይጣን

ዕለት በዕለት በምንሰብከው ስብከትና በባህላዊ ሃይማኖት መካከል ውጊያው እየተባባሰ መጣ። በፀለይንና በሰበክን ጊዜ ሁሉ ወደ መንፈሳዊ ውጊያ እንገባለን። ሰዎች ሁልጊዜ ስለ ሰይጣን ይጠይቁናል። ሰይጣን ምን ያደርገናል? ሰይጣን ሊሞት ነውን? እነዚህን እየተቃወሙት የሚሰብኩትን ሰዎችንስ ይገድላቸዋልን? እያሉ ሲጠይቁን፣ የእኛ መልስ ምን ጊዜም ተመሳሳይ ነው። «ሰይጣን ውሸታም ነው ዘወትር ሊጎዳችሁና ሊያታልላችሁ ይፈልጋል፣ ከባርነት በስተቀር የሚሰጣችሁ ነገር የለም።» በኢየሱስ እመኑ እርሱም ከኃጢአት ነፃ ያወጣችኋል እንላቸዋለን።

## ሙስሊሞች

ሙስሊሞች በዚያን ጊዜ በአካባቢው ትልቅ መስጊድ ሠርተው ነበር። ብዙ የሲዳማ ሰዎችም ሙስሊም መሆን እንፈልጋለን ቢሉም ሰላምንና ነፃነትን ፍሰጋ የሚያደርጉት ሌላው የመፍትሔ ክፍል ነው። ባሕላዊ ሃይማኖታቸው

ነፃነት ሲሰጣቸው ባለመቻሉ ምናልባት ሙስሊም በመሆን ሰላምን የሚያገኙ እየመሰላቸው ነው።

በተለያዩ ጊዜያቶች ዶዳና እኔ ወደ መስጊድ እየሄድን እዚያ ለተሰበሰበው ሕዝብ እንሰብክ ነበር። በአጠገባችን ዳንባራ ኬላ በሚባል አነስተኛ ከተማ ውስጥ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ነበር። ግን የሚተባበሯቸው የሲዳማ ሰዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው። የቤተክርስቲያኑ አምልኮ የሚካሄደው በግዕዝ ነው። ያንን የጥንት ቋንቋ ማንም ሊረዳው አይችልም። እዚያ የሚኖር አንድ ቄስ ምንም አይቃወመንም። በኋላ ግን ከሌላ ቦታዎች የመጡት ብዙ ተቃውሞ አስነሱብን።

## አስተርጓሚዎች

ለወር ያህል በአስተርጓሚ መስበክ አድካሚ ልምምድ ነበር። በግልጽ ለመናገር ሥራችን ግቡን በመምታቱ ተደንቄአለሁ። ከወላይታ እንደተመለስኩ ከአስተርጓሚ ነፃ መሆን እንዳለብኝ ተገነዘብኩ። የሲዳሚኛ ቋንቋ ተምሬ በዚያ መስበክ አስፈላጊዬ ነው ብዬ አሰብኩ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ «እግዚአብሔር ተናግሯል» የምትል ትንሽ መጽሔት በሲዳሚኛ እንደምታስፈልገን ተገነዘብን። ዶዳ በሸሎ የሚኖር ጓደኛ ነበረው፣ ያ ሰው ሦስት ቋንቋ ይችላል። ስለዚህም ወደ ሸሎ ተጓዝን። ከአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን ገለበጥን። ከዚያም ትርጉሙን በሲዳሚኛ ቋንቋ ከትንሽ ማብራሪያ ጋር ጻፍን። ወደ አርኬ በተመለስን ጊዜ ያንን ጥቅስ ለሰዎቹ እያነበብኩላቸው ያለማስታወሻዬ ለመናገር እንድችል በቃሌ ማጥናት ጀመርኩኝ።

## ዶዳ ሄደ

በአርኬ ለወር ያህል ከቆየ በኋላ ለእኔና ለዶዳ በየፊናችን የምንሰማራበት ጊዜ ደረሰ። የእኔ አዕምሮ ተዘጋጅቷል፣በሰሜናዊ ሲዳማ እንድሰብክ እግዚአብሔር ተናግሮኛል። ለዚሁም ምንም ጥርጣሬ ስላልነበረኝ ወደ ወላይታ ተመልሼ ጉበዟን ሙሽራዬን የጳውሎስን እናት ወደ ሲዳማ ለማምጣት መዘጋጀት ፈለኩኝ።

በሲዳማ ኑሮው ከእኔ የበለጠ ለእርሷ አስቸጋሪ መሆኑን ባውቅም አዕምሮዋን አዘጋጅታ ስለነበር አብራኝ ለመሄድ ፈልጋለች። ለአገልግሎታችን የነበራት ትጋት እኔንም ከመጠን በላይ እንድነሳሳ አድርጎኛል። ስለዚህ እርሷ በፍፁም አታማርርም እኔም እንድማረር አትፈልግም። ዶዳ ለቤተሰቦቹ ብቸኛ ስለነበረ ያረጁ ወላጆቹን ለመንከባከብ ወደ ወላይታ የመመለስ ግዴታ



ነበረበት። እግዚአብሔር ለእኔ የሰጠኝን ጽኑ እምነት ለእርሱ ስላልሰጠው ይገፍው በሲዳማ ለማቆየት ያደረኩት ጥረት አልነበረም።

## ኑሮ መመሥረት

በአርኬ በነበርኩበት ወር ለሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት መኖሪያችን የሚሆነንን ትንሽ ቤት ሠራሁ።

የቤታችን ግድግዳው የተሠራው በተፈለጠ ጠርብ ሲሆን፣ በጥልቁ ተቆፍሮ ተተክሏል። ጣራው በቀጫጭን ጨፈቃዎች ታስሮ እላዩ በሙሉ በሳር የተሸፈነ ነበር። የሲዳማዎች ቤቶች ሁሉ እንደዚያ ናቸው። በጣም ርካሽ፣ በበጋ ቀዝቃዛ ሲሆን በክረምት ሌሊቶች ሞቃታማ ነበር።

ቦኮ ትንሽ መሬት ቆርሶ ለጥቶኝ ስለነበረ በቆሎና ጤፍ በመዝራቴ ለምግባችን አልተቸገርንም። ቤቱና እርሻዬ ለቦኮ ወደ ሲዳማ ለመመለሴ ዋስትናው ነበር። ከወላይታ ቤተክርስቲያን ምንም ደሞዝ ይከፈለኛል ብዬ አልጠበቅኩም። በዚያን ጊዜ በሰሜናዊ ሲዳማ ምንም ቤተክርስቲያኖች ስላልነበሩ ከሲዳማ ሰዎችም የምጠብቀው እርዳታ አልነበረም።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ የመጣሁበት የወላይታ ቤተክርስቲያን እንደ ወንጌላዊ መዝግበውኝ በየወሩ አራት ብር ለጥቂት ዓመታት ይከፍሉኝ ነበር። ከዚያም ክፍያውን አቆሙብኝ። በመጀመሪያዎቹ ዓመታትማ ከነርሱ ምንም አልጠብቅም ነበር። ታዲያ የሚያስጨንቀኝ ነገርም አልነበረም።

ሁልጊዜ የሚያስፈልገኝን ወደሚያቀርብልኝ እግዚአብሔር እመለከት ነበርና እርሱም ሁሉን አድርጎልኛል።

## የማንበብና የመጻፍ ችሎታ

በጠቅላላው አገልግሎቴ ውስጥ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ከሌሎቹ የበለጠ ጠቀሜታ ያለው ነበር። የተጻፉ መጽሔቶች በሲዳሚኛ ቋንቋ ለምን እንደሌሉና በጣም ጥቂት የሆኑ መጽሔቶች በወላይትኛ ቋንቋ መገኘታቸው ያስደንቃችሁ ይሆናል። የነበረን ብቸኛ መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ የተጻፈ ነበር።

ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል አንብበን ለመረዳት የአማርኛን ፊደሎች ማጥናት ያስፈልጋል። ብዙዎቹ አዳዲስ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል ለራሳቸው ለማንበብ ይሻሉ። በቤተክርስቲያን መስበክ ባይችሉም እንኳን ለአንዳንድ ሴቶች ማንበብን አስተምረናል።

ብዙውን ጊዜ ወንዶቹ ሴቶቻቸው ማንበብና መጻፍ እንዲማሩ አይፈልጉም። በሁለተኛ ቋንቋቸው መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንዲችሉ ከዶዳ ጋር በነበርኩ ጊዜ ቦኮንና ባለቤቱን አማርኛ ፊደልና ንባብ አስተምሬአለሁ። ሁላችንም የምንጠቀምበት መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሆኖ ትርጉሙ ሁሉም ላይገባን ቢችልም ዋና ዋና ነጥቦችን እንገነዘብ ነበር።